ዘጠኝ

ሪቫይቫል እና መንደርደሪያዎቹ

ሪቫይቫል በምንም ዓይነት መሰናከል የለበትም። እንዲያውም እድሚው አጭር ናት። ያችኑም አደነቃቅፈን ልናሳጥራት አያስፈልግም። ብዙዎች ለብዙ ጊዜ አርግዘውታል። እርግዝና በሚያስከትለው የጤና መጓደል፣ ናፍቆትና ስጋት ውስጥ አልፈዋል። እንበለ ዕረፍት ለአያሌ አመታት አምጠውታል። ብዙ ዋጋ ተከፍሉበታል። ስለዚህ መጨንገፍ የለበትም። በአጭር መቀጨት የለበትም። ማደግ፣ መመንደግ ነው ያለበት።

ይህንን የምንፈልግ እኛ ብቻም አይደለንም። እግዚአብሔር እራሱም ይፈልገዋል። እርሱማ ሪቫይቫልን ያማጠው ለአያሌ አመታት ሳይሆን ለዘላለም ነው። ከዚህ በኋላ ላለው ዘላለም ሳይሆን ከዚህ በፊት ለነበረው ዘላለም። በእርግዝናችን የእርሱን እርግዝና ነው የተጋራነው። ምጡን ነው በምጣችን ያማማጥነው። በግለሰብና በብሔረሰብ፣ በአገርና በአህጉር፣ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ረገድ ብዙ ቅድመ ዝግጅቶች አድርጓል። ብዙ ጠብቋል። ስለዚህ ለእርሱም ሪቫይቫል መጨንገፍ የለበትም። በአጭር መቀጨት የለበትም። ማደግ፣ መመንደግ ነው ያለበት።

የእግዚአብሔርና የእኛ ፍላጎት መገጣጠሙ መልካም ነው። በቂ ግን አይደለም። ልጅ ስለ ተወለደ ብቻ ያድጋል? ባለፈው ምዕራፍ ሪቫይቫልን እንዲጨነግፍ፣ በአጭር እንዲቀጭ፣ ከሚያደርጉት መሰናክሎች ውስጥ አንዳንዶቹን አንስተናል። በዚህ ምዕራፍ ሪቫይቫልን እንዲያድግና እንዲመነደግ ከሚያደርጉት መንደርደሪያዎች ውስጥ አንዳንዶቹን እናነሳለን። መሰናክሎቹ ሪቫይቫልን ወደ ኋላ ይጎትቱታል። ያደናቅፉታል። ይጥሉታል። መንደርደሪያዎቹ ደግሞ ወደ ፊት ይገፉታል። መንገዱን ምቹ ያደርጉለታል። ያስሮጡታል።

ታሪክን የምናጠናው እንዳንደግመው ነው

ሰዎች ከታሪክ ይማራሉ? እናጥብበው። ቤተ ክርስቲያን ከታሪክ ትማራለች? እኛ ከታሪክ እንማራለን? ጥያቄው አከራካሪ ጥያቄ ነው።

አንዳንዶች ሲመልሱ ሰዎች ከታሪክ ቢማሩማ ኖሮ ለምን "ታሪክ እራሱን ይደግማል?" ይላሉ። መድረኩ ይለዋወጣል። ተዋንያኑ ይለዋወጣሉ። ተውኔቱ ግን ያው የሰለቸን አሮጌ ተውኔት ነው። ለስንተኛ ጊዜ እንደ ሆነ አሐዙን ዘነጋነው እንጂ ያንኑ ቀድሞ ያየነውን ተውኔት ነው አሁን እንደገና በሌላ መድረክና በሌሎች ተዋንያን እንድናየው የምንገደደው። በእውነት ታሪክ እራሱን ይደግማል።

ሌሎች ደግሞ "ከታሪክ የማይማሩ ሁሉ እንዲደግሙት ተፈርዶባቸዋል" ይላሉ። ታሪክን የሚደግሙት ሰዎች ሁሉ ሳይሆኑ ከታሪክ የማይማሩ ሰዎች ብቻ ናቸው ማለታቸው ነው። ታሪክን መድገም የግዴታ አይደለም ማለታቸው ነው። ይህም ደግሞ እውነት ነው። ታሪክን መድገም የግዴታ አይደለም።

ስመ ጥሩው ደራሲና ገጣሚ ከበደ ሚካኤል "አዝማሪና የውሃ ሙላት" በተሰኘ ግጥማቸው "ታሪክ እራሱን ይደግማል" ከሚሉት ጋር የወገኑ ይመስላሉ። በዚያ ግጥም ውስጥ ወንዝ ሞልቶ አላሻግር ያለው አዝማሪ በወንዙ ዳር ቆሞ፣ መሰንቆውን እየመታ፣ ግጥሙን እየደረደረ ውሀውን ያሞግሰዋል። ይህንን ያየ ሌላ መንገደኛ ምን እያደረገ እንዳለ አያ አዝማሪን ይጠይቀዋል። አዝማሪውም ልኩ ተነክቶ ውሀው ይጎድልለትና ያሻግረው እንደሆነ በማለት በዜማና በቅኔ እያሞጋገሰው እንዳለ ይገልጥለታል። በአዝማሪው አለማስተዋል የተደነቀው ጠያቂ ውሀው ከመውረዱ ተግ እንደማይል፣ ሁልጊዜም የሰማው እየሄደ ያልሰማው እንደሚመጣ ያስገነዝበዋል።

ከበደ ሚካኤል ይህንን እጅግ ጥልቅ የሆነ ፍልስፍና ያቀረቡልን እጅግ ውብ በሆነ ግጥም ነው። ከትንሽ አንሶ እስከ ትልቅ ድረስ ባለው የታሪክ ሂደት ውስጥ የዚህን ፍልስፍና እውነትነት በየጊዜው የምናስተውለው ቢሆንም እንኳን እውነትነቱ ለሁልጊዜና ለሁሉ ሁኔታ ነው ለማለት ደግሞ አንችልም። በወራጅ ውሀና በሰዎች መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ሰው ስለ ሰማ ወይም ለመስማት ከግስጋሴው ተግ ይላል። ሁልጊዜም እንኳን ባይሆን ከሰማው ይማራል። አቋሙንና አቅጣጫውን ይቀይራል። የትም ቢሆን፣ መቸም ቢሆን፣ የሰዎች ሁሉ የአንዋንዋርና የዕድገት ሂደት በዚህ መሠረተ ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው።

ከሁሉም በላይ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ "አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ትምህርት እንድናገኝበት ተጽፎአል" ይላል (ሮሜ 15:4)። ሰው ከታሪክ መማር ይችላል ማለቱ ነው። አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ የተባሉት ስለ እስራኤል ሕዝብ የተጻፉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መሆናቸው ነውና። ይህም ብቻ አይደለም። ሰው ከታሪክ መማር

አለበት ማለቱም ነው። አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ የተጻፈው መጪው ትውልድ እንዲማርበት ነውና።

በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ደጋግመን ያነሳነው የዊልስ ሪቫይቫል ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ የመሆን ዕድል የተቸረው ሪቫይቫል ነበር። ዕድሜው ግን ሁለት አመት ብቻ ሆነ። ለዚህ ሪቫይቫል መቀስቀስ እግዚአብሔር በእጅጉ የተጠቀመበት ሰው ኢቫን ሮበርትስ የተባለ የሃያ ስድስት አመት ወጣት ነው። በብዙዎች እምነት ኢቫን ለዊልስ ሪቫይቫል ጀማሪውና መሪው ብቻ አልነበረም። ለዚያ ሪቫይቫል በአጭር መቀጨትም ምክንያቱ በአብዛኛው እርሱው ነበር። ለሪቫይቫል መቀስቀስ ምክንያት የሆኑ ሰዎች ተመልሰው ለዚያው ሪቫይቫል መክሸምም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው። ለዚህ ነው ሪቫይቫልን የሚጠሙ ሁሉ ስለ ቀደሙ ሪቫይቫሎች፣ ስለ ብርቱና ስለ ደካማ ጎናቸው ማጥናት የሚገባቸው።

የአንድነታችን ሰባት አንዶች

ሪቫይቫልን ከሚያሽመደምዱት መሰናክሎች አንዱ በክርስቲያኖች መካከል የሚፈጠር መከፋፈልና መለያየት ሲሆን ከሚያራምዱትም ነገሮች ዋኛው አንድነታችው ነው። ክርስትና ቀለምንና ቋንቋን፣ አገርንና አህጉርን የሚያልፍ ነገር ነው። በዓለም ዙሪያ ዛሬ "ክርስቲያን ነኝ" የሚሉ ሰዎች ቁጥር 1.9 ቢልዮን ይገመታል። እነዚህ 4.1 ሚልዮን በሚገመቱ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያንና 32,000 በሚሆኑ ዲኖሚኔሽኖች ስር ይገኛሉ።[1] በእነዚህ ሁሉ መካከል በእውነት አንድነት ሊኖር ይችላል? ከቻለስ ያ ምን ዓይነት አንድነት ይሆናል? በቀለምና በቋንቋ፣ በዲኖሚኔሽን ሰምና በአጥቢያ ብዛት ላለመሰናከል "ክርስቲያን ነኝ" ባይ ሁሉ ለዚህ ጥያቄ ጥርት ያለ መልስ ሊኖረው ያስፈልጋል።

ክርስቲያኖችን አንድ የሚያደርጉን ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ አዲስ ኪዳን በግልጽ አስቀምጦልናል።

> በሠላም ተሳስራችሁ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በተጠራችሁ ጊዜ ለአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ። እንዲሁም አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ። ደግሞም ከሁሉ በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር፣ የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ። (ኤፌ 4:3-6)

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ክርስቲያኖች ሁሉ የጋራቸው የሆኑ ሰባት አንድ አንድ የሆኑ ነገሮች አሏቸው። እነዚህም አንድ ተስፋ፣ አንድ አካል፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት፣ አንድ ጥምቀትና አንድ አምላክ ናቸው። እነዚህ ሰባት አንዶች የሌሏቸው ሰዎች እውነተኛ ክርስቲያኖች አይደሉም። ክርስቲያኖች በእነዚህ የጋራቸው በሆኑ ሰባት አንዶች ላይ የተመሠረተውን አንድነታቸውን በትጋት እንዲጠብቁት ታዝዘዋል።

ከሰባቱ አንዶች መካከል ሦስቱ አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ አምላክ የሚሉ መሆናቸውን ልብ ይሏል። በሥስትነት ያለው የእግዚአብሔር አንድነት ጉዳይ ነው። የሥላሴ አስተምህሮ። አንድ ተስፋ የተባለው የጌታ ዳግም ምጽአት ነው። እርሱ "የተባረከው ተስፋችን" ነው (ቲቶ 2፡13)። አንድ ጥምቀት የተባለው የህፃን ወይም የአዋቂ ጥምቀት አይደለም። የውሀ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም አይደለም። አንድ ኃጢአተኛ ሰው በንስሐና በእምነት ጌታን ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚጠመቀው ጥምቀት ነው (1ኛ ቆሮ 12፡12-13፤ ገላ 3፡ 27-28)። በአካሉ ውስጥ ብልት የሚደረግበት ጥምቀት ነው።

እንግዲህ እንደዚህ አዲስ ኪዳናዊ አስተምህሮ የአንድነታችን መሠረቶች መላዕክትም፣ ማርያምም፣ አጽዋማትም፣ የውሀም ሆነ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም አይደሉም። እነዚህ ሰባት አንዶች ያሉት ሪቫይቫል ከየትም አቅጣጫ ቢነፍስ አብረነው ልንነፍስ እንችላለን። ያ የማይሆንልን ከሆነ ደግሞ አርፈን እንድንቀመጥ፣ እንዳናደናቅፈው፣ ጥንቃቄ እንድናደርግለት ይገባናል። "ከሁሉ በላይ የሆነ፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር፣ የሁሉም አባት የሆነ፣ አንድ አምላክ" በዚያ አለና።

አንድነት ማለት አንድ አይነት ማለት አይደለም

ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ አይነት ካልሆኑ በስተቀር በመካከላቸው አንድነት ሊኖር የሚችል የማይመስላቸው ሰዎች ብዙ ናቸው። እንደዚህ ዓይነቶቹም ሰዎች በአላማኞች መካከል ብቻ ሳይሆን በእኛ በአማኞቹም መካከል ሞልተዋል። ከቶውንም አላማኞቹ እንደዚህ እንዲመስላቸው ሰበብ የሰጠናቸው እኛ አማኞቹ ነን። አንዳችን የሌላችንን ትክክል አለ መሆን ስንሰብክ ሰሙን። ጎራ ለይተን እርስ በርሳችን ስንጣላ አዩን። ስንተባበር ሳይሆን ስንፎካከር ተመለከቱን።

እንደ አዲስ ኪዳን ትምህርት ከሆነ ግን በክርስቲያኖች መካከል አንድነት እንዲኖር ክርስቲያኖች ሁሉ የግድ አንድ ዓይነት መሆን የለባቸውም። ይህንን ግልጽ ከሚያደርጉት የአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ውስጥ ሦስቱን ብቻ ልጥቀስ። የመጀመሪያው ከላይ ያየነው የአንድ አካልነት ጉዳይ ነው። ያ አንድ አካል የክርስቶስ አካል ነው። ያ አንድ አካል ሁለንታዊዋ ቤተ ክርስቲያን ናት። እውነተኞች ክርስቲያኖች ሁሉ በነፍስ ወከፍ በዚያ አንድ አካል ውስጥ ያሉ ብልቶች ናቸው። ካቶሊኮች፣ ኦርቶዶክሶች፣ ወንጌላውያን ሊሆኑ ይችላሉ። ብልቶች ሁሉ ተመሳሳይ አይደሉም። በቅርጻቸው፣ በአካሉ ውስጥ ባላቸው ቦታ፣ በመጠሪያ ስማቸውና በሚሰጡት አገልግሎት አንዱ ከሌላው ይለያሉ (1ኛ ቆሮ 12፡14-26)።

ሁለተኛው በክርስቲያኖች መካከል ያለው አንድነት "የመንፈስ አንድነት" የመሆኑ ጉዳይ ነው (ኤፌ 4፡3)። ለዚህ ነው ክርስትና ቀለምንና ቋንቋን፣ አገርንና አህጉርን ያልፋል ያልኩት። ክርስትና የሚያልፈው እነዚህን ብቻ ግን አይደለም። በክርስቲያኖች መካከል ያለው አንድነት የዲኖሚኔሽን ወይም የድርጅት አንድነት አይደለም። በክርስቲያኖች መካከል አንድነት እንዲኖር የአምልኮ ሥርዓቶቻችን፣ የአስተዳደር ዘይቤዎቻችን፣ አንድ አይነት መሆን አይኖርባቸውም።

ሦስተኛው "አሰራርም ልዩ ልዩ ነው፤ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው" የሚለው አሳብ ነው (1ኛ ቆሮ 12፡6)። በመሠረቱ ይኸ ጥቅስ የሚናገረው ስለ ጸጋ ስጦታዎች ነው። ስለ ጸጋ ስጦታዎች ስናስብ አብዛኛውን ጊዜ የምናስበው የተለያዩ ስጦታዎች ከተሰጡአቸው ግለሰብ ምዕመናን ጋር አያይዘን ነው። የጸጋ ስጦታዎች ለግለሰብ ምዕመናን ብቻ ሳይሆን ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያንም እንደሚሰጡ ሞምር አድርገን ልናስብ ይገባል።

ለምሳሌ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጠንካሮች ናቸው። የሌሎች ጥንካሬ ደግሞ በጸንጠቆስጤአዊ ልምምዶች ረገድ ሊሆን ይችላል። የአንዳንዶች ብርቱ ጎን የወንጌል ስርጭት ይሆናል። የሌሎች ደግሞ ምዕመናንን ደቀ መዛሙርት በማድረግ አኳያ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች በአመራርና በአስተዳደር ከሌሎች የተሻሉ ይሆናሉ። አንዳንዶችም በሥነ ጽሑፍ፣ አንዳንዶችም በሥነ ዜማ ከሌሎች ይልቅ የተሻለ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። "ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።" "ሁሉን" ማለት የሚደረጉትን ድርጊቶች ሁሉ ማለት ነው። "በሁሉ" ማለት በአድራጊዎቹ ሁሉ ማለት ነው። አንዱ እግዚአብሔር በአብያተ ክርስቲያን ሁሉ በሚያደርጋቸው ድርጊቶች ሁሉ እርሱን እንድናደንቅባቸው፣ እኛም እንዳንደናቀፍባቸው ይገባል።

መቸም አብያተ ክርስቲያን በሁሉ ረገድ የተሟሉ ቢሆኑ ይወዳሉ። የሁልጊዜ ፍላጎታቸውና የቀን ከሌት ጥረታቸውም ይኸው ነው። መልካም ነው። ሆኖም እንደ ግለሰብ ምዕመናን ሁሉ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያንም የቱንም ያህል ቢጥሩ ሁሉ በሁሉ ረገድ ብርቱ ሊሆኑ የሚችሉ አይመስልም። ቀድሞውኑ ሲያንዳቸው እራሳቸውን በራሳቸው እንዲችሉ (self sufficient) ሳይሆን እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ አድርጎ ነው። ከአካል ብልቶች ውስጥ እራሱን በራሱ የሚችል፣ የሌሎች አገልግሎት የማያስፈልገው ብልት አለ? መርሑ ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያንም ይሠራል።

ሪቫይቫል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። መንፈስ ቅዱስም ሥራውን በነፃነት ለመሥራት የቅዱሳኑን የልብ አንድነት ይፈልጋል። ቅዱሳን በልብ አንድነት አብረው በሚሆኑበት በዚያ በረከትና ሕይወት ለዘላለም ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር እንዳዘዘ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (መዝ 133)። የሚመጣው ሪቫይቫል አብያተ ክርስቲያን በቃላቸው ብቻ ሳይሆን በአንድነታቸውም ሞምር የሚሰብኩበት ሪቫይቫል ነው የሚሆነው (ዮሐ 17:21)። አብያተ ክርስቲያንና ምዕመናን ለዚያ እራሳችንን ማዘጋጀት አለብን።

የመስቀሉ መካከለኛነት

በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ መካከለኛው ጉዳይ የክርስቶስ መስቀል ነው። እግዚአብሔር ዓለሙን የሚያድነው በክርስቶስ መስቀል ነው። እግዚአብሔር ለሰዎች የኃጢአታቸውን ስርየት የሚሰጣቸው በክርስቶስ መስቀል ነው። እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት የሚለውጠው (transform) በክርስቶስ መስቀል ነው። እግዚአብሔር ዲያብሎስን ድል የነሳው በክርስቶስ መስቀል ነው። እግዚአብሔር ሞትንና ሲዖልን የሻረው በክርስቶስ መስቀል ነው። የክርስቶስ መስቀል ማለትም የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ማለት ነው። አዲስ ኪዳን "የመስቀሉ ቃል" እያለም ይጠራዋል (1ኛ ቆሮ 1:18)።

ሞትንና ሕይወትን፣ ገሃነመ እሳትንና መንግሥተ ሰማያትን የሚለያቸው የክርስቶስ መስቀል ነው። ጨለማንና ብርሃንን፣ ኩነኔንና ጽድቅን የሚከፍላቸው የክርስቶስ መስቀል ነው። ሰማይንና ምድርን፣ ሰውንና እግዚአብሔርን ያስታረቀ የክርስቶስ መስቀል ነው። የክርስቶስ መስቀል ማለትም ወንጌል ማለት ነው (ሮሜ 1:1-4፤ 1ኛ ቆሮ 15:1-4)። ወንጌል ማለትም መልካም ወሬ፣ የምሥራች ማለት ነው።

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መልዕክታቸው የክርስቶስ መስቀል ነው (ሉቃ 24:25-27፣ 44-47)። የአዲስ ኪዳን መጻህፍትም መልዕክታቸው የክርስቶስ መስቀል ነው (1ኛ ቆሮ 1:23)። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ሪቫይቫል መልዕክቱ የክርስቶስ መስቀል ነበር። ሌሎች ሪቫይቫሎችም ሁሉ መልዕክታቸው ከክርስቶስ መስቀል የተለየ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር ሪቫይቫል የሚልከው ኃጢአተኞች የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሰምተው በማመን የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ ነው።

እራሳቸውን በሪቫይቫል ውስጥ የሚያገኙ አገልጋዮች ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱሱ ማዕከላዊ መልዕክት ለሆነው ለክርስቶስ መስቀል ታማኞች እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። ለሰዎች ሁሉ ጽድቅንና ቅድስናን፣ ሠላምንና ዕረፍትን፣ ጤናንና ብልጥግናን የሚሰጣቸው እርሱ ነው። ከዚህ ውጪ ግን የወቅቱን ኑሮ አቅጣጫ እያዩ፣ የሰዎችን የሥጋ ፍላጎት እያዳመጡ መልዕክታቸውን ቢለዋውጡ በመጀመሪያ በራሳቸው፣ ቀጥሎም በሪቫይቫሉ ላይ የእግዚአብሔርን እርግማን ያመጣሉ። "... እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክም ቢሆን እኛ ከሰበክንላችሁ የተለየ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ተብሎ ተጽፎአልና (ገላ 1:8)።

ሚዛናዊነት

በሪቫይቫል ወቅት በብዙዎች ፊት ከሚጋረጡት ፈተናዎች መካከል አንዱ የሚዛናዊነት መጥፋት ነው። የሪቫይቫል ወቅት የእግዚአብሔር ቤት በሕፃናት የሚሞላበት ወቅት ነው። ሕፃንነታቸው በመንፈሳዊው ዕድሜአቸው ነው። እንደዚያ ባለ ወቅት ቤተ ክርስቲያን ምን ልትመስል እንደምትችል ለመገመት በዕድሜአቸው ሁለት፣ ሦስትና አራት አመት የሆናቸው ብዙ ሕፃናት ያሉበት ቤት ምን እንደሚመስል ማሰብ ነው። ብዙ እንቅስቃሴ፣ ብዙ መሩዋሩዋጥ፣ ብዙ መገጫጨት፣ ብዙ መጩዋጨዋህ ይኖራል። በቤቱ ውስጥ ያሉ ዕቃዎች ሁሉ ይነካካሉ፣ ይሞከራሉ፣ ይተረማመሳሉ፣ ይሰባበራሉ። ሃይ የሚል ከጠፋ ሌላም ብዙ ጉዳት ሊደርስ ይችላል።

ምንድነው ምክንያቱ? ምክንያቱማ ሕይወት ነው። ሕይወት አለ። ጉሽ ሕይወት። ትኩስ ሕይወት። ከጥንቃቄ ጋር የተፋታ ሳይሆን ገና ያልተጋባ ሕይወት። እራሱን በዕውቀት የመምራት ብቃት ገና የሌለው ሕይወት። አብያተ ክርስቲያን በአዳዲስ ሰዎች ይጥለቀለቃሉ። ሰዎቹ ግን ገና ሕፃናት ናቸው። ሁሉን መንካት፣ ሁሉን መሞከር አለባቸው። አዲሱን ዓለማቸውን ለማወቅ ያላቸው መንገድ ያ ብቻ ነው። በዚህ መንገዳቸው ላይ አደጋ እንዳለ አያውቁም። እሳት

ማማሩን እንጂ ማሳረሩን ገና አልደረሱበትም። በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ "መጠርጠር" የተሰኘ ቃል ገና የለም።

በእነዚህ አካባቢ ጽንፈኛነት (extremism) የወቅቱ ወግ (order of the day) ይሆናል። ቃሉን ለቤተ ክርስቲያን ተጠቅመንበት አናውቅም እንጂ ይኸኛውን ጽንፈኛነት "ግራ" ጽንፈኛነት ልንለው እንችላለን። ጽንፈኛነት የግራ ብቻ ሊሆን አይችልም። የግራ ባለበት ሁሉ የቀኝ ደግሞ ሁልጊዜ አለ። የቀኝ ጽንፈኞቹ በስምንተኛው ምዕራፍ "ዕድሜ መስተዋትም መጋረጃም ነው" በሚለው ርዕስ ውስጥ "አባቶች" ያልኳቸው ናቸው። እሳቱ አሳርሮአቸው፣ እባኩም ነድፎአቸው ያውቃሉ። ለዚያ ልምምዳቸው "ተሞክሮ" የሚል ስም አውጥተውለታል። ለአዲስ ነገር "ሰፍ" አለማለት ማለት ነው። "ልጥ ጊንጥ" ሲመስል ማለት ነው።

እርግጥ ነው አባቶች ሁሉ እንደዚህ፣ ልጆችም ሁሉ እንደዚያ አይደሉም። ሚዛናዊነትን የማጣት ችግር ሁልጊዜ የዕድሜ ጉዳይ ብቻ አይደለም። ልጆች በቀኝ አባቶችም በግራ አክራሪነት ተሰልፈው የሚገኙበት አጋጣሚም አይጠፋም። ለመሆኑ ብዙ ጊዜ ሚዛናዊነት የሚታጣባቸው ጉዳዮች ምንድናቸው? አንዳንዶቹን እንጥቀሳቸው።

ቃል/ኃይል

ይህንን አንዳንዶች አስተምህሮ/ልምምድ እያሉ ይጠሩታል። ሌሎችም ቃል/መንፈስ ይሉታል። በሁለቱ መካከል ልዩነት የማይታያቸውም ይኖራሉ። ለሁሉም በክርስትና ውስጥ እነዚህ ሁለቱ ሁልጊዜ አሉ። እነዚህንም ሁለቱን በተመለከተ በምዕመናን መካከል ብዙ ጊዜ የሚዛናዊነት መጉደል ይከሰታል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት የአጵሎስና የጳውሎስ ቡድን አባላት በዚህ ረገድ ሚዛናዊነት የጎደላቸው ምዕመናን ሳይሆኑ አይቀሩም (1ኛ ቆሮ 1:12)። አጵሎስ የታወቀ አስተማሪ ነበረና (የሐዋ 18:24-28)። በማስተማሩ ከአጵሎስ ያንሳል ባይባልም ጳውሎስ በቆሮንቶስ ወንጌልን የሰበከው ". . . መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ . . ." በቃል ብቻ አልነበረምና (1ኛ ቆሮ 2:4-5)።

ቃል የምንለው በጆሮ የሚሰማውን ሲሆን ኃይል የምንለው ደግሞ በዓይን የሚታየውን ነው። ክርስትና ከመጀመሪያው ጀምሮ የተሰበከው በእነዚህ በሁለቱ በጣምራ ነው። ". . . ወንጌላችንን ያበሠርንላችሁ በቃል ብቻ ሳይሆን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ . . . ነው" (1ኛ ተሰ 1:5)። ስለ ኃይሉ የነገረን ቃሉ ነው። ነገር ግን ኃይሉ ያለ ቃሉ

ይቅርና ቃሉም ያለ ኃይሉ በቂ እንደሆነ ብናስብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የምንሆን አይመስለኝም። አገልግሎት ግን የጸጋ ሥጦታ ጉዳይ ነውና ሁሉቱንም በአካል ውስጥ እንጂ በግለሰብ ውስጥ ካላየናቸው ብለን ችክ ብንል አሁንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አንሆንም። ቃሉ ለዓለም ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ሥጦታ ሲሆን ኃይሉ ግን ቃሉን በእምነት ለተቀበሉት ብቻ የሚሰጥ ጸጋ ነው። ቃሉ ባልነገረን ኖሮ ስለ ኃይሉ ባላወቅን ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ባልተሰበከልን ኖሮ ቃሉ ወደ ሕይወታችን ባልደረሰና ሕይወታችንንም ባልለወጠ ነበር።

ሁለንታዊ/አጥቢያዊ

እንደ አዲስ ኪዳን አስተምህሮ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሁለት መልኮች አሏት። ከሁለቱም መልኮችዋ ጋር በመጀመሪያ ያስተዋወቀን ጌታ ኢየሱስ እራሱ ነው (ማቴ 16:18፤ 18:17)። የመጀመሪያው ጥቅስ የሚናገረው ስለ ሁለንታዊዋ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ሁለተኛው ጥቅስ ግን አጥቢያዊ መልኳን ነው የሚያሳየን። ሁለንታዊው መልኳ በዓለም ያሉ አማኞች ሁሉ፣ የሞቱትም ሆነ በሕይወት ያለነው በአንድነት አብረን ያለንበት ነው። አጥቢያዊው ግን በሕይወት ያለነው ብቻ በየአካባቢአችን እንደየፍላጎታችን ተደራጅተን ያለንበት ነው።

በሁለንታዊው መልኳ ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያው ድል ነስታለች። የገሃነም ደጆች አይችሉአትም፣ በአጥቢያዊው መልኳ ግን ገና በትግል ላይ ነች። አባላትዋ እርስ በርሳቸው ይበዳደላሉ። ዳኝነት ታያለች። ለአንዱ ስትፈርድለት በሌላው ላይ ትፈርድበታለች። በሁለንታዊው መልኳ "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" ተብላለች (ገላ 3:28)። በአጥቢያዊ መልኳ ግን ዘግናኝ አላት። አሠሪዎችና ሠራተኞች በውስጥዋ አሉ። ያታም አላት። አንድ ሰው ሳትሆን ብዙ ሰዎች ናት። በሁለንታዊው መልኳ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ሥፍራ ተቀምጣለች (ኤፌ 2:7)። በአጥቢያዊ መልኳ ግን ገና በምድር ላይ ወንጌልን ትሰብካለች።

ሌሎችም ልዩነቶች አሉ። በሁለንታዊው መልኳ አትታይም። በአጥቢያዊ መልኳ ግን በየነገዱና በየቋንቋው ተገልጣ አለች። ሰዎች በክርስቶስ ባመኑበት በዚያው ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ የሁለንታዊዋ አባላት ይደረጋሉ። በክርስቶስ አካል ውስጥ ይጠመቃሉ። ከዚያ ቀጥሉ በራሳቸው ውሳኔ የአጥቢያዊዋ አባላት እንዲሆኑ ይጠበቃሉ። ከዚያችኛዋ ጋር የድልዋ ተካፋዮች እንደ ተደረጉ፣ ከዚህችኛዋ ጋር ደግሞ የትግልዋ ተካፋዮች ለመሆን በፈቃዳቸው እራሳቸውን መስጠት ይገባቸዋል። በሁለንታዊዋ አለልክ ተሰበው ከአጥቢያዊዋ እንዳይቆረጡ

በአጥቢያዊዋም አለቅጥ ተወጥረው ለሁለንታዊዋ ደንታ እንዳያጡ ሊጠነቀቁ ያስፈልጋቸዋል።

የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ/የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ

ይህንን ርዕስ "የመንፈስ ቅዱስ ኃይል/የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ" ማለትም ይቻላል። ሥጦታዎቹ "የጸጋ ሥጦታዎች" እየተባሉም ይጠራሉ። በቁጥር በርካታ ናቸው[2]። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ተጠቅሰዋል። ሐያ ያህሉ ግን በሁለት ምዕራፎች ውስጥ ተሰብስበው ይገኛሉ (ሮሜ 12፤ 1ኛ ቆሮ 12)። ከሥጦታዎቹ ጥቂቶቹ (ምናልባት ከአራት የማይበልጡ) የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለሰዎች ሁሉ በሚታይ መልኩ የሚገለጥባቸው ናቸው። እንደዚያ በመሆናቸውም የአማኞችንና የአላማኞችን ትኩረት በእጅጉ ይስባሉ።

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚባለው የክርስቶስ ባህርይ ነው። በግልጽ የተጠቀሰው በገላትያ መጽሐፍ በአምስተኛው ምዕራፍ ውስጥ ቢሆንም በሌሎቹም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ውስጥ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ብዙ ብዙ ተብሎለታል። የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚያፈራው ፍሬ ነው። አማኙ እግዚአብሔርን እየታመነ፤ ሥጋውን፤ ዓለምንና ሰይጣንን እየታገለና እየጣለ፤ ከኃጢአት እየራቀና ጽድቅን እየተከተለ፤ የሚኖረው ዕለታዊ ኑሮው ነው። ፍሬ እንደ መሆኑ መጠን ቅርንጫፎች በግንዱ ላይ በሚታዩበት በዚያው ቅጽበት አብሮ ላይታይ ይችላል። እያደረ እየዋለ ግን መታየቱ ምንም ቢሆን አይቀርም።

የሥጦታና የፍሬ የእነዚህ የሁለቱ አስፈላጊነት በሁሉም ዘንድ የታመነበት ቢሆንም አንዱን ከሌላው ይልቅ የማስበለጥ አዝማሚያ ግን በብዙዎች ዘንድ ይታያል። ማን የቱን ከየቱ ይልቅ እንደሚያስበልጥ ከሰው ሰው፤ ከአካባቢም አካባቢ ሊለያይ ይችላል። አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረን ግን ለአማኙ ስጦታዎችን የሚሰጥ፤ ፍሬውንም በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚያፈራ መንፈስ ቅዱስ እራሱ ነው። በአማኙ ሕይወት ውስጥ ሁለቱም የጸጋ ሥራ ናቸው። ቢሆኑም ሁለቱም የአማኙን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃሉ - ቃሉን የማንበብ፤ ቃሉን የመታዘዝ፤ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት የመትጋት፤ ከቅዱሳን ጋር በፍቅር ላይ የተመሠረተ ህብረት የማድረግ።

ቤተ ክርስቲያን በባዙር እነዚህ ሁለቱ ደግሞ ባዙሩ በሚጓዝባቸው ሁለት ሐዲዶች ሊመሰሉ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ሁሉ

እንድታደርሰው የተሰጣትው መልዕክት አላት። ይህንን መልዕክት በተገቢው ሁኔታ ለማድረስ እነዚህን ሁለት ሐዲዶች ቆንጥጣ ረግጣ መጓዝ አለባት። በአንድ ሐዲድ ብቻ ላይ የሚጓዙ ባቡሮች ዛሬ በዓለማችን አሉ። ቤተ ክርስቲያን ግን ምን ጊዜም ቢሆን ከእነዚህ ሁለት ሐዲዶች በአንዱ ላይ ብቻ እየተጓዘች የተሰጣትውን ተልዕኮ እንደሚገባ ልታደርስ አትችልም።

የወይን ጠጅ/አቁማዳ

ስለ አዲሱ የወይን ጠጅና ስለ አሮጌው አቁማዳ የነገረን ጌታ ኢየሱስ ነው (ማቴ 9፡17)። እርሱ ባስተማረበት ይዘቱ አቁማዳ ማለት ለወይን ጠጅ መያዣነት ከለፋ የፍየል ሌጦ የተሰራ ስልቻ ነው። ንግግሩ ምሳሌአዊ ሲሆን አዲስ የወይን ጠጅ ያለው የአዲስ ኪዳን ትምህርት፤ አሮጌው አቁማዳ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው። የብሉይ ኪዳኑ ሥርዓት የአዲስ ኪዳኑን ትምህርት ለማስተናገድ ችሎታ አልነበረውም። ለዚህ ነው "አሮጌ" የተባለው።

የጌታ አባባል ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ላለነው ለእኛም ቢሆን ትምህርት ሰጪ ነው። የወይን ጠጁ በክርስቶስ ያለው አዲስ ሕይወት ነው። አቁማዳው የቤተ ክርስቲያን የአደረጃጀት፤ የአወቃቀር፤ የአስተዳደር ዘይቤ ነው ልንል እንችላለን። የሁለቱ ግንኙነት፤ በተለይም በሪቫይቫል ወቅት፤ ብዙ ጊዜ ይሻክራል። ከዚህም የተነሳ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ ብዙ አቁማዳዎች ፈንድተዋል። ብዙ የወይን ጠጅም ፈስሷል። ብዙ ሪቫይቫሉችም ያለ ቀሪ ቀርተዋል።

የቆረፈዱ አቁማዳዎች እንደገና ሊለሰልሱ ይችላሉ። የማይለሰልሱ ዓይነት ከሆኑም በሌሎች አቁማዳዎች ሊተኩ ይችላሉ። የወይን ጠጁ ግን በምንም ዓይነት ቢሆን መፍሰስ የለበትም። እንዳይፈስም ሁልጊዜ አቁማዳ ያስፈልገዋል። አዲስ አቁማዳ ሳያዘጋጁ አሮጌውን አውጥቶ መጣል የወይን ጠጁን ያለ አቁማዳ ያስቀረዋል። የሪቫይቫልን መከር የምንከትበት ጎተራ አይኖረንም ማለት ነው። የሪቫይቫልን ፍሬ ሳናፍስ እንቀራለን ማለት ነው። የወይን ጠጁ ይፈስሳል፤ ፈስሶም ይቀራል ማለት ነው።

በጌታ ፊት/በሰው ፊት

"... ዓላማችን በጌታ ፊት ብቻ ሳይሆን በሰዎችም ፊት መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ ነው" (2ኛ ቆሮ 8፡21)። ሐዋርያው

ጳውሎስ ይህንን የሚጽፈው እርሱና አብረውት ያሉት ወንድሞች ለዕርዳታ የሰበሰቡትን ገንዘብ እንዴት እንደሚያስተዳድሩ ለመግለጽ ነው። ይሁን እንጂ በገንዘብ ጉዳይ ላይ ብቻ ላይሆን በሌሎችም ጉዳዮች ላይ በዚሁ መርህ እንደሚመሩ ከመልዕክቶቹ በስፋት መመልከት እንችላለን።

አንዳንድ አገልጋዮች "ጌታን ደስ ይበለው እንጂ ስለ ሰው ግድ የለኝም" ሲሉ ይደመጣሉ። አዎን፣ ጌታን ደስ የሚያሰኙ፣ ሰው ግን ደስ የማይሰኝባቸው ነገሮች ይኖራሉ። እነዚህ አገልጋዮች እንደዚህ የሚሉት እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች በተመለከተ ከሆነ ልክ ናቸው። እንዲያው ስለ ማንኛውም ነገር ከሆነ ግን ልክ አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያን "... በማያምኑ ሰዎች ዘንድ መልካም ስም እንዲኖረው ያስፈልጋል" ይላል (1ኛ ጢሞ 3፡7)። በማያምኑ ሰዎች ዘንድ መልካም ስም እንዲኖረን የሚፈለግብን ከሆነ በሚያምኑ ሰዎችማ ዘንድ እንዴት ነዋ?

ሚኒስትሪዎች ምንድናቸው?

ስለ "ሪቫይቫልና መንደርደሪያዎቹ" በሚናገረው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ሚኒስትሪዎች ማንሳት ለምን ያስፈልጋል? ሚኒስትሪዎች ለሪቫይቫል መንደርደሪያም፣ መሰናከያም ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። መሰናከያ የሚሆኑት መሰናከያ ለመሆን ፈልገው ሳይሆን ካለማወቅ የተነሳ ስለሚሆን ነው። መንደርደሪያ የሆኑትም ከሆኑት የተሻለ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። ይኸ እየመጣ ያለ ሪቫይቫል በእግዚአብሔር በኩል ብዙ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎበታል ብያለሁ። በሰውም በኩል ብዙ ዋጋ ተከፍሎበታል። ስለዚህም ሁላችንም የሚጠበቅብንን ዓውቀን እራሳችንን እንድናዘጋጅለት ነው።

መንፈሳዊ መነቃቃት (ሪቫይቫል) መደበኛ መውረጃ እንዳለው ወንዝ አይደለም። በሚመጣበት ጊዜ በማናቸውም በተመቸው ቦታ ሁሉ ሰብሮ እንደሚፈስሰው ጎርፍ ነው። ከጎርፍ የሚለይበት ነገር ቢኖር የውሀ ልክ የሌለው መሆኑ ነው። ግለትም ወደ ዝቅታና ወደ ከፍታ ሁሉ የሚፈስስ መሆኑ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልገደብና አልገታ የሚለው፣ ወደ ተለያዩ ማህበራዊ ዘርፎች የሚዘልቀው በዚህ ምክንያት ነው። ከአስራ ስድስተኛው ምዕት አመት ማብቂያ ጀምሮ በግልጽ እየታየ የመጣውም ይኸው ነበረ።

ወንጌልን ወደ ዓለም ሁሉ የማድረሱ ጉዳይ አብያተ ክርስቲያን በተለመደው አደረጃጀታቸውና አሠራራቸው ሊወጡት የሚችሉት ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህም የሚሰጡን ማህበራት በአውሮፓና በአሜሪካ

መደራጀት ጀመሩ። በጣም ጥቂቶቹ እና የተቋቋሙባቸው አመታት እነሆ፦

ዳች ሚስዮን	1602
አንግሊካን ሚስዮን	1649
ዴኒሽ-ሐሌ ሚስዮን	1705
ሞራቭያን ሚስዮን	1732
ባፕቲስት ሚስዮናዊ ማህበር	1792
የሎንዶን ሚስዮናዊ ማህበር	1795
የቤተክርስቲያን ሚስዮናዊ ማህበር	1799

ወንጌል የግለሰብንና የማህበረሰብን ሕይወትና አንዋንዋር ለበጎ ይለውጣል። የሚሠራጭበት መንገድ ከአንድ በላይ ነው። ከግለሰብም ሆነ ከማህበረሰብ ከሁለቱም ሚፍ መኖት ይቻላል። ለዚህ ሁሉ ግን አብያተ ክርስቲያኑ የሰለጠኑ መሪዎች ያስፈልጓቸዋል። መንግሥታዊና ሕዝባዊ የሆኑትም ተቅዋማት እግዚአብሔርን የሚያውቁ፣ ከቅዱስ ቃሉ ጋር በደንብ የሚተዋወቁ፣ በአዕምሮና በመንፈስ የዘመኑን ተግዳሮት ለመቋቋም የሚበቁ መሪዎች ያስፈልጓቸዋል። በዚህ ዓለማ ነበር ቀጥሎ ስማቸው የተጠቀሰው በጣም ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች በጊዜው የተመሠረቱት፦

ሐርቫርድ	1636
ዬል	1701
ፕሪንስተን	1746
ዊተን	1860

እነዚህ በየአገሩ ከሚከፈቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችና ሴሚናሪዎች ሌላ ናቸው። ይህ ብቻም አልነበረም። ቃለ እግዚአብሔርን በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጎምንና ማሠራጨትን፤ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሉችን በወንጌል መድረስንና ማለደግን ዓላማቸው አድርገው የተነሱ ማኅበሮችም ነበሩ። የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፦

ብሪቲሽ ኤንድ ፎረን ባይብል ሶሳይቲ	1804
አሜሪካን ባይብል ሶሳይቲ	1817
ናሽናል ባይብል ሶሳይቲ አፍ ስኮትላንድ	1861
ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር	1844
ወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማህበር	1851
ሳልቬሽን አርሚ	1865
የቃለ እግዚአብሔር አንባብያን ማህበር	1869

በዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ፣ በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የተቋቋሙት ሚኒስትሪዎች ለቁጥር ያታክታሉ። (በዚያ አገር ብዙ ሚኒስትሪዎች የሚመሠረቱበት ዋና ምክንያት የመንግሥቱ የግብርና የቀረጥ አሰባሰብ ፖሊሲ ለሚኒስትሪዎች ገንዘብ መለገስን

የሚያበረታታ በመሆኑ ነው። በአገራችን የፖለቲካ ሥርዓቱ ስለሚፈቅድ ነው።) አገልግሎታቸው በአገራችን ከሚታወቀው መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፦

ወጣት ለክርስቶስ	1943
ቢሊይ ግርሃም ኤቫንጀሊስቲክ አሶስዬሽን	1950
ካምፐስ ክሩሲድ ፎር ክራይስት (በአገራችን ታላቁ ተልዕኮ)	1951
ዎርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል	1951

እነዚህ ሁሉ ሚኒስትሪዎች ናቸው። አንዳንዶቹን አሁን ሚኒስትሪ ለማለት ቢከብደንም እንኳን በተጀመሩበት ጊዜ ሚኒስትሪዎች ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን አጋዥ ድርጅቶች እንላቸዋለን። ከእግዚአብሔር በሆነ ራዕይ፣ በቅጡ በተጠና አሠራርና እንዲሁም በብዙ ጸሎትና ምልጃ ነበር የተመሠረቱት። ስለሆነም በአንድ አገር ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ለብዙ ጎጢአተኞች መዳንና ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት፣ ለብዙ አብያተ ክርስቲያን መመሥረትና ማደግ፣ ያበረከቱት ድርሻ አንድ፣ ሁለት፣ ተብሎ ተቆጥሮ የሚዘለት አይደለም።

የሚኒስትሪዎች ሁሉ ታሪክ ግን ከላይ እንደተባለው ዓይነት አይደለም። አንዳች ሳይፈይዱ፣ መሥራቾቻቸውን ጎልተዋቸው ወደ አለመኖር የሄዱ ብዙዎች ናቸው። በኖሩባቸው ጥቂት አመታትም ቢሆን አብያተ ክርስቲያንን ሲያግዙ ሳይሆን ሲገዘግዙ፣ ሲያንፁ ሳይሆን ሲያፈርሱ የኖሩ ጥቂቶች አይደሉም። በአለማወቅ ካልሆነ በስተቀር ይህ በአገራችን እንዲደገም የሚፈልግ እንደሌለ ተስፋ እናድርግ። የማይደገመው ግን ምን ብናደርግ ወይም ምን ባናደርግ ነው? ጥቂት ሐሳቦችን ልሰንዝር።

በመጀመሪያ ሚኒስትሪ ለመጀመር የሚፈልጉ ሁሉ ስለ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር አጀንዳ በአደራ የተሰጠው ለእስራኤል ነበር። እግዚአብሔርም አጀንዳውን የሚተገብረው ከእስራኤል ጋር በመሆንና በእስራኤል አማካኝነት ነበር። በአዲስ ኪዳን ዘመን እስራኤል በቤተ ክርስቲያን ተተክታለች። ቤተ ክርስቲያንም ይህን ተልዕኮዋን (አደራዋን) የምትወጣው በሁለንታዊው ሳይሆን በአጥቢያዊው መልኳ ነው።

ከአራቱ ወንጌላትና ምናልባትም ከሐዋርያት ሥራ በስተቀር ሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የተጻፉት ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ነው። በግለሰቦች ስም የተጻፉትም ቢሆኑ በጊዜው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በኃላፊነት ቦታ ላይ ሆነው በማገልገል ላይ ለነበሩ ግለሰቦች ነው የተጻፉት። ስለሆነም ሚኒስትሪዎች በምንም መልኩ

ቢሆን ከአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ጋር የሚተባበሩ እንጂ የሚፎካከሩ ሊሆኑ እንደማይገባቸው መገንዘብ አለባቸው። አጥቢያ አብያተ ክርስቲያኑ ምንም ዓይነት ድካም ቢኖርባቸው በሚኒስትሪዎች አይተኩም።

ሁለተኛው አሳብ ከመጀመሪያው አሳብ የሚመነጭ ነው። በመጀመሪያው አሳብ ላይ ትክክለኛ አቋም የሌለው ሰው ወደ ሁለተኛው ሊሸጋገር አይችልም። ሚኒስትሪ ለመጀመር የሚፈልጉ ሰዎች ምንም ዓይነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከማድረጋቸው በፊት ራዕያቸውን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይግለጹላቸው። እንዴት በተግባር ሊተረጉሙት እንደሚፈልጉም ይንገሩአቸው። የምክርና የጸሎት እገዛ ይጠይቋቸው። ምናልባት የታሰበው አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን በኩል በተሻለ ሁኔታ ይከናወን ይሆናል። ምናልባት ራእዩ ከእግዚአብሔር አይደለም ይሆናል። ምናልባትም ራእዩ ከእግዚአብሔር ሆኖ በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ ግን ገና ይሆን ይሆናል።

ከእግዚአብሔር ራእይ ተቀብለናል የሚሉ ሰዎች ራእያቸውን በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለማስፈተሽ መፍራት የለባቸውም። ነገሩ ከእግዚአብሔር ከሆነ፣ ለተፈፃሚነቱ እርሱ እራሱ ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል። የቤተ ክርስቲያናቸውን መሪዎች ድጋፍና ባርኮት ሳያገኙ ግን አንዳች እርምጃ ባይወስዱ መልካም ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሚኒስትሪ ለመጀመር የሚፈልጉ አባሎቻቸውን አነጋግረው፣ አብረዋቸውም ጸልየው፣ ነገሩ ጤናማ ሆኖ ካገኙት ለሰዎቹ ቀኝ እጃቸውን ለመስጠት መፍራት የለባቸውም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሚኒስትሪዎች የተጻፈ ነገር መቸም አናገኝም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ነገር የሌለው ስለ ሚኒስትሪዎች ብቻም አይደለም። ስለ ሚስዮናዊ ማህበሮችም የተጻፈ ነገር የለም። ስለ ዲኖሚኔሽኖችም የተጻፈ ነገር የለም። ስለ ምስክር ቡድን፣ ስለ ድራማ ክበብም እንዲሁ የተጻፈ ነገር የለም። እነዚህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በሆነ በሆነ ወቅትና በሆነ ምክንያት የተፈጠሩ ክስተቶች ናቸው። አብያተ ክርስቲያንም በእነዚህ ሁሉ በእጅጉ ተጠቅመውባቸዋል። ስለዚህ ለወንጌል ስርጭትና ለምዕመናን ዕድገት እስከጠቀሙ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያንን ሽክም እስከ አቃለሉ ድረስ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን የሚያከብሩ እስከ ሆኑ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ባርኮቷን ባትነፍጋቸው መልካም ይሆናል።

ሦስተኛው ሚኒስትሪ መጀመር የሚፈልጉ ሰዎች መገንዘብ የሚገባቸው እግዚአብሔር በምድር ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን የሰጠው ለቤተ ክርስቲያን መሆኑን ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የክርስቶስ አካል ናት። የክርስቶስ አምባሳደርም ናት። ሚኒስትሪዎች ቦርዶች

ይኖሩአቸዋል። የብዙዎቹ ቦርዶች የአማካሪዎች ቦርዶች ናቸው። ቦርዶቹ የዳይሬክተሮች ቢሆኑም እንኳን ሥልጣናቸው ድርጅታዊ ሥልጣን ብቻ ነው። ሚኒስትሪዎችና በሥራቸው ያሉ ምዕመናን ግን ለራሳቸው ጥንቃቄና ጥበቃ ሲሉ በድርጅታዊ ሥልጣን ስር ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሥልጣንም ስር ሊሆኑ ያስፈልጋቸዋል።

አራተኛውና የመጨረሻው አሳብ ሚኒስትሪዎች የሚጀመሩት ጀማሪዎቻቸው ከተለያዩ ምንጮች ገንዘብ ስለተቸሩ ወይም ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር መግባባት ስለተቸገሩ መሆን የለበትም። ሚኒስትሪ አገልግሎት ነው። መመሥረትም ያለበት ከቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ለሚሸሹ ወይም መተዳደሪያ ለሚሹ ሰዎች ሽፋን ለመስጠት ሳይሆን በተፈተነ ጥሪ፣ በጠራ ራእይና በመለኮታዊ ምሪት ነው።

ስኬታማነት መለኪያው ምንድነው?

ስኬታማ (successfull) የሚባል ሰው ምን የሆነለት ሰው ነው? ስኬታማ መሆን የሰው ሁሉ ፍላጎት ስለሆነ እንደ እግዚአብሔር ቃል አንድን ሰው ስኬታማ የሚያሰኙት ነገሮች ምን እንደሆኑ ማወቁ ለሪቫይቫል በመንደርደሪያነት ሊያገለግል ይችላል። ስለ "ሪቫይቫልና መሰናክሎቹ" በተናገርኩበት ምዕራፍ ውስጥ ስለ "ሰይጣናዊ ሳንኮች" አንስቻለሁ። ሪቫይቫልን የሚያደፈርሱት ግን ሰይጣናዊ ሳንኮች ብቻ ሳይሆኑ ሥጋዊ ሳንኮችም ጭምር ናቸው። ሰይጣን በአማኝ ሰው ሥጋዊነት በብዙ ስለሚጠቀም የሁለቱ ሳንኮች አንድነትና ልዩነት ብዙ ጊዜ በውል ላይታወቀን ይችላል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ለነበረው የችግሮች ክምችት ዋነኛው ምክንያት የምዕመናኑ ሥጋዊነት እንደነበረ ይታወቃል (1ኛ ቆሮ 3፡1-4)።

እና ስኬት ምንድነው? ይህንን ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አንጻር ለመመለስ ነገሩን ከሁለት አቅጣጫዎች መመልከት ያስፈልጋል- ከዓለማዊ ሰው አቅጣጫና ከአማኝ ሰው አቅጣጫ። ከዓለማዊ ሰው አቅጣጫ ስኬት ምንድነው? ጌታ ኢየሱስ ስለ አንድ እርሻው ብዙ ሰብል ስለያዘለት ሐብታም ሰው በምሳሌ ተናገረ (ሉቃ 12፡16-21)። ሰውየው ለራሱ ". . . ለብዙ አመት የሚበቃህ ብዙ ሀብት አለህ . . .ብላ፣ ጠጣ፣ ደስ ይበልህ አለዋለሁ" ይላል። እግዚአብሔር ግን "አንተ ሞኝ!! ዛሬ በዚህ ሌሊት ነፍስህ ከአንተ ትወሰዳለች . . ." ይለዋል።

በሰው መለኪያ ይኸ ሐብታም ሰው ያለ ጥርጥር የተሳካለት ሰው ነው። በእግዚአብሔር መለኪያ ግን ሞኝ ሰው እንደሆነ ነው ከምሳሌው የምናስተውለው። የዚህ ሰው ሞኝነት እምኑ ላይ ነው? ባለጠግነቱ በሰው ፊት ብቻ ስለ ነበረ፣ በእግዚአብሔር ፊት ግን ደሀ ስለ ነበረ

ነው። ጌታ እንዳስተማረን ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምንም አይጠቅመውም (ማቴ 16፡26)።

በመሠረቱ ለማንም ሰው ቢሆን ዓለሙን ሁሉ ማትረፍ አይቻለውም። ጌታ ግን የሚለው ቢቻለውም ኖሮ እንኳን ነፍሱንም አብሮ ካላተረፋት በስተቀር ምንም አይጠቅመውም ነው። ጥቅሱ የሚናገረው ስለ ሰው ነፍስ ክቡርነት ነው። ዓለሙ በሙሉ ለአንድ ሰው ነፍስ ተመጣጣኝ ዋጋ ሊሆን ስለ አለመቻሉ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ጌታ ስለ ነፍላችን ነፍሱን የሰጠው። በጌታ በራሱ ነፍስ ካልሆነ በስተቀር የሰው ነፍስ በሌላ በምንም ነገር ስለማትገዛ።

ስለዚህ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ዓለማዊ ሰው ስኬታማ ሰው አይደለም። ብዙ ነገሮች ጎድለውበት እየኖረ ይቅርና ዓለሙን በሙሉ አትርፎ ቢኖርም እንኳን የተሳካለት ሰው አይደለም። ምክንያቱም ነፍሱን ከስሮአል። ለአንድ አመት ብቻ ከብሮ ለሃምሳ ዓመት ሙሉ ግን ከስሮ የኖረን ነጋዴ ማንም "ስኬታማ ነው" አይለውም። በሥጋው ከብሮ በነፍሱ ግን ከስሮ የቀረ ሰው እንደዚያ ማለት ነው። ለአርባ ወይም ለሃምሳ ዓመት ከብሮ ለዘላለም ግን ከስሮ የቀረውን ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ስኬታማ አይለውም።

አሁን እኛን የሚያሳስበን ግን ያ አይደለም። ከሚያምን ሰው አቅጣጫ ስኬት ምንድነው? የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከሆነ ሰው አቅጣጫ ስኬታማነት ምንድነው? ለሪቫይቫል በመንደርደሪያነት ሊያገለግለን የሚችለው ለጥያቄው በተለይ ከዚህ አቅጣጫ የምንሰጠው ምላሽ ነው።

መብትን መቀዳጀት አይደለም፣ ግዴታን መወጣት ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ስለ ግዴታቸው እንጂ ስለ መብታቸው የሚላቸው አንድም ነገር እንደሌለው ልብ አድርገዋል? ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲታዘዙ (ቆላ 3፡18)፣ ባሎችም ሚስቶቻቸውን እንዲወድዱአቸው (ቆላ 3፡19) ይነግራቸዋል። ልጆች ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙ (ቆላ 3፡20)፣ ወላጆችም ልጆቻቸውን እንዳያስመርሯቸው (ቆላ 3፡21) ይመክራቸዋል። ሠራተኞች ለአሠሪዎቻቸው እንዲታዘዙ (ቆላ 3፡22)፣ አሠሪዎችም ሠራተኞቻቸውን በቅንነት እና በእኩልነት እንዲያስተዳድሩአቸው (ቆላ 4፡1) ያስታውቃቸዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምዕመናቸውን በምሳሌነት እንዲመሩአቸው (1ኛ ጴጥ 5፡1-4)፣ ምዕመናን

ለመሪዎቻቸው ሊታዘዙ (1ኛ ጴጥ 5:5)፣ ዜጎችም ለመንግሥታቸው ሊገዙ እንደሚገባቸው (ሮሜ 13:1) ያስቀምጥላቸዋል።

ሌላው ወገን መብታችንን እንዲጠብቅልን መጠየቃችንን ትተን እያንዳንዳችን የየራሳችንን ግዴታ ብቻ ብንወጣ የሁሉ መብት የተጠበቀ ይሆናል። በተግባር የሚተረጉሙት በቁጥር በቂ ሰዎች ቢገኙ ኖሮ የሰዎች ሁሉ እኩልነትና መብት ወደ ሰፈነበት ማህበረሰብ ለመሸጋገር ይኸ አቋራጩ ጎዳና ይሆን እንደ ነበረ የሚያጠያይቅ አይመስልም። ከዚህ አንፃር ስኬታማው አማኝ፣ ወይም ስኬታማው አገልጋይ ማነው? ያለ ጥርጥር ግዴታውን የተወጣው ነው።

ታዋቂነት አይደለም፣ ታማኝነት ነው

ጌታን እንድናገለግልበት ለሁላችንም የተሰጠን ነገር አለ። መክሊትም አልነው ወይም ምናን ወይም የጸጋ ሥጦታ ለሁላችንም የተሰጠን ነገር አለ። ሰጪው ለማን፣ ምን፣ በምን መጠን እንደሰጠ ያውቃል። ሂሳብ በሚወራረድበት ጊዜ ባለ አንዱ የባለ ሁለቱን ያህል፣ ባለ ሁለቱም የባለ አምስቱን ያህል እንዲያወራርዱ አይጠየቁም። በተሰጣቸው ሥጦታ ሠርተውበት ላገኛቸው አገልጋዮቹ ሁሉ የተናገረው “. . . አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፣ በጥቂቱ ታምነሃል፣ በብዙ እሾምሃለሁ . . .” የሚል ተመሳሳይ ቃል ነው።

በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ፉክክር ስፍራ የለውም። ከማን፣ በምን ለመብለጥ ነው ፉክክሩ? ማንኛችንም ብንሆን ከተሰጠን አልፈንና አስበልጠን ማገልገል እንደሆነ አይቻለንም። ለዚህ ነው ጌታ “. . . እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፦ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፣ ልናደርግ የሚገባንን አድርገናል በሉ” ያለው (ሉቃ 17:10)። ይልቅዬ ሊያሳስበን የሚገባው የታዘዝኩትን ሁሉ አድርጌ እሆን ወይ? የሚለው ነው። በበኩሌ የመጀመሪያዎቹን ሐዋርያት ጨምሮ የታዘዘውን ሁሉ ያደረገ አገልጋይ ሊኖር መቻሉን በጣም አድርጌ እጠራጠራለሁ። እንዴት ሊኖር ይችላል? ይኖራል ከተባለም ደግሞ ያደረገው ሊያደርገው የሚገባውን ብቻ ነው።

ከሥጋ ባህርያት አንዱ ታዋቂነትን መፈለግ ነው። ታዋቂነትን መፈለግ እራሳችንን ከሌሎች ጋር ወደ ማወዳደርና ከሌሎች ጋር ወደ መፎካከር ያደርሰናል። ዓለማውያን ሳለን ከሌሎች ጋር መወዳደሪያዎቻችንና መፎካከሪያዎቻችን ወገንና ሥልጣን፣ ዕውቀትና ሐብት፣ ውበትና ስኬታማነት፣ እና የመሳሰሉት ነበሩ። አማኞች በተለይም ደግሞ አገልጋዮች ስንሆን እርስ በርስ መወዳደሪያዎቻችንና መፎካከሪያዎቻችን መንፈሳዊ ነገሮች ይሆናሉ። የተሰጡን የጸጋ

ሥጦታዎች፣ የምናገለግልባቸው መድረኮች፣ የጸሎት ሕይወቱ፣ የቃለ እግዚአብሔር ዕውቀቱ መወዳደሪያና መፎካከሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። ለእግዚአብሔር አገልግሎት የምንሰጠው የገንዘብ መጠን፣ የምንሮጠው ሩጫ፣ የምንቀበለው መከራ፣ የምንከፍለውም ዋጋ ሁሉ መወዳደሪያና መፎካከሪያ ሊሆኑን ይችላሉ።

ነፍሳችን እንጂ ሥጋችን ገና እንዳልተቤዠ መዘንጋት የለብንም። ታዋቂነት መፈለግ ስር የሰደደ፣ ከሥጋም ጋር የተዋሐደ ነገር ነው። አፈር የሆነው ይኸ ሥጋችን ሲታጠብ ቢኖር ሊጠራ አለመቻሉ የሚያስገርም አይደለም። አንድ አማኝና አገልጋይ፣ በሆነ ነገር፣ ከሌላ አንድ አማኝና አገልጋይ እንደሚሻል ሲመስለው ያን ጊዜ “. . . በትህትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቁጠሩ . . .” የሚለውን አምላካዊ ቃል ይተላለፋል (ፊል 2:3)። “ትዕቢት” በተባለውና ከኃጢአት ሁሉ በከፋው ኃጢአት ይወጋል።

ትዕቢተኛ ሰው ከሌሎች ጋር አብሮ ማገልገል አይሆንለትም። የራሱን አሳብ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የሌሎችን አሳብ ማስተናገድ ይከብደዋል። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች መገዛት ይቸግረዋል። እርሱ ራሱ መሪ በማይሆንበት አገልግሎት ውስጥ አይገኝም። እግዚአብሔር ደግሞ “ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል” (ምሳ 3:34፤ ያዕ 4:6፤ 1ኛ ጴጥ 5:5)። በሪቫይቫል ጊዜ እንደዚህ ያለ አገልጋይ ሆነን እንዳንገኝ በቅድሚያ የበኩላችንን ውሳኔ ማድረግ፣ ትህትናን መለማመድ፣ የእግዚአብሔርንም እገዛ መለመን ይገባናል። ለራሳችንና ለሪቫይቫሉ ስንል። መንደርደሪያ እንጂ መደናቀፊያ እንዳንሆን።

ማፍረስ አይደለም፣ ማነጽ ነው

የሪቫይቫል ጊዜ ብዙ ሰዎች አገልጋዮች እየሆኑ የሚሉበት ነው። ሁሉም የሚያገለግሉባቸው የተለያዩ የጸጋ ሥጦታዎች ይኖሩአቸዋል። የሚያገለግሉባቸው የጸጋ ስጦታዎች ያሏቸው ሁሉ ግን የአዲስ ኪዳኑን የአገልግሎት መርሆዎች በበቂ ሁኔታ የተገነዘቡ ላይሆኑ ይችላሉ። እንዳልተገነዘቡ ከቀሩ ደግሞ ውሉ አድሮ በራሳቸውና በሪቫይቫሉ ላይ ችግር ማስከተላቸው አይቀርም። አዲስ ኪዳናዊ ከሆኑ የአገልግሎት መርሆዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ራሱ አገልግሎት ሲናገር ይህንን በጣም ግልጽ ያደርገዋል።

> ጌታ ስለ ሰጠን ሥልጣን በጣም ብመካም አላፍርበትም። ምክንያቱም ይህ ሥልጣን የተሰጠን እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለም (2ኛ ቆሮ 10:8)።

ጳውሎስ የሚጽፈው በብዙ ቁጥር ነው። እዚህም ላይ የሚናገረው ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ጋር ለነበሩትም ጭምር ስለ ተሰጣቸው መንፈሳዊ ሥልጣን ነው። የሚቀጥለው ግን ስለራሱ ብቻ ነው።

> . . . በዚህ ዓይነት ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ ጌታ በሰጠኝ ሥልጣን አላስጨንቃችሁም፤ ምክንያቱም ጌታ ሥልጣን የሰጠኝ እናንተን ለማነጽ እንጂ እናንተን ለማፍረስ አይደለም (2ኛ ቆሮ 13፡10)።

ለመሆኑ የጳውሎስ ሐዋርያነት ምድቡ ከአስራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ነው? ወይስ ከቤተ ክርስቲያን ሐዋርያት? በይሁዳ ምትክ አስራ ሁለተኛ ሐዋርያ እንዲሆን አስራ አንዱ ሐዋርያት በዕጣ የመረጡት ሰው ማትያስ መሆኑ ይታወቃል (የሐዋ 1፡21-26)። ብዙ ሰዎች ግን አስራ ሁለተኛው ሐዋርያ እንዲሆን በጌታ የተመረጠው ሰው ማትያስ ሳይሆን ጳውሎስ ነው ይላሉ። ስለ ማትያስ አለመመረጥም ሆነ ስለ ጳውሎስ መመረጥ የሚደረድሩአቸው ጠንካራ ማስረጃዎች አሏቸው። እነዚያን ማስረጃዎች መመልከት ለእኛ እዚህ ቦታ ላይ አስፈላጊነት የለውም። ሆኖም ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ የጳውሎስ ሥልጣን ለበጉ ሐዋርያት የተሰጠው ሥልጣን ነው ማለት ነው። ያም ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛው መንፈሳዊ ሥልጣን ነው። ይህ ከፍተኛ መንፈሳዊ ሥልጣን የሚሰጠው አጥቢያ አብያተ ክርስቲያንን ለማፍረስ ሳይሆን ለማነጽ እንደሆነ ነው ጳውሎስ የሚነግረን።

ሐዋርያው የመንፈስ ቅዱስን ሥጦታ ለሚፈልጉ ምዕመናን ሲጽፍ “. . . መንፈሳዊ ሥጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ” ይላል (1ኛ ቆሮ 14፡12)። ደግሞም “. . . ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ” ይላል (ኤፌ 4፡29)። “ክፉ ቃል” የሚለው የሚያፈርሰውን ንግግር ነው። ይህም ብቻ አይደለም። “. . . ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ያውም እናንተ ናችሁ” ይላል (1ኛ ቆሮ 3፡17)። እዚህ ቦታ ላይ “ቤተ መቅደስ” የሚለው ግለሰብ ምዕመናንን ሳይሆን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዋን እንደሆነ ግልጽ ነው።

ከእነዚህ ጥቅሶች በግልጽ የምንረዳው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ከላይ ከሐዋርያው ሥልጣን አንስቶ እስከ ታች እስከ ተራው ምዕመን ተራ ቃል ድረስ የማፍረስ ሳይሆን የማነጽ አገልግሎት መሆኑን ነው። በመሠረቱ የሰውን ሕይወት ማፍረስ መንፈሳዊ ሥልጣንም ሆነ መንፈሳዊ ሥጦታ አይጠይቅም። ከዚህ በመነሳት አንዳንድ ጥያቄዎች እስቲ እንጠይቅ፦ በሆነ ምክንያት አንዲትን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መገንጠል ወይም ማስገንጠል ማነጽ ነው ወይስ ማፍረስ? በአጥቢያ

አብያተ ክርስቲያን፣ በአገልጋዮቻቸውና በምዕመናኖቻቸው መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ማሻከር ማነጽ ነው ወይስ ማፍረስ? በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓት እርምጃ የተወሰደበትን አገልጋይ የቅጣቱን ጊዜ ሳይፈጽም፣ ወደ ንስሐ ሳይደርስ፣ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ያለውን ችግር ሳይፈታ፣ ቤተ ክርስቲያኑም ሳትፈቅድ አገልጋይ አድርጎ መውሰድ ያንን አገልጋይ ማነጽ ነው ወይስ ማፍረስ? ምዕመናንን ከአንድ አጥቢያ ወደ ሌላ ማፍለስ ማነጽ ነው ወይስ ማፍረስ?

ምዕመናን ከአንድ አጥቢያ ለቅቀው ወደ ሌላ አጥቢያ ሄዱ እንጂ ከእግዚአብሔር መንግሥት ለቅቀው አልሄዱም ሊባል ይችላል። ችግሩ ግን ያ አይደለም። እስቲ እንደዚህ እንየው። የአንድ አገልጋይ ፍላጎት መሆን ያለበት ምዕመናን ሁሉ በያሉበት ደህና እንዲሆኑ ነው ወይስ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ነው? ማንም ጤኛ ሰው ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ይታወቃል። ሆኖም ማረጋገጫው ቃል ሳይሆን ተግባር ነው። የአገልጋዩ ፍላጎት የምዕመናኑ ደህንነት ብቻ ከሆነ ለዚያ የሚያስፈልጋቸውን ጸጋ በያሉበት እያሉ ለምን አያካፍላቸውም? በእርሱ ጸጋ ለመገልገል ካሉበት እንዲወጡና እርሱ ወዳለበት እንዲመጡ ለምን ይጠይቃቸዋል? ነገ ደግሞ ከእርሱ ወደ ሌላ ይሄዳሉ። እና መጨረሻው የት ነው? ትርፉስ ምንድነው?

እርሱም አንድ ብልት ብቻ እንጂ አካል አይደለም። ምዕመናኑ ለደህንነታቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ከእርሱ ዘንድ ብቻ ሊያገኙ አለመቻላቸው እንደሆነ የታወቀ ነው። ምዕመናኑ በያሉበት ሆነው በሁሉ ባለው ጸጋ መገልገል እንዲችሉ ሁኔታዎች ለምን አይመቻቹላቸውም? እነዚህ ምዕመናን እኮ ለብዙ አመታት የደከሙባቸው አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን አሉ። የመንፈስ ልጆቻቸው ናቸው። ለደህንነታቸው ደንታ የሌለው ሰው ከሆነ ቦታ ትናንትና መጥቶ፣ በሆነ ደካማ ጎናቸው በኩል ተጠግቶ፣ የደከሙበትን ሁሉ ሲያፈርሰው ምን ይሰማቸዋል? ቢያንስ በዚያ ሰው ላይ ልባቸው ያዝናል። ግንኙነታቸው ይሻክራል። ያም መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ በነፃነት እንዳይንቀሳቀስ ሊከለክለው ይችላል። ሪቫይቫል ይጨነግፋል። በጥቂት አገልጋዮች ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች አለመገዛት ብዙዎች ለብዙ አመት አምጠው የወለዱት ሪቫይቫል በአሞር ይቀጫል።

በተመሠረተው መሠረት ላይ

ስለ ስኬታማነት ነው እየተነጋገርን ያለነው። በእግዚአብሔር ዓይን ስኬታማ የሚባለው አገልጋይ ምን የሆነለት አገልጋይ ነው? የዚህን

ጥያቄ መልስ ለማየት ነው እየሞከርን ያለነው። ብዙ ሰዎችን ማስከተል የቻለ አገልጋይ ነው? ብዙ ገንዘብ ያለው አገልጋይ ነው? ትልቅ ሕንፃ የሠራ አገልጋይ ነው? በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ብዙ ቅርንጫፎች ያሉት ድርጅት የመሠረተ አገልጋይ ነው? የሕዝቡን ወቅታዊ ጥያቄዎች የሚመልስ፣ የሕዝቡን ወቅታዊ ችግሮች የሚፈታ አገልጋይ ነው? በዘመን አመጣሽ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚጠቀም አገልጋይ ነው?

ስኬታማው አገልጋይ እነዚህ ሁሉ ሆነውለት ሊሆን ይችላል። እነዚህ እዚህ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ በመሠረቱ መጥፎ ነገሮች አይደሉም። ሆኖም ለማንም ሰው ሊሆኑለት የሚችሉ ነገሮች ናቸው። አንድ ኮከብ ቆጣሪ፣ አንድ ቆማሪ፣ አንዲት ዝሙት አዳሪ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሊሆኑላቸው ይችላሉ። ስለዚህ ለአንድ የክርስቶስ አገልጋይ የስኬታማነቱ መለኪያ እነዚህ ሊሆኑ በፍጹም አይችሉም።

ከላይ እንዳየነው ስኬታማው አገልጋይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈርስ ሳይሆን የሚያንጽ ነው። በማን ላይ ነው ግን የሚያንጸው? የሕንፃው መሠረት ማነው? "ምንድነው?" ያላልኩት ሆነ ብዬ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" ይላል (1ኛ ቆሮ 3፡11)። የክርስትና እምነት የተመሠረተው በክርስቶስ ላይ ነው። ክርስትና ያለ መላእክት፣ ያለ ቅዱሳን፣ ያለ ሰማዕታት፣ ለመቆም ይችላል። ያለ ክርስቶስ ግን ለአንድ አፍታም እንኳን ለመቆም አይችልም።

ከክርስቶስ በስተቀር ሌሎች መሠረቶች መሥርተዋል በማለት ወንጌላዊው የክርስትና ዘርፍ ካቶሊካዊውንና አርቶዶክሳዊውን የክርስትና ዘርፎች ሊከሳቸው ብዙ መቶ አመታት ኖሮአል። ሆኖም በግወትም ይሁን ባለማወቅ በዘመናት ውስጥ ክርስትናን በክርስቶስ ላይ ሳይሆን በሌሎች የተለያዩ ነገሮች ላይ ለመመሥረት ሙከራ ያደረጉ ወንጌላውያን ክርስቲያኖችም አሉ። ዛሬም አሉ። ከእነዚህ ሌሎች መሠረቶች መካከል እንደ እምነት፣ እንደ ብልጽግና፣ እንደ ተአምራት ያሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

እሳት በማያቃጥለው የሕንፃ መሣሪያ

አንድ አገልጋይ የሚያፈርስ ሳይሆን የሚያንጽ መሆኑ፣ የሚያንጸውም በሌላ መሠረት ላይ ሳይሆን በተመሠረተው መሠረት ማለትም በክርስቶስ ላይ መሆኑ እጅግ መልካም ነገሮች ናቸው። የመጨረሻ

ነገሮች ግን አይደሉም። የስኬታማው አገልጋይ መጨረሻ እንዲያውም በምድር ላይ እያለ አይታወቅም። መጽሐፍ ቅዱስ ". . . እያንዳንዱ በሥጋው ስላደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር እንደየሥራው ብድራቱን ለመቀበል ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ አለብን" ይላል (2ኛ ቆሮ 5፡10)።

ጳውሎስ ይህንን የሚለው ስለማያምኑ ሰዎች ሳይሆን ስለሚያምኑ ሰዎች ነው። ስለ ጠፉ ሰዎች ሳይሆን ስለ ዳኑ ሰዎች ነው። ወደ ገሃነመ እሳት ስለሚወርዱ ሰዎች ሳይሆን ወደ መንግሥተ ሰማያት ስለሚገቡ ሰዎች ነው። "ሁላችንም" ነው የሚለው። እርሱም እራሱ በዚህ የፍርድ ወንበር ፊት ይቆማል ማለት ነው። ይህ የፍርድ ወንበር ሰዎች በምድር ላይ በነበሩበት ጊዜ ስላደረጉት ነገር (ስላገለገሉት አገልግሎት ማለት ነው) እንደየሥራቸው ዋጋቸውን የሚቀበሉበት ነው።

> . . .ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ (እንደሚያንጽ ማለት ነው) መጠንቀቅ አለበት . . . በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ወይም በብር፣ በከበረ ድንጋይ ወይም በእንጨት፣ በሣር ወይም በገለባ የሚገነባ ቢኖር እያንዳንዱ በምን እንደ ሠራ የሚገለጥበት የፍርድ ቀን ይመጣል። በዚያን ቀን የእያንዳንዱ ሥራ በእሳት ተፈትኖ ይገለጣል" (1ኛ ቆሮ 3፡10-13)።

ስድስት ዓይነት የሕንፃ መሣሪያዎች ናቸው በስም የተዘረዘሩት። እሳት በመቋቋም ችሎታቸው ነው ከላይ ወደ ታች ደረጃ የተሰጣቸው። ቶሎ ባለ መቅለጥ ወይም ቶሎ ባለ መቃጠል ችሎታቸው ማለት ነው። ወደድንም ጠላንም በተመሠረተው መሠረት ላይ እያነጽን ያለነው በእነዚህ የሕንፃ መሣሪያዎች ነው። አብዛኞቻችንም እያነጽን ያለነው በቀላልና በገፍ በዙሪያችን በምናገኘው የሕንፃ መሣሪያ እንደሚሆን እገምታለሁ። ያም ማለት በገለባ፣ በሣር፣ በእንጨት ማለት ነው። በዚህ ቅደም ተከተል። ዛሬ፣ በሰዎች ፊት፣ ሙሉ የምንመስል ብዙ አገልጋዮች፣ ያን ቀን፣ በጌታ ፊት፣ ሙልሜችንን እንደምንወጣ የተረጋገጠ ነገር ነው። ስለዚህ የፍርድ ቀን ሲያስብ ሳይሆን አይቀርም ሐዋርያው የሚከተለውን የጻፈው፦

> በሰዎች ወይም በመላእክት ቋንቋ የመናገር ችሎታ ቢኖረኝ እንኳ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ እና እንደሚንሿሿ ጸናጽል መሆኔ ነው። ትንቢት የመናገር ሥጦታ ቢኖረኝና ምሥጢርንም ሁሉ ብረዳ፣ ዕውቀትም ሁሉ ቢኖረኝ፣ ተራራን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚያዛውር እምነትም ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ያለኝን ሁሉ ለደሆች ባካፍል፣ ሥጋዬም እንኳን ሳይቀር በእሳት እንዲቃጠል

አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም (1ኛ ቆሮ 13፡ 1-3)።

ተራራን ከቦታ ወደ ቦታ በሚያነቃንቅ እምነት አገልግሎ ከንቱ መሆን? እራስን በእሳት ለመቃጠል አሳልፎ ሰጥቶ አንዳች ጥቅም ማጣት? እ! የስኬታማው አገልጋይ መስፈርት (standard) የቱን ያህል ከፍ ያለ ነው? ምንኛስ በማንም ሰው የማይደረስበት ነው? አገልጋይ የሚለውን ስም ለመላበስ አማኝ መቸኮል የለበትም። ስሙን የተላበስነውም ብንሆን መፍራት አለብን። አገልጋይ መጠንቀቅ አለበት። አገልጋይ እራሱን ሁልጊዜ መፈተሽና ማስፈተሽ አለበት። በማን ያስፈትሽ? በመጀመሪያ በጌታ በራሱ። ቀጥሎም በሌሎች አገልጋዮች። በማያንቆላጵሱት አገልጋዮች ቢሆን ደግሞ ይመረጣል። አገልጋይ ሁልጊዜ ለመማር፣ ሁልጊዜ ለመመከር፣ ሁልጊዜም ለመታረም የተዘጋጀ መሆን አለበት።

"ክብሬን ለሌላ አልሰጥም"

ተወዳጁ የእስራኤል ንጉሥ አንድ ጊዜ በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ወደቀ። ይህም የሆነው ንጉሡ የሕዝብ ቆጠራ ባስደረገ ጊዜ ነበር (1ኛ ዜና 21)። ንጉሡ ዳዊት በፈጸመው በዚያ ኃጢአት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ከእስራኤል ሰባ ሺህ የሚሆኑ ሰዎችን ገድሉአል። ለአንድ ንጉሥ የሕዝቡን ቁጥር ማወቅ ኃጢአት ነውን? አይደለም። ዛሬ መንግሥታት ሁሉ የሕዝባቸውን ቁጥር በዕድሜና በፆታ፣ በከተማና በገጠር፣ በብሔረሰብና በሃይማኖት፣ በትምህርትና በሞያ ለይተው ያውቃሉ። ወይም ለማወቅ ጥረት ያደርጋሉ። በየአገሩ የሕዝቡ ቁጥር በየአመቱ በአማካኝ በምን ያህል እንደሚጨምርም ይታወቃል። ዛሬ በየአገሩ ኤኮኖሚያዊውና ማህበራዊው እንቅስቃሴ የሚተለመው እንደዚህ ዓይነቱን መረጃ መሠረት በማድረግ ነው።

ታድያ ይኸ መንግሥታት ሁሉ የሚያደርጉትና ሊያደርጉትም የሚገባ የሕዝብ ቆጠራ ንጉሡ ዳዊት ሲያደርገው ለምን ኃጢአት ይሆናል? ከቶውንም እንደዚያ ባለ ጥንታዊ ዘመን እንደዚህ ያለ ዘመናዊ ነገር ማድረጉ አያስመሰግነውምን? አሳስመሰገነውም። ቆጠራው አልክረም ኃጢአቱ። ያንን ቆጠራ ለማስደረግ የተነሳሳበት የውስጥ ፍላጎቱ (motive) ነበር ኃጢአቱ። ያ ፍላጎቱ በእግዚአብሔር ፊት ንፁህ አልነበረም።

እስከዚያ ጊዜ ድረስ ዳዊት ባላቋረጠ ዘመቻ ላይ ነው የነበረው። በዘመተበት ቦታ ሁሉ እግዚአብሔር ድል ይሰጠው ነበር። በዙሪያው የነበሩ መንግሥታት ሁሉ ገብረውለታል። ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ ከነበሩ መሳፍንትና ነገሥታት ማንም ያላስፋፋውን ያህል የእስራኤልን ድንበር አሰፋፍቷል። አሁን ሕዝቡን የሚያስቆጥረው የሠራዊቱን ብዛት ለማሳየት ነው። የገናናነቱን ልክ ለማሳወቅ ነው። ባለፉት ዘመቻዎች ሁሉ ድልን ያቀዳጀው የሠራዊቱ ብዛት እንደ ሆነ ማሰብ ጀምሮአል። በአጭሩ ዳዊት የእግዚአብሄርን ክብር ተሻምቷል። እግዚአብሔር ደግሞ ክብሩን ለሌላ አይሰጥም (ኢሳ 48፡11)።

ዳዊትን ያጋጠመው ይህ ፈተና በመከናወን ማግሥት ማንንም አገልጋይ ሊያጋጥመው የሚችል ፈተና ነው። የዚህ አይነቱ ፈተና ወደ እኛ የሚመጣው በተለይ ድል በመንሳታችን ደስ ብሎን ሳያባራ፣ በስኬታችን ስቀን ሳናበቃ ነው። የድል ጊዜ ሰው ከብርቱ ትግል በኋላ እፎይታ፣ ከሀዘን በኋላ ደስታ፣ ከውጥረት በኋላ ፋታ የሚያገኝበት ጊዜ ነው። መንፈሱና ሥጋው ከሰነበቱበት ("ተጠንቀቅ" ሁኔታ ውስጥ ወጥተው በ"አሳርፍ" ወይም በ"ተዝናና" ሁኔታ ውስጥ የሚገቡበት ጊዜ ነው። ትጥቅ የሚላላበት ጊዜ ነው። እንደዚህ ያለው ጊዜ ለጠላት የሚሰጠው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሆነ በምድራዊውም ጦርነት ይታወቃል። እንደዚህ ዓይነቱን ጊዜ ጠብቆ ነው ሰይጣን ዳዊትን ያጠቃው። እንደዚህ ባለው ጊዜ ነው ዳዊትን የመሰለ ታላቅ ጦረኛ ንጉሥም በጠላት ዒላማ ውስጥ በቀላሉ የገባው።

እግዚአብሔር ክብሩን ለሌላ ለማንም አይሰጥም። እግዚአብሔር ክብሩን ከሌላ ከማንም ጋር አይጋራም። "እንደልቤ የሆነ ሰው" ብሎ ለመሰከረለት ለዳዊትም በዚህ ነገር አስተያየት አላደረገለትም። እግዚአብሔር ክብሩን የሚፈልገው ከገዛ ሕዝቡም ብቻ እንኳን አይደለም። የታላቂቱ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ለሰባት አመታት እንደ ከብት ሳር እንዲበላ የተፈረደበት ምን ነበር? "ይህችን ታላቅ የባቢሎን ከተማ ክብሬና ግርማዬ እንዲገለጥባት በኃይሌ ብርታት የሠራኋት እኔ አይደለሁምን?" ስላለ ነው (ዳን 4፡30)። "ንግግሩን ገና ሳይጨርስ" ነበር የእግዚአብሔር ፍርድ የተላለፈበት። ሄሮድስን የእግዚአብሔር መልአክ የመታውና በትል ተበልቶ የሞተው ክብርን ለእግዚአብሔር ስላልሰጠ ነው (ሐዋ 12፡20-23)።

ስለ "ሪቫይቫልና መንደርደሪያዎቹ" በሚናገረው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ይህንን ንውስ ርዕስ መጨመር ለምን አስፈለገ? የሪቫይቫል ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር ከወትሮው በጣም በተለየ ሁኔታ በዕምቃምና በመጠናም መልኩ የሚገለጥበት ጊዜ በመሆኑ ነው። የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥባቸው አገልጋዮች ሁሉ ይህንን የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን ባህርይ በቅጡ የተረዱ ላይሆኑ ስለሚችሉ ነው።

ምናልባትም በገዛ ሥጋቸው ውስጥ ሁልጊዜ የሚኖረውን ክብርን የመፈለግ ደካማ ጎን ገና ያልነቁበት ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። በሪቫይቫሉ ውስጥ ተጠቃሚና ጠቃሚ እንጂ ተጎጂና ጎጂ እንዳይሆኑ በቅድሚያ ለማስገንዘብ ነው።

የሞግዚቶች ያለህ!

ይህንን ንዑስ ርዕስ "የእረኞች ያለህ!" ማለት ይቻላል። የሪቫይቫል ጊዜ ብዙ ልጆች ለእግዚአብሔር የሚወለዱበት ጊዜ ነው። ብዙ ልጆች በሚወለዱበት በዚያ ብዙ አሳዳጊዎች ያስፈልጋሉ። ይህ ንዑስ ርዕስ "ያሳዳጊዎች ያለህ!" ቢባልም ይስማማኛል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሪቫይቫል ስትጠብቅ አሁን ሰላሳ አመታት አስቆጥራለች። ምናልባት ለብዙዎች ስለ ሪቫይቫል የሰሙት የተሰፋ ቃል ዘግይቶባቸዋል። እውነት ዘግይቶ ከሆነ የዘገየው በቂ ሞግዚቶች እስኪዘጋጁ ድረስ ነው። ሞግዚቶች ሳይዘጋጁ ልጆች ቢወለዱ ምን ያደርጋል? ከሚወለዱት ብዙዎች ይሞታሉ። በእግዚአብሔርም (በአባታቸው) ቤት ለቅሶ ይሆናል። እንዲህ እንዳይሆን እግዚአብሔር ይከልክል።

እኛም እንከልክል። እኛ ደግሞ እንዴት አድርገን ነው የምንከለክለው? በዚህኛውና በቀደመው ምዕራፎች ከምንከለክልባቸው መንገዶች ውስጥ ዋና ዋና የመሰሉኝን ጠቅሻለሁ። እያንዳንዳችን የተጠቀሱትን መሰናክሎች ለማንሳትና የተጠቀሱትንም መንደርደሪያዎች ለመዘርጋት የሚቻለንን ሁሉ ስናደርግ ነው። እንደዚያ ስናደርግ አንድም ሕፃን በሕፃንነቱ እንዳይሞት መከልከል ባይቻለንም እንኳን በሕፃንነታቸው የሚሞቱ ሕፃናትን ቁጥር (infant mortality rate) በእጅጉ እንቀንሳለን።

እንደዚያ የምናደርገው ደግሞ ስለ አገልግሎት፣ ስለ ራሳችንና ስለሌሎች አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን የተለወጠ አመለካከት ሲኖረን ነው። "የወንድሜ ጠባቂው ኖኝን?" የሚል ቋንቋ በመካከላችን መሰማቱ ፈጽሞ ሲቀር ነው (ዘፍ 4:9)። በምትኩ የሁላችንም መመሪያ " . . .ግልገሎቼን መግብ . . . ጠቦቶቼን ጠብቅ. . . በጎቼን አሰማራ" የሚል ሲሆን ነው (ዮሐ 21:15-19)። ያኔ በእግዚአብሔር ቤተሰብ መካከል መገፋፋት እየቀነሰ መተቃቀፍ ይበዛል። እንደዚያም ሲሆን የእግዚአብሔር ክብር በምድራችን ላይ ይለቀቃል። የኢትዮጵያም መንቀፍት እውን ይሆናል።

ዘጠኝ

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 David B. Barrett And Frank Kaleb Jansen. "The World In Figures" Congress Notebook, Lausanne II, 1989.

2 በቁጥር ወደ ሰላሳ የሚሆኑ በስም ሊጠቀሱ የ ችችሉ ስጦታዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ።

አስር

የመጨረሻው መጨረሻ

በኢትዮጵያ ሊከሠት ስላለው ሪቫይቫል ሲነሳ ቁጥራቸው ጥቂት ያይደለ አማኞች ያ ሪቫይቫል የሚከሠተው ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በነፍስ መከፍና በአገር አቀፍ ደረጃ ሊያደላድለን እንደሆነ ያስባሉ። ያኔ መሐይምነታችን በትምህርት እንደሚለወጥ፣ ደህንነታችን በብልጽግና እንደሚዋጥ ያምናሉ። ያን ጊዜ ፀሐያችንና ዝናማችን እንደሚፈውሱ፣ ተራሮቻችንና ኮረብቶቻችን በረከት እንደሚያፈሱ ተስፋ ያደርጋሉ። ሚዳችን ልምላሜ እንደሚለብስ፣ በረሀችንም እንደሚያረስ ይጠቁማሉ። በሁሉ ረገድ እራሳችንን እንደምናሸንፍ፣ ለሌሎችም እንደምንተርፍ ይናገራሉ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ሊጎበኝበት ስላለው መንፈሳዊና ሥጋዊ በረከቶች በ"ቅዱስ መንፈሱ" ሲናገር ይህ ጸሐፊ የእርሱን ያህል የሰማ ሌላ ሰው ሊኖር መቻሉን እስከሚጠራጠር ድረስ ሰምቷል። በሰባዎቹ መጨረሻ ላይ አንድ አሜሪካዊ ወደ ኢትዮጵያ መጣ። ባረፈበት ሆቴል የእንግዶች ማረፊያ (lounge) ውስጥ የሆነ የሆነ ነገር ሲናገር የሰሙት አንዳንድ ወንድሞች ወደ ቢሮዬ ይዘውት መጡ። አሜሪካዊውን አነጋገርኩት። ያለኝ ነገር ከሞላ ጎደል ይህንን ይመስላል፦

> ክርስቲያን ባለ ኢንዱስትሪ ነኝ። አንድ ቀን በቤቴ ውስጥ ስጸልይ እግዚአብሔር ስለ አገራችሁ ተናገረኝ። ሐብታም አገር ናት። መለመን አይገባትም። ከዋና ከተማዋ ብዙም ሳይርቅ፤ ብዙም ደግሞ ወደ ውስጥ ሳይጠልቅ፣ ሊወጣ የሚችል የከበረ የማዕድን ሐብት አላት። ይህንን ለፕሬዚዳንታችሁ ጻፍኩለት። ክርስቲያን ጂኦሎጂስቶች በራሴ ወጭ ይዤልህ ልምጣ። የአገርህን አፈር ይመርምሩልህ አልኩት። ስድስት ጊዜ ፃፍኩለት። አንድም መልስ አልሰጠኝም። ቢቸግረኝ እራሴ ተነስቼ መጣሁ።

ሌላ ጊዜ በናይሮቢ (ኬንያ) አንድ ኡጋንዳዊ አገኘሁ። የተገናኘነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። ከሩዋንዳዊት ባለቤቱ ጋር ነበር። እንዲህ አለኝ፦

ከሁለት አመት በፊት ጌታ ስለ ኢትዮጵያ ተናገረኝ። በኃይልና በብልጽግና (power and prosperity) እጎበኛታለሁ አለኝ። ይህንንም የማደርገው ወደ ዓለም ሁሉ ለመሄድና ወንጌልን ለመስበክ እንዲችሉ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እኔና ባለቤቴ ሚስዮናውያን ሆነን ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት እየተዘጋጀን ነን። ባለቤቴ የአማርኛ ቋንቋ እያጠናች ነው።

አሁንም ሌላ ጊዜ በዕድሜአቸው በጣም የገፉ ባልና ሚስት ከአውስትራሊያ መጡ። በእምነታቸው ካቶሊኮች ናቸው።

> እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ተናገረን። እኛ ኢትዮጵያን አናውቃትም ነበር። እግዚአብሔር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሳየን። የምንተዳደረው በጡረታ አበል ነው። ያንን አጠራቅመን ይህችን የእግዚአብሔር ዓላማ ያለባትን አገር ለማየት መጣን።

አረጋውያኑ ባልና ሚስት በገጠርና በከተማ እየተዘዋወሩ በሚዳሙና በጎዳናው፣ በለማኙና በሊስትሮው ሁሉ ላይ እጆቻቸውን እየጫኑ ሲጸልዩ ሰንብተው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

እንደዚህ ያሉ ከውጭ አገሮች ዜጎች ብቻ የሰማኋቸውን ሌሎች አምስትና ስድስት አጋጣሚዎች፣ በአገር ውስጥ ከሰማኋቸውም ትንቢቶች ብዙ መጥቀስ እችላለሁ። ትንቢቶቹን የመፈተኑን ጉዳይ አሁንም ለአንባቢ እተዋለሁ። አንድ ጥያቄ ማንሳት ግን የግድ ይኖርብኛል። የሚመጣው ሪቫይቫል ከችግሮቻችን ሁሉ ሊገላግለን ነው ወይ የሚመጣው? እግዚአብሔርስ ሪቫይቫል የሚልክበት ዋነኛ ምክንያት ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ያለፉትን ሁለት ሺህ አመታት "የመጨረሻው ቀን"፣ "የመጨረሻው ዘመን"፣ "የመጨረሻው ሰዓት" እያለ ይጠራቸዋል (ሐዋ 2:17፤ ዕብ 1:2፤ 1ኛ ጴጥ 1:20፤ 1ኛ ዮሐ 2:18)። "የመጨረሻው ዘመን" የሚለው አባባል ከዚህ ቀደም ሲል ሌሎች ዘመናት እንደ ነበሩ ያሳስበናል። እነዚያም ዘመናት እንደ መጡና እንደ ሄዱ፣ የተመደበላቸውን ጊዜ እንደ ጀመሩና እንደ ጨረሱ፣ ያስታውሰናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ይኸኛውም ዘመን ጅማሬ እንደ ነበረው ሁሉ ፍፃሜም እንደ ሚኖረው ያስገነዝበናል።

የመጨረሻው ዘመን የተጀመረው ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥጋ ወደዚህች ዓለም ሲመጣ ነበር። ያ ከሆነ አሁን ሁለት ሺህ አመታት አልፈዋል። የመጨረሻው ዘመን ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህች ዓለም ሲመጣ ይጨረሳል። ለመሆኑ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደዚህች ዓለም የሚመጣበት ጊዜ መቼ እንደሚሆን የሚያውቅ አንዳች

ነገር አለ? አንዳች ነገር ሳይሆን ብዙ ነገር አለ። ዋና ዋና የመሰሉኝን በዚህ የመጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ እናያለን።

ትንቢቱ እና ዓለም አቀፋዊ ይዘቱ

ሪቫይቫል በመጠባበቅ ላይ የምትገኝ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለችም። ከአፍሪቃ አገሮች ውስጥ የኤርትራ፣ የሱዳን፣ የጋና፣ የናይጄሪያ፣ የኬንያ፣ የኡጋንዳ፣ የሩዋንዳ፣ የደቡብ አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ሪቫይቫል እንደሚልክላቸው በቅዱስ መንፈሱ እንደተናገራቸውና እነርሱም በመጸለይና በመጠባበቅ ላይ እንዳሉ አውቃለሁ። ከሰሐራ በስተ ደቡብ ያሉ የሌሎች አገሮች አብያተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ተስፋ ሳይኖራቸው እንደማይቀር እገምታለሁ።

የጀርመን ቤተ ክርስቲያን ለመላው አውሮፓ በሚተርፍ ሪቫይቫል እንደሚጎበኛት እግዚአብሔር እንደተናገራትና እርስዋም በመጸለይና በመጠባበቅ ላይ እንዳለች አውቃለሁ። ለአውስትራሊያ ቤተ ክርስቲያን በ1922 በስሚዝ ዊግልስዎርዝ አማካይነት ተመሳሳይ ትንቢት እንደተነገረላት ሰምቻለሁ። እንዲያውም ያንን ሪቫይቫል በዓይንህ ሳታይ አትሞትም የተባሉ አዛውንት ሰው በሚልኒዬሙ መጨረሻ ላይ (2000) በሚልበርን አግኝቻለሁ።

የቻይና እና የላቲን አሜሪካ አብያተ ክርስቲያን በሪቫይቫል ውስጥ ናቸው ይባላል። ስለተቀሩት የእስያ አገሮች፣ በብዙ ደሴቶች ውስጥ ስላሉት አብያተ ክርስቲያን የሰማሁት ነገር የለም። ስለ ሰሜን አሜሪካ አብያተ ክርስቲያን ያላነሳሁት ስለ እነርሱ ብዙ ስለሚጸፍና ብዙም ስለምንሰማ ነው። በአጠቃላይ ስለ ሁሉም የሚጸፈውና የሚወራው ሁሉ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። ልዩነት ቢኖር ምናልባት እኩሌቶቹ "አሁን በሪቫይቫል ውስጥ ነን" ሲሉ እኩሌቶቹ ደግሞ "ገና ሪቫይቫል እንጠብቃለን" በማለታቸው ነው።

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ላሉት የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ሪቫይቫል እንደሚልክላቸው በቅዱስ መንፈሱ የተናገረበት ይህ የትንቢት ቃል በቅዱስ ቃሉም የተደገፈ ነው ወይ? አዎ በኋላ "ምልክቶቹ" በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር ተጨማሪ ማስረጃ እጠቅሳለሁ። እስከዚያው የሚከተሉትን ሁለት ጥቅሶች ብቻ ልጥቀስ።

> ከዚህ በኋላ መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈሰሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ራእይ ያያሉ . . . ታላቁና አስገራሚው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ደም

ትመስላለች፤ የእግዚአብሔርንም ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል . . . (ኢዩ 2፡ 28-32)።

ይኸ ትንቢት የተነገረው ስለ መጨረሻው ዘመን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ አረጋግጦታል (ሐዋ 2፡ 17-21)። የተነገረውም ስለ "እስራኤል ዘሥጋ" ሳይሆን ስለ "እስራኤል ዘመንፈስ" እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ጨምሮ ግልጽ አድርጎታል (ሮሜ 10፡9-13)። ትንቢቱ የተነገረላቸው ሰዎች ትንቢቱ በተነገረላቸው ጊዜ "እስራኤል ዘሥጋ" ነበሩ። ጴጥሮስ በሚፈጸምላቸው ጊዜ ግን "የጌታን ስም በእምነት በመጥራት" 'እስራኤል ዘመንፈስ" ሆነዋል። ኢዩኤል "እግዚአብሔር" (ያህዌ) ያለውን ጳውሎስ "ጌታ" (ኢየሱስ) በሚለው እንደተካው ልብ ይሏል።

በመጨረሻው ዘመን መጀመሪያ ላይ የዘነበው ጳንጠቆስጤአዊ ዝናም የኢዩኤል ትንቢት ፍፃሜ እንደሆነ ጴጥሮስ ነግሮናል። አሁን በመጨረሻው ዘመን መጨረሻ ላይ ያ ዝናም እንደገና መዝነብ ጀምሮአል። የመጀመሪያው የዘነበው በሜዲትራንያን ባህር ምሥራቃዊ አጋማሽ ዙሪያ ባሉት አገሮች ላይ ነበር። የአሁኑ በዓለም ሁሉ ላይ ነው እየዘነበ ያለው። ኢዩኤልም እግዚአብሔር ". . . . የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ አዝንቦላችኋል . . ." በማለት ስለ ሁለት ዝናሞች ይናገራል (2፡23)። የፊተኛው የበልጉ፣ የኋለኛው ደግሞ የክረምቱ መሆኑ ነው። የክረምቱ ዝናብ ምድርን ለዚያ ዘመን የመጨረሻ ለሆነው መከር የሚያዘጋጃት ከፊተኛው ይልቅ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ዝናም ነው።

> ለሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል በመላው ዓለም ይሰበካል፤ በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል (ማቴ 24፡14)።

መጨረሻው ይመጣል ማለት የመጨረሻው ዘመን ይጨረሳል ማለት ነው። ክርስቶስ ዳግመኛ ወደዚህች ዓለም ይመጣል ማለት ነው። የዓለም መጨረሻ ይሆናል ማለት ነው። ያ ከመሆኑ በፊት ግን ወንጌል በመላው ዓለም ለሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ይሰበካል ማለት ነው። የመጨረሻው ዘመን መጨረሻ የወንጌል ሥርጭት ዘመን ነው። የወንጌል ሥርጭቱም ይዘት ዓለም አቀፋዊ ነው። ስለሆነም በየአህጉሩና በየአገሩ ያሉ አብያተ ክርስቲያን ሁሉ እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉም ሆነ በቅዱስ መንፈሱ ሪቫይቫል ሊልክላቸው ተስፋ እንደሰጣቸው ቢያምኑ አልተሳሳቱም።

ግሎባዊም፣ ጎሣዊም

የትንቢቱን ዓለም አቀፋዊነት ለማሳየት ሌላ አንድ ነገር በምሳሌነት ልጨምር። ያለፉት አስር አመታት ዓለማችን በአንድ ጊዜ ግሎባዊም፣ ጎሣዊም በሆኑ ሁለት አመለካከቶች እየተጥለቀለቀች የመጣችባቸው ናቸው። "ግሎባላይዜሽን" እና "ኤትኒሲቲ" የተባሉት ቃላት አሁን በየዕለቱ ከየወረቀቱና ከየአንደበቱ የሚያመጡ ሆነዋል። የተነሳሁት የእነዚህን ቃላት ወይም ጽንሰ ሀሳቦች ትርጉም ለማስተንተን አይደለም። የተነሳሁት በ1974 ዓ.ም. አካባቢ የተነገረ አንድ ትንቢት ለማስታወስ ነው። የዚያ ትንቢት አስደናቂነት የሚገባን የተነገረበትን ጊዜ መለስ ብለን ስናስተውለው ነው።

ያ ጊዜ ዓለም በሞላው በሁለቱ ማለትም በካፒታሊስቱና በሶሻሊስቱ ጎራዎች የተከፈለችበት ነበር። የሶሻሊስቱ ጎራ ከሚመራባቸው መፈክሮች መካከል ግንባር ቀደሞቹ "የዓለም ሞቁኖች ተባበሩ!"፣ "ዓለም አቀፋዊ ወዝ አደርነት ይለምልም!" የሚሉ ነበሩ። ከእነዚህ መፈክሮች ጎላ በቢልዮኖች የሚቆጠሩ የምሥራቅ አውሮፓ፣ የእስያ፣ የላቲን አሜሪካና የአፍሪቃ ወዝ አደሮች፣ ገበሬዎች፣ ተማሪዎችና ምሑራን ተሰልፈዋል። ከእነዚህ መፈክሮች ጀርባ "የማይበገር" የሚመስል እጅግ ግዙፍ የሆነ የጦር ኃይል፤ ለአንድ አፍታ እንኳን ተግ የማይል፣ ለማንም ደግሞ ፋታ የማይሰጥ የፕሮፖጋንዳ ማሺነሪ፣ በጣም የተወሳሰበ፣ የአንድ አገር ዜጎችንም ሁሉ የተበተበ የስለላና የቁጥጥር መዋቅር ቀን ከሌት ይንቀሳቀሳሉ።

ያ ዘመን ለአንድ ኢትዮጵያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ባለ ኢንዱስትሪ ይልቅ አንድ ካምቦዲያዊ የፋብሪካ ሠራተኛ እንደሚቀርበው ተደርጎ የሚታመንበት ነበር። በቅርብ ያለውን፣ የወንዝን ልጅ፣ ምናልባትም በሥጋ እንኳን የሚዛመድን ሰው በማይታረቅ ቀራኔ የተጣሉት "ጠላት" እያሉ፣ ውቅያኖስ ተሻግሮ፣ አህጉር አቋርጦ፣ ጨርሶ የማያውቁትን ሰው "ጓድ" የሚሉበት ነበር ያ ዘመን። ሶሻሊስታዊው ሥርዓት ከሰባ አመታት ብዙም ባልበለጠ አጭር ዕድሜው ዓለሙን በሙሉ "መደብ አልባ" ብቻ ሳይሆን፣ ብሔር አልባ፣ አገር አልባና ድንበር አልባ ሊያደርግ ትንሽ የቀረው የሚመስልበት ሁኔታ ላይ የተደረሰበት ነበር ያ ዘመን።

በዚያን ዘመን በአንድ የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ላይ የሚከተለው የትንቢት ቃል መጣ፦

> ልጆቼ ሆይ! ይህ ሕዝብ ገና በጎሣና በዘር ይበጣበጣል። ይህንን እርም ወደ ቤቴ እንዲታሸገው ምሥጢርን ከወዲሁ እገልጥላችኋለሁ።

በጊዜው ከነበረው ሁኔታ (ግሎባዊ ሁኔታ እንበለው?) አንፃር ሲታይ ይህንን ትንቢት ከእግዚአብሔር ነው ብሎ ለመቀበል በጣም ያስቸግር ነበር። እግዚአብሔር ግን የሚናገረው በጊዜው እንዳለው ሁኔታ ሳይሆን እንደ ሁሉን ዓዋቂነቱ ነው። ስለሆነም አስር አመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተናገረው ሆነ። በሆነም ጊዜ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም የሆነው። ዓለም አቀፋዊ ይዘት ባለው መልኩ ነው የሆነው። የቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት፦

ሩስያ	አርሜንያ	ቱርክሚኒስታን
ጆርጂያ	አዘርባጃን	ኡዝቤክስታን
ኢስቶንያ	ካዛክስታን	ኡክሬይን
ሊቱዋንያ	ኪርጊስታን	ቤላሩስ
ላትቪያ	ታጂኪስታን	ሞልዶቫ

ተብላ አስራ አምስት ሆነች።

የቀድሞዋ ቼኮዝሎቫኪያ ቼክና ስሎቫኪያ ተብላ ለሁለት ተከፈለች። የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያም፦

ሰርቢያና ሞንቴኒግሮ
ቦዝኒያና ሔርሲጎቪና
ክሮኤሽያ
ስሎቪንያ
መቄዶንያ

ተብላ አምስት ሆናለች። ገናም ያለቀላት አትመስልም። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያም ሁለት ወጥቶአታል። በዚያ ያበቃላት ይሁን ወይም አይሁን በእርግጠኛነት መናገር የሚችል ማንም ሰው አሁን የለም። በቅርቡ ኢንዶኔዥያም ሁለት ሆናለች። ሦስት ብትሆንላቸው የሚወዱ ደሴቶች እንዳሉም ይሰማል።

ዓለም ግሎባዊም ጎሣዊም እየሆነች የመሄድዋ ግሥጋሴ የሚገታ አይመስልም። እነዚህ ክስተቶች አሁን እየተንጋገርንለት ባለው ሪቫይቫል ውስጥ ምን ፋይዳ ይኖራቸው ይሆን። የግሎባዊው ግልጽ ነው። ዓለምዋን አንዲት ትንሽ መንደር ያደርጋታል። በእስያ ሆኖ በአፍሪቃ ስለሚፈነዳ ሪቫይቫል ለማወቅ ምንም ጊዜ አይወስድም። ምናልባትም ከእስያ ሳይወጡ በዚያ ሪቫይቫል ውስጥ ተካፋይ መሆን ይቻል ይሆናል። የጎሣዊውም ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ስለ ሕዝቦች የሚገደውን ያህል ስለ ፖለቲካ ድንበሮች እንደማይገደው ነው የምናውቀው።

ጌታ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ተልዕኮ "...ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ ... ደቀ መዛሙርቱ አድርጓቸው ..." የሚል ነው (ማቴ 28፡19)። ቋንቋውን የሚያውቁት ሰዎች እንደሚነግሩን "ሕዝቦች" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል "ኤትኖስ" ነው። በየዕለቱ፣

ከየወረቀቱና ከየአንደበቱ ይደመጣል ያልኩት "ኤትኒሲቲ" የተባለው ቃል ዝርያው ከዚያ ነው። በዘመኑ ፍፃሜ ላይ እንደሚሆን ለሐዋርያው ዮሐንስ የተገለጠለት ራእይም የሚያረጋግጥልን ተልዕኮው የሚጠናቀቀው በዚህ መልክ እንደሚሆን ነው፦

> ... እነሆ በዙፋኑና በበጉ ፊት ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመው ነበር። በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብለው ጮሁ፦ "ማዳን በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው የአምላካችንና የበጉ ነው" (ራእ 7፡9-10፤ 5፡9-10)።

ጥላዎቹ

በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የክርስቶስ ጥላ ወይም ምሳሌ ስለሆነው የናስ እባብ አንስቼ ነበር። በሙሴ መጻህፍት ውስጥ የጥላነት ጠባይ የሚታይባቸው ሰዎችና ሥርዓቶች ብዙ ናቸው። ባለ ጥላውን የምናገኘው ግን ሁልጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ከባድ እንቅልፍ በጣለበትና በጎላ ሴት (ሚስቱ) አድርጎ የፈጠራትን አጥንት ከጎኑ በወሰደ ጊዜ አዳም የክርስቶስ ጥላ ነበር። በክርስቶስም ላይ እንዲሁ ከባድ እንቅልፍ (ሞት) ጥሎበት ከጎኑ በፈሰሰው ደምና ውሀ ቤተ ክርስቲያንን (ሚስቱን) ፈጥሮአልና።

የኖህ መርከብ የክርስቶስ ጥላ ነበር። ጥላውና አካሉ የሚመሳሰሉባቸውን ነጥቦች ለማሳየት ብጀምር ይህችን መጽሐፍ ከምፈልገው በላይ ዳጎስ ያደርጋታል። አብርሃም የሚወደውን አንድ ልጁን ለመሰዋት ሲዘጋጅ ስለ እኛ አንድ ልጁን ለመስዋዕትነት የሰጠው የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ነበር። ይስሐቅም መስዋዕት ለመሆን ለአባቱ ፈቃድ እራሱን በሰጠ ጊዜ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ለአባቱ የታዘዘው የክርስቶስ ጥላ ነበር። ግብፅን የመታው መቅሰፍት እንዳያገኛቸው፣ ከግብፅም ባርነት ነፃ እንዲወጡ እስራኤላውያን በየቤታቸው ያረዱት የፋሲካ በግ ከኃጢአት ባርነት በደሙ ለሚዋጀን የእግዚአብሔር በግ ጥላው ነበር።

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከዚህ ቀጥዬ ስለ ሁለት ጥላዎች በተከታታይ እናገራለሁ። ከላይ የጻፍኩአቸውን ሁለት አንቀፆች የጻፍኩት አንባቢው ስለ ጥላዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊነት አሳብ እንዲኖረው ነው። ልጽፍባቸው ያለሁት ሁለት ጥላዎች አሁን ያለነው በመጨረሻው ዘመን መጨረሻ ላይ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። እንባቢው እነዚህን ሁለት ጥላዎች ካያቸው በኋላ በመጨረሻው ዘመን መጨረሻ ላይ የመሆናችን ነገር ቁልጭ ብሎ ይታየዋል።

ስድስተኛው ቀን

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን፣ በውስጣቸውም ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ የፈጠረው በስድስት ቀናት ውስጥ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዘፍ 1)። የፍጥረቱ ሁሉ መደምደሚያ አድርጎ አዳምን የፈጠረው በስድስተኛው ቀን ነው። ሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከመፍጠር ሥራው ያረፈበት ቀን ነው (ዘፍ 2፡ 1-3)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት መጻሕፍት ሁሉ የዘፍጥረትን መጽሐፍ ያህል ጥያቄ የሚያስነሳ ሌላ መጽሐፍ የለም። ከዘፍጥረትም መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ያህል ብርቱ ሙግት የሚያስነሳ ሌላ ክፍል የለም። ስድስቱ ቀናት ባለ ሃያ አራት ሰዓት ቀናት ነበሩ ወይ? ፀሐይ የተፈጠረችው በአራተኛው ቀን ሲሆን ስለ መጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት "መሸ፤ ነጋም፤ የመጀመሪያ ቀን"፣ "መሸ፤ ነጋም፤ ሁለተኛ ቀን"፤ ወዘተ. ማለት እንዴት ተቻለ? በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የአንዳንድ ሰዎችን ዕድሜ መሠረት በማድረግ ሲሰላ በምድር ላይ የሰው ልጅ እድሜ በጠቅላላው ስድስት ሺህ አመት ብቻ ነው። ዛሬ የብዙ ሚልዮን አመታት ዕድሜ እንደ ነበራቸው በምርምር የተረጋገጠላቸው የሰውና የእንሰሳት አካላት ቅሪቶች (fossils) በቁፋሮ እንደ ተገኙ እያወቅን የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ እውነት ነው ብሎ መቀበል እንዴት ይቻላል?

ጥያቄዎቹ ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ መልስ የለሾች አይደሉም። መልሶቹ አንዳንዴ ከሰው ሰው ሊለያዩ ይችላሉ። አንዳንዴም ሰውን ሁሉ እኩል ላያጠግቡ ይችላሉ። እንደዚህም መሆኑ ያለቀና የደቀቀ፣ ሳያኝኩትና ሳያላቁጡት የሚውጡት ነገር ብቻ ለለመዱ ሰዎች ላይስማማቸው ይችላል። ለአንዳንዶች ግን የእግዚአብሔር ነገር ለሰው አእምሮ አለመቅለሉ፣ አንዳንዴ እስከ ወዲያኛውም ድረስ ሊገባን አለመቻሉ ለመጽሐፉ መለኮታዊነት ተጨማሪ ማረጋገጫ ይሆንላቸዋል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በዚህ በስድስቱ ቀናት የመፍጠር ሥራ ሂደት ውስጥ የጥላነት ጠባይም ይታያቸዋል። እንደዚህ እንዲታያቸው ምክንያት የሚሰጣቸው መጽሐፍ ቅዱሱ እራሱ ነው።

> ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳን የተከደነው ለሚጠፉት ነው። ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሐን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ . . . "በጨለማ ብርሃን ይብራ" ያለው እግዚአብሔር ብርሐኑን በልባችን አብርቶአልና (2ኛ ቆሮ 4፡3-6)።

በዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ የመጀመሪያ ቁጥሮች ውስጥ ጨለማ በምድር ጥልቅ ላይ እንደ ነበረ ተጽፎአል። ዛሬም በክርስቶስ በማያምኑ ሰዎች አሳብ (ልብ) ላይ ጨለማ እንዳለ ነው ይኸ ጥቅስ የሚናገረው። ያኛውን ጨለማ "ብርሃን ይሁን" በማለት ያስወገደው እግዚአብሔር ነበረ። ዛሬም "በጨለማ ብርሃን ይብራ" በማለት ብርሃኑን በልባችን የሚያበራ እግዚአብሔር እንደሆነ ነው ይኸ ጥቅስ የሚያብራራው። ያ በምድር ጥልቅ ላይ የነበረ ጨለማና ይኸ በሰው አሳብ ላይ ያለ ዕውርነት አንድ ናቸው ወይስ ሁለት? የዚያኔው "ብርሃን ይሁን" እና የዛሬው "ብርሃን ይብራ"ስ?

> ወዳጆች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ አመት፣ ሺህ አመትም እንደ አንድ ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር አንርሳ (2ኛ ጴጥ 3፡8)።

ጴጥሮስ ይህንን የሚለው እግዚአብሔር ዘላለማዊ አምላክ ስለሆነ አንድ ቀንም ሆነ አንድ ሺህ አመት ለእርሱ ያው ናቸው፣ ምንም ልዩነት የላቸውም ሊለን ፈልጎ ሊሆን ይችላል። ሊለን የፈለገው ግን ይህንን ብቻ ላይሆን ይችላል። ሊለን የፈለገው ይህንን ብቻ ቢሆን ኖሮ "ይህን . . . አንድ ነገር አትርሱ" በማለት ለምን ያስጠነቅቀናል? እየተናገረ ያለው ደግሞ ስለጌታ ምፅአት ነው። የጌታ ዳግም ምፅአት የዘገየ ስለሚመስላቸው ሰዎች ነው። ይህ የጴጥሮስ አባባል እነዚያ ስድስት ቀናት ለእነዚህ ስድስት ሺህ አመታት ጥላዎች ነበሩ የሚል አንድምታ እንዳለው ነው ብዙዎች የሚያምኑት።

ሰባተኛው ቀን እግዚአብሄር ከሥራው ያረፈበት ቀን እንደሆነ የዘፍጥረት መጽሐፍ ይነግረናል። ጌታ ኢየሱስ ግን "አባቴ እስከ ዛሬ ድረስ ይሠራል፣ እኔም ደግሞ እሠራለሁ" አለ (ዮሐ፣ 5፡17)። እግዚአብሔር "ከሠራው ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን አረፈ" ከተባለ በኋላ አባትና ልጅ እስከ ዛሬ የሚሠሩት ምንድነው? ሰው በኃጢአት ወድቆ እያለ እግዚአብሔር ዕረፍት የለውም። ስለዚህ ያለፉት ስድስት ሺህ አመታት እግዚአብሔር በኃጢአት የወደቀውንና ከእርሱም የተለየውን የሰውን ልጅ ከራሱ ጋር የማስታረቅና ወደ እራሱ የመመለስ ሥራ እየሠራ ያለባቸው አመታት ናቸው። ይህንን ሥራውን ሲጨርስስ ምን ይሆናል?

> ስለዚህ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ቀርቶለታል። ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የሚገባ ሁሉ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፣ እርሱም ደግሞ ከሥራው ያርፋል። እንግዲህ ማንም የእነዚያን አለመታዘዝ ተከትሎ እንዳይወድቅ ወደዚያ እረፍት ለመግባት እንትጋ (ዕብ 4፡9-11)።

ይኸ ጥቅስ ከሥራ የሚያርፈው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ሰውም ዕረፍት እንደሚሆን ነው የሚናገረው። ይህ ጥቅስ በዕረፍት የተመሰለው ጽድቅ የሚገኘው በእምነት እንጂ በሥራ እንዳይደለም ነው የሚናገረው። ከአርባ አመታት የምድረ በዳ ጉዞ በኋላ ወደ ተስፋቸው ምድር የገቡት እስራኤላውያን ያገኙት ምድራዊና ጊዜአዊ እረፍት እንጂ ሰማያዊና ዘላለማዊ ዕረፍት ግን ገና እንዳላገኙ ነው የሚናገረው።

እነዚህን ብቻ ግን አይደለም ይኸ ጥቅስ የሚናገረው። በክርስቶስ በማመን በየግላቸው ወደዚያ ዕረፍት የገቡትም ቢሆኑ የሰንበት ዕረፍት ገና በፊታቸው እንዳለላቸው እንዲያውቁትም ሞምር ነው የሚናገረው። እነርሱም ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንዲተጉ ነው የሚመክራቸው። "ትጉ" ሳይሆን "እንትጋ" ነው የሚላቸው። ይህም የሚያመለክተው ወደዚያ የሰንበት ዕረፍት የመልዕክቱን ጸሐፊ ጨምሮ ሁላችንም ገና እንዳልደረስን ነው።

ስድስቱ ቀናት የስድስቱ ሺህ አመታት ጥላዎች ከሆኑ በምድር ላይ የሰው ልጅ ዕድሜ ተፈጽሟል ማለት ነው። ሰባተኛው ቀን የሰንበት ዕረፍት ቀን ነው የሚሆነው። የክርስቶስ መንግሥት ለአንድ ሺህ አመት ምድርን የምታስተዳድርበት ዘመን ነው የሚሆነው ማለት ነው።

> ሰባተኛውም መልአክ መለከቱን (ሰባተኛውን መለከት) ነፋ፤ በሰማይም እንዲህ የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ተሰሙ፤ "የዓለም መንግሥት የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት ሆነች፤ እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል" (ራእ 11፡15)።

ስድስተኛው በዓል

በእስራኤል በየአመቱ የሚከበሩ ሰባት በዓላት አሉ። በጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ ተጠቅሰዋል። በዓላቱ "የእግዚአብሔር በዓላት" ይባላሉ። እነዚህ በዓላት በሙሉ የተገለጠ የጥላነት ጠባይ አላቸው። የፋሲካው በዓል የደህንነት፣ የቂጣው በዓል የቅድስና፣ የበኩራቱ በዓል የትንሳኤ፣ የመከሩ በዓል የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ መውረድ ጥላዎች ነበሩ። ለተቀሩት ለሦስቱም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ አዲስ ኪዳናዊ አካላት አሏቸው።

አዲስ ኪዳናውያኑ አካላት እንደ ብሉይ ኪዳናውያኑ ጥላዎቻቸው ተፈፃሚነታቸው በሦስት ደረጃዎች ነው። የመጀመሪያውን ደረጃ ግለሰባዊ ደረጃ ልንለው እንችላለን። እያንዳንዱ በዓል በእያንዳንዱ እስራኤላዊ ሕይወት ውስጥ በየአመቱ ይፈጸማል። በእነዚህ በዓላት አከባበር ላይ እያንዳንዱ እስራኤላዊ በየአመቱ በነፍስ መከፍ ይካፈላል።

በቀደመው አንቀጽ ውስጥ እንደተወሳው እነዚህ በዓላት በአዲስ ኪዳንም ዘመን በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ ይፈጸማሉ። ወይም ሊፈጸሙ ያስፈልጋል።

ግለሰባዊ ፍፃሜው ጎልቶ የማይታየው ምናልባት የበኩራት በዓል ብቻ ይሆናል። የበኩራት በዓል ግለሰባዊ ፍፃሜውን የሚያገኘው በጌታ ትንሳኤ ነው። ከዚያ ካለፈም ጌታ ነፍሱን በመስቀል ላይ በሰጠ ጊዜ ከመቃብር በተነሱት ሰዎች ሕይወት ይሆናል (ማቴ 27፡ 52-53)። በቀረነው አማኞች ሕይወት ግን በመንፈሳዊ ረገድ ካልሆነ በቀር በሥጋዊ ረገድ ገና ፍፃሜውን አላገኘንም።

ሁለተኛው ደረጃ አስራኤል-ዓቀፋዊ የሆነው ደረጃ ነው። እነዚያ በዓላት የእስራኤል ብሔራዊ በዓላትም ነበሩ። የአማኞች ሁሉ ስብስብ የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም እንደ ግለሰብ ሁሉ በሰባቱ በዓላት ልምምዶች ውስጥ ታልፋለች። ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከዳር እስከ ዳር የቅድስና ንቅናቄ የተጧጧፈበት አስራ ዘጠኝኛው ምዕት ዓመት የቂጣ በዓል ሊባል ይችላል። በጰንጠቆስጤአዊው እንቅስቃሴ በጣም የታወቀው ሃያኛው ምዕት አመት ደግሞ የመከር በዓል ሊባል ይቻላል።

ሦስተኛው ደረጃ ወቅታዊ የሆነው ደረጃ ነው። በጥላነታቸው እነዚያ በዓላት ሁሉ የሚከበሩባቸው የየራሳቸው ወቅቶች ነበሩአቸው (ዘሌ 23፡4)። በአይሁድ ዘመን አቆጣጠር መሠረት የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ በዓላት የሚከበሩት በመጀመሪያው ወር ውስጥ ሲሆን የመጨረሻዎቹ ሦስቱ ደግሞ በሰባተኛው ወር ውስጥ ነው የሚከበሩት። የመከር በዓል ብቻ ነው በሦስተኛው ወር ውስጥ የሚከበረው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደዚህ በተወሰኑ ጊዜአት የሚመጡ እኛ የምናውቃቸው በዓላት የሉም። እኛ የምናውቃቸው በዓላት የሉም ማለት ግን እግዚአብሔርም የሚያውቃቸው የሉም ማለት አይደለም። በየአመቱ ባይመጡም እንኳን ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ በምትቆይበት የእንግድነት ዘመንዋ እርሱ እንዳወቀ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጊዜ ይመጡ ይሆናል።

እነዚያን ወቅቶች የወሰነው እግዚአብሔር እራሱ ነው። ወቅታዊ ከሆነው ከእነዚያ በዓላት አከባበር አንጻር ሲታይ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የምትገኘው በጰንጠቆስጤ በዓል ወቅት አይደለም። በመለከትና ምናልባትም በሥርየት በዓል ወቅት ይመስለኛል። እነዚህ ሁለት በዓላት የምን ጥላ ናቸው?

> እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፦ "ከተቀጠቀጠ ብር ሁለት መለከት አብጅ። ማህበረሰቡን ለመጥሪያ፣ ከሠፈራቸውም እንዲነሱም ለመቀስቀሻ አድርጋቸው። ሁለቱ

> መለከቶች ሲነፉ ማህበረሰቡ በሙሉ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አንተ ዘንድ ይሰብሰብ። ነገር ግን አንዱ መለከት ብቻ ከተነፋ አለቆች . . . አንተ ዘንድ ይሰብሰቡ። መለከቱ ከፍ ባለ ድምፅ ሲነፉ በስተ ምሥራቅ የሰፈሩት ነገዶች ጉዞ ይጀምሩ . . . በግፍ በመጣባችሁ ጠላት ላይ ስትዘምቱ መለከቶቹን ከፍ ባለ ድምፅ ንፉ . . . እንዲሁም በደስታችሁ ቀናት መለከቱን ንፉ . . . በአምላካችሁ ፊት መታሰቢያ ይሆንላችኋል . . . (ዘኍ 10፡1-10)።

መለከት ቢያንስ በአራት ምክንያቶች እንደሚነፋ ነው ከዚህ ክፍል የምናየው። ሕዝቡን በመሪአቸው በሙሴ ዙሪያ ለመሰብሰብ፣ ሕዝቡን ለማስጓዝ፣ በጦርነት ጊዜ በእግዚአብሔር ለመታሰብ፣ እና በደስታቸው ቀናት በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን። ቤተ ክርስቲያን አሁን ያለችበት ወቅት ከቀደመው ከማናቸውም ወቅት ይልቅ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ዙሪያ እየተሰበሰቡ ያሉበት ወቅት ነው። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ኤኪውሜኒካል እንቅስቃሴ የጀመረው ከአስራ ዘጠኝኛው ምዕት አመት መጀመሪያ ገደማ ጀምሮ ቢሆንም፣ "ኤኪውሜኒካል"[1] የሚባለው ቃል ግን መሰማት የጀመረው በሐያኛው ምዕት አመት የመጀመሪያ አጋማሽ ነው።

ይህ እንቅስቃሴ ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶአል። "ካቶሊክ" ወይም "አርቶዶክስ" ወይም "ፕሮቴስታንት" ወይም "ጰንጠቆስጤ" ስለሚሉት ስያሜዎች ብዙዎች ብዙ ግድ የላቸውም። የአስተምህሮ ልዩነቶች ምንም ስሜት አይሰጡአቸውም። ስለ ዲኖሚኔሽን ቀርቶ ስለ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ብዙዎች ብዙ ደንታ የላቸውም። የሚገዳቸው፣ ስሜት የሚሰጣቸው፣ ደንታ ያላቸው ስለ "ክርስቶስ" ብቻ ነው። ቁጥራቸው ጥቂት ያይደለ አብያተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ ምዕመናን እንደዚህ የሆኑት እንደሚገባ ስላልተማሩ ይመስላቸዋል። ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ስላልተማሩ ብቻ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በመለከት በዓል ወቅት ላይ ስለደረሰች ነው።

ስለ "መንፈሳዊ ውጊያ" ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን አሁን በጣም ብዙ የምንሰማው ስለ ምንድነው? በዓለም ዙሪያ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዛሬ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ብዙ መጻሕፍት የሚጻፉት ስለ ምንድነው? የአርነት (ደሊቨራንስ) እንቅስቃሴ የጀመረው በስድሳዎቹ ውስጥ ነው። እንቅስቃሴው በጊዜው በዓለም ዙሪያ በተለይም በጰንጠቆስጤአውያኑ ሰፊር ብዙ ግርግርና ብዙ ግብግብ አስነስቷል። ዛሬ ግን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ረገድ ብዙ አድጋለች። ከአርባ አመታት በፊት ወደማታውቀው አዲስ ልምምድ ውስጥ ገብታለች። ሰይጣንና ርኩሳን መናፍስቱ ከዚያ በፊት አልነበሩም? ነበሩ እንጂ! ቤተ

ክርስቲያንን ተዋግተው፣ ቤተ ክርስቲያንም ተዋግታቸው አታውቅም? ያውቃሉ እንጂ! ታውቃለች እንጂ! ይኸ የመለከት በዓል ወቅት ስለሆነ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሕብረት አምልኮ የሚሰጠውም ትኩረት እንዲሁ ባለፉት አስራ አምስትና ሐያ አመታት ውስጥ ፈጽሞ ተለውጧል። በተለይ ጌታን ለማምለኪያ በተዘጋጀ ቅኔ፣ እጅግ ውብ በሆነ ጣዕመ ዜማ፣ በተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች ቅንብር፣ በአካላዊም እንቅስቃሴ ጭምር፣ ተቀምጦ ሳይሆን ተነስቶ፣ እጆችን አጣጥፎ ሳይሆን ዘርግቶ፣ ዓይኖችን ጨፍኖና በተመስጦ ሆኖ ለሰላሳና ከዚያም በላይ ደቂቃዎች ጌታን ማምለክ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። በዓለም ዙሪያ በከተማና በገጠር ነው እየሆነ ያለው። በአብያተ ክርስቲያንም ሁሉ ዘንድ ነው። ለምን አሁን? ለቤተ ክርስቲያን ይህ የመለከት በዓልዋ ወቅት ስለሆነ ነው።

ስድስተኛው በዓል የስርየት በዓል ነው፦

> የሰባተኛው ወር አስረኛ ቀን የስርየት ቀን ነው። የተቀደሰ ጉባዔ አድርጉ። አንዳች ነገርም አትብሉ። መስዋዕትም በእሳት ለእግዚአብሔር አቅርቡ። በእግዚአብሔር በአምላካችሁ ፊት ለእናንተ ስርየት የሚደረግበት የስርየት ቀን ስለሆነ በዚያ ዕለት ምንም ሥራ አትስሩ። በዚያ ዕለት ሰውነቱን የማያጎሳቁል ማንኛውም ሰው ከወገኖቹ መካከል ተለይቶ ይጥፋ . . . ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ፣ አጎሳቁሉ (ዘሌ 23፡ 27-32)።

"የስርየት ቀን" በመባል ስለሚታወቀው ታላቅ ቀን ነው ይኸ ጥቅስ የሚናገረው። የስርየት ቀን ሕዝቡ ለሠሩት ኃጢአት አመታዊ ስርየት የሚያገኙበት ቀን ነው። ሊቀ ካህኑ በአመት አንድ ጊዜ በታላቅ ፍርሃት እግዚአብሔር ወደ አለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ይገባል። በመጀመሪያ ስለ ራሱና ስለ ቤተሰቡ፣ ቀጥሎም ስለ ሕዝቡ ሁሉ፣ ስለ ቅድስተ ቅዱሳኑ፣ ስለ መገናኛው ድንኳን፣ በስርየት መክደኛው ላይ ደም ይረጫል (ዘሌ 16)። በስርየት ቀን እስራኤል እህል እንዳይበሉ፣ ሰውነታቸውንም እንዲያጎሳቁሉ ታዝዘዋል። ስድስተኛው በዓል ለቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የመጨረሻው በዓልዋ ነው።

ሰባተኛውን በዓል እስራኤላውያን የምድራቸውን ፍሬ ከሰበሰቡ በኋላ ነው የሚያከብሩት (ዘሌ 23፡39)። እስከ ሰሙም "የመከተቻ" ወይም "የዳስ" በዓል ነው የሚባለው። ከበኩራት በዓል ጀምሮ ያሉት አምስቱ በዓላት ከእርሻ ጋር የተያያዙ ናቸው። ሰባተኛው በዓል የሚከበረው ቤተ ክርስቲያን ከምድር ላይ ስትነጠቅ ነው። መንፈሳዊው መከር ተሰብስቦ ሲያበቃ ነው።

ስድስተኛው በዓል ታዲያ የምን ጥላ መሆኑ ነው? የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ከጀመረ ወዲህ ያሉት 480 ምናምን አመታት የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የእግዚአብሔር ማዳን፣ የእግዚአብሔር ምህረት የተገለጠባቸው አመታት ናቸው። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን በተሐድሶ እንቅስቃሴዎችና በሪቫይቫሉች የጎበኘባቸው፣ ቅዱስ መንፈሱን በሚልዮኖች ላይ ያፈሰሰባቸው፣ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በዓለም ሁሉ የተሰበከባቸው አመታት ናቸው።

በአንፃሩ ግን እነዚሁ አመታት ታላላቅ ውድቀቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሰቱባቸው አመታትም ነበሩ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በሉተራውያኑ ላይ ካደረሰችባቸው ስደት፣ እንግልት እና ሞት፣ ሉተራውያኑ በ“ዳግም አጥማቂዎቹ” ላይ ያደረሱት በምን መልኩ ያንሳል? ከዚያ በኋላ የመጣነውም ብንሆን አንዳችን በአንዳችን ላይ ሲቻለን በአካል፣ ሳይቻለን ደግሞ በቃል ያደረስነው ጉዳት ተዘርዝሮ መች ያልቃል?

ያፈጠጠ የዘር መድልዎ በነበረባቸውና አሁንም ባለባቸው ብዙ አገሮች ውስጥ ያሉ ብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን በዘር መድልዎው ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ሆነዋል። በእነዚህ አገሮች ጥቁሮችና የአገሬው ተወላጆች የማይገቡባቸው መኖሪያ ሰፈሮችና መዝናኛ ስፍራዎች ብቻ ሳይሆኑ አብያተ ክርስቲያንም ሞምር ነበሩ።

የዘር መድልዎው ወደ ዘር ማጥፋት ደረጃ ያደገባቸውም አገሮች አሉ። በአውስትራሊያ አቦርጂኖች፣ በኒውዚላንድ ማኦሪዎች፣ በሰሜን አሜሪካ “ቀይ ህንዶች” እና ጥቁር አሜሪካውያን የደረሰባቸውን ማሰብ እንችላለን። ግዙፋን በሆኑት በእነዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች በእነዚያ አገሮች ውስጥ ከነበሩት አብያተ ክርስቲያን ብዙዎች ተሳታፊዎች ሆነዋል።

የዘር መድልዎና የዘር ማጥፋት ነጮች በጥቁሮች ላይ የፈጸሙትና የሚፈጽሙት በደል ብቻ አይደለም። አሁን በሐያኛው ምዕት አመት የመጨረሻ አመታት በሩዋንዳ የታየው የዘር ማጥፋት ጥቁሮች በጥቁሮች ላይ ያደረሱት ነበር። በዚያ የዘር ማጥፋት ወንጀል የብዙዎች ደም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈስሷል። ብዙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እጆቻቸው በሰው ደም በሽቅጠዋል። ዓለማችን የበለጠ ግሎባዊም ጎሣዊም እየሆነች በምትሔድባቸው በፊታችን ባሉት አመታት በቤተ ክርስቲያን ፊት የበለጠ እየተጋረጠ የሚሄደው ተግዳሮት ጎሠኛነት ይሆን ይሆናል።

በሐያኛው ምዕት አመት መጨረሻ ላይ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በገንዘብ ፍቅር፣ በሥልጣን መባለግ፣ በዝሙት ኃጢአቶች

እየወደቁ በዓለም ዙሪያ የብዙ ምዕመናንን አንገት አስደፍተዋል። የእግዚአብሔርን ቃል አስነቀፈዋል። የጌታን ስም አስሰድበዋል። የወንጌልን ሩጫ አሰነካክለዋል። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ስርየት በዓል ወቅት መድረሷን ያመለክታሉ። ስለ ፈፀመቻቸው ስለ እነዚህ ሁሉ ኢክርስቲያናዊ ድርጊቶች በመራራ ኃዘንና በጽኑ ንስሐ በእግዚአብሔር ፊት ልትወድቅ ከሚገባት ወቅት ላይ መሆንዋን ያሳያሉ። በአንዳንድ አገሮችም የብሔራዊ ንስሐ እንቅስቃሴዎች ሊስተዋሉ ጀምረዋል። እንደዚህ ዓይነቶቹ እንቅስቃሴዎች በበለጠ ስፋትና በበለጠም ጥልቀት እንደሚቀጥሉ ይጠበቃል። ምክንያቱም ወቅቱ የስርየት በዓል ወቅት ነውና ነው።

ስድስተኛው ዘመን

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓዋቂዎች የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚያሳልፈውን ጊዜ በሰባት ዘመናት ይከፍሉታል። የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር በሰባት ዘመናት ውስጥ እንደሚያልፍ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚናገረው ነገር ባይኖርም እንኳን ሰባቱ ዘመናት እንዴ ከሌላው ተለይተውና ቁልጭ ብለው ይታያሉ። ሰባቱም ዘመናት በተመሳሳይ ሁኔታ መልካምና አዎንታዊ ጅማሬ አላቸው። በሰባቱም ዘመናት ውስጥ ሰው ለእግዚአብሔር ሊኖረው የሚገባውን ታዛዥነት ይገልጥባቸው ዘንድ የተቀመጡለት መፈተኛዎች አሉ። ሰባቱም ዘመናት በተመሳሳይ ሁኔታ በሰው ውድቀት ይደመደማሉ።

የመጀመሪያው ዘመን አዳምና ሔዋን በኤድን ገነት የኖሩበት ዘመን ነው። “የንጽሕና ዘመን” እየተባለ ይጠራል። ርዝመቱ ምን ያህል እንደነበረ አይታወቅም። በጣም አጭር ሳይሆን እንደማይቀር ግን ይታመናል። ምክንያቱም ሰው በኤድን ገነት በተድላና በደስታ ሲኖር ሰይጣን ለረኅም ጊዜ ዝም ብሎ ተመልከቶታል ብሎ ለማሰብ ስለሚያስቸግር ነው።

ሁለተኛው ዘመን አዳምና ሔዋን ከኤድን ገነት ከተባረሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ ጥፋት ውሀ ድረስ ያለው ነው። “የሕሊና ዘመን” ይሉታል። ከሁለተኛው እስከ አምስተኛው ድረስ ያሉት ዘመናት ዕድሜ ይታወቃል። ሦስተኛው ዘመን ከጥፋት ውሀ በኋላ እግዚአብሔር ለኖህ ቃል ኪዳን ሲገባለት ይጀምርና አብራም እስከ ተጠራበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል። “የሰው መንግሥት ዘመን” ይባላል። አራተኛው ከአብራም መጠራት አንስቶ ሀግ እስከ ተሰጠበት ጊዜ ያለው ሲሆን “የተስፋ ዘመን” ይሰኛል። አምስተኛው “የህግ ዘመን” የሚባለው ሲሆን ለእስራኤል ልጆች በሲና ወይም

በኮሬብ ተራራ ህግ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጌታ ሞትና ትንሳኤ ያለው ጊዜ ነው።

ስድስተኛው አሁን ያለንበት ዘመን ነው። ይኸ ዘመን ከዘመናቱ ሁሉ በጣም ረዥሙ ነው። እስከ አሁን ከ1970 አመታት በላይ አስቆጥሮአል። ይህ ዘመን መቼ እንደሚያበቃ በትክክል ባይታወቅም አሁን ያለነው በመጠናቀቂያው ላይ እንደሆነ አስረግጠን እናውቃለን። ስድስተኛው ዘመን "የጸጋ" ወይም "የምህረት" ወይም "የቤተ ክርስቲያን" ወይም "የመንፈስ ቅዱስ" ዘመን እየተባለ በተለያዩ ስሞች ይጠራል። በጌታ ደቀ መዛሙርት ላይ መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ከወረደበት ከጰንጠቆስጤ ቀን አንስቶ እስከ ጌታ ዳግም ምፅአት ድረስ ይዘልቃል።

ሰባተኛውና የመጨረሻው ዘመን "የአንድ ሺህ አመቱ የክርስቶስ መንግሥት" በመባል የሚታወቀው ዘመን ነው። ይኸ ዘመን ጌታ ዳግም ከመጣ በኋላ የሰው ልጅ በምድር ላይ የሚኖረው የመጨረሻው አንድ ሺህ አመት ነው። ከእነዚህ ሰባት ዘመናት በፊትና በኋላ "ያለፈው ዘላለም" እና "የሚመጣው ዘላለም" ይገኛሉ።

ምልክቶቹ

ከመጀመሪያው የጌታ ወደ ምድር መምጣት ጋር የተያያዙ በቁጥር ወደ 300 የሚሆኑ ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አሉ ይባላል። ስለሚወለድበት ጊዜ፣ ስለሚወለድበት ቦታ፣ ከሴት እንደሚወለድ፣ ከድንግል ሴት እንደሚወለድ፣ ከይሁዳ ነገድ እንደሚወለድ፣ ከእሴይ ዘር እንደሚወለድ፣ ስለ አገልግሎቱ፣ ስለ ሕማማቱ፣ ስለ ሞቱና ስለ ትንሳኤው ዝርዝር ጉዳዮች ተተንብየዋል። የተተነበዩ ትንቢቶችም ሁሉ አንድ በአንድ በትክክል ተፈጽመዋል። እነዚህን ያህል ብዙ ትንቢቶች በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ በአጋጣሚ ሊፈፀሙ እንደማይችሉ የፕሮባቢሊቲ ሕግ ያረጋግጣል።

በትንቢቶቹና በትክክል በመፈጸማቸውም እጅግ የተደነቁ አንዳንድ ተመራማሪዎች ትንቢቶች የተባሉት በእውነት ትንቢቶች ሳይሆኑ ድርጊቶቹ ከተፈፀሙ በኋላ የተጻፉ መሆን አለባቸው እስከ ማለት ደርሰዋል። ዳሩ ግን ይህም የሚያስኬዳቸው ሆኖ አልተገኘም። ለምን? ቢባል እነዚህን ትንቢቶች የያዙና ከጌታ ልደት ብዙ አመታት ቀደም ሲል የተጻፉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዚህ በሐያኛው ምዕት አመት ከየዋሻው ተገኝተዋልና።

ስለ መጀመሪያው የጌታ መምጣት ከተነገሩት ትንቢቶች ስለ ሁለተኛው መምጣቱ የተነገሩት በስምንት እጥፍ ይበልጣሉ ይባላል። እኛን የዛሬዎቹን የበለጠ ሊያሳስበን የሚገባው ይኸ ነው። ስለ መጀመሪያው አመጣጡ እንደዚያ በዝርዝር የሚያወሱት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በእጃቸው ውስጥ የነበሩላቸው ብዙ አይሁዳውያን ጌታ በመጣ ጊዜ ሳያውቁትና ሳይቀበሉት ቀሩ። እግዚአብሔር ካልረዳንና እኛም ካልተጠነቀቅን በስተቀር ስለ ሁለተኛው አመጣጡ በበለጠ በዝርዝር የሚያወሱት የአዲስ ኪዳን መጻህፍት በእጃችን ያሉልን እኛም ተመሳሳይ አደጋ ሊደርስብን ይችላል።

ስለ ጌታ ዳግም ምጽአትና ስለ ዘመኑ አጨራረስ የተጻፉት ትንቢቶች በሦስት ይከፈላሉ። በመጀመሪያ እስራኤልን በተመለከተ የተጻፉ ትንቢቶች አሉ። ቀጥሉም ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ ትንቢቶች አሉ። በመጨረሻም ከእስራኤልም ከቤተ ክርስቲያንም ያልሆኑትን የቀረውን ዓለም የሚመለከቱ ትንቢቶች አሉ። ስለ ጌታ ዳግም ምጽአትና ስለ ዘመኑ አጨራረስ የሚናገሩትን ትንቢቶች በዚህ ዓይነት ከፋፍለን ብንመረምራቸው ከብዙ ግራ መጋባት እንተርፋለን። በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የመጨረሻውን ዘመን መጨረሻ በተመለከተ ከተጻፉልን ከሦስቱ ዓይነት ትንቢቶች ውስጥ በናሙናነት አንድ አንድ ብቻ እንመለከታለን።

እስራኤል

ታላቁ ፍሬደሪክ የቤተ መንግሥቱን ቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ የማያዳግም ማስረጃ በአንድ ቃል ብቻ እንዲሰጠው ጠየቀው ይባላል። ቁሱም "ግርማዊ ሆይ! አይሁድ!" በማለት መለሰለት[2]። የአይሁድን ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሌሎችም የታሪክ መጻሕፍት በጥንቃቄ በመመርመር ብቻ ብዙ ሰዎች የእስራኤልን አምላክ ወደ ማወቅ ደርሰዋል። ስለ ዘመኑ አጨራረስ የተነገሩ አያሌ ትንቢቶችንም ለመፍታት እስራኤል ቁልፍ ናት።

> . . . ልትወርሷት ከምትገቡባት ምድር ትነቀላላችሁ። ከዚያም እግዚአብሔር ከአንዱ የምድር ዳርቻ እስከ ሌላው ዳርቻ በሕዝቦች ሁሉ መካከል ይበትንሃል . . . በእነዚያም ሕዝቦች መካከል ዕረፍት አታገኝም . . . (ዘዳ 28፡63-65)።

ይህንን ትንቢት ሙሴ ሲናገርባቸው እስራኤላውያኑ ገና ወደ ከነዓን ምድር አልገቡም። ዘመኑ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1450 አመት ገደማ ይሆናል። የአሦር መንግሥት አስሩን ነገደ እስራኤል ከምድራቸው ባፈለሰ ጊዜ ይኸ ትንቢት ሊፈፀምባቸው ጀመረ።

ከተነገረ ከ728 አመት ገደማ በኋላ ማለት ነው። በ586 ኢየሩሳሌም ስትሰበርና ሰሎሞን ያሠራው ቤተ መቅደስ ሲፈርስ ስለ እስራኤል መበተን የተነገረው የሙሴ ትንቢት ተጠናቀቀ።

ነገር ግን ሙሴ የተነበየው ስለ እስራኤል መበተን ብቻ ሳይሆን እንደገና ስለ መሰብሰብዋም ጭምር ነበር፦

> . . . አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልስልሃል፣ ይራራልሃልም። አንተን ከበተነበት አህዛብ መካከል እንደገና ይሰበስብሃል። ከሰማይ በታች እጅግ ሩቅ ወደ ሆነ ምድር ብትጋዝ እንኳን አምላክህ እግዚአብሔር ከዚያ ይሰበስብሃል። መልሶም ያመጣሃል። የአባቶችህ ወደ ሆነችው ምድር ያመጣሃል። አንተም ትወርሳታለህ (ዘዳ 30:3-5)።

ይኸ ትንቢት ሙሉ ፍጻሜውን ሊያገኝ የጀመረው አሁን በእኛ ዕድሜ ማለትም በ1948 ነፃና ሉዓላዊ የሆነ የእስራኤል መንግሥት ሲመሠረት ነው። እስከዚያ ጊዜ ድረስ የነበሩት አመታት ሁሉ የገዘርውት እስራኤል (የእስራኤል ዳያስፖራ) አመታት ነበሩ። ይህንን የእስራኤልን እንደገና መሰብሰብና የመንግሥትዋንም እንደገና መመሥረት ጌታ ለዳግም ምፅዓቱ ቁልፍ ምልክት አድርጎ ጠቅሶታል።

> ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ሚፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ። እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ ዕ ወቁ። እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይኸ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ ቃሌ ግን አያልፍም (ማቴ 24:32-35)።

ጌታ ይህንን የተናገረው "የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱ ምንድነው?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ነው (24:3)። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የሰጣቸው ምልክቶች ብዙ ናቸው። ነገር ግን "የሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ" እንደሚባለው ለምልክቶቹ ሁሉ ማሰሪያ የሚሆነው እስራኤል ሉዓላዊት መንግሥት ሆና እንደገና መመሥረትዋ ነው።

የበለስዋ ዛፍ ምልክትነት እንዲያው በተራ ምሳሌነት የቀረበ ሊሆን አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የበለስ ዛፍ የእስራኤል ምሳሌ ሆና በተደጋጋሚ ተጠቅሳለች (ሆሴ 9:10፤ ናሆ 3:12)። ጌታ ስለ በለስዋ ዛፍ ማቆጥቆጥ ከመናገሩ በፊት ስለ በለስዋ ዛፍ ያስጨበጠን ሌላ ግንዛቤም አለ፦

> ደግሞም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ ተናገረ። አንድ ሰው በወይኑ እርሻ ቦታ የተተከለች አንዲት የበለስ ተክል ነበረችው። እርሱም ፍሬ ሊፈልግባት መጥቶ ምንም

> አላገኘም። የወይን አትክልት ሠራተኛውንም እነሆ ፍሬ ልፈልግባት ሦስት አመት ወደዚህች በለስ መጥቼ ምንም አላገኘሁም። ስለዚህ ቁረጣት፤ ለምን አፈሩን ታሚጥጣለች? አለው። እርሱ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት፦ ጌታ ሆይ፣ ዙሪያዋን እስክቆፍርላትና ፍግ እስክማደርግላት ድረስ ለዘንድሮ ብቻ ተዋት። ለከርሞ ካፈራች መልካም ነው፣ አለበለዚያ ትቆርጣታለህ (ሉቃ 13:6-9)።

ይህንን የሚመስል ሌላም ምሳሌ ጌታ ተናግሮአል (ማቴ 21:33-41)። የሉቃሱን ምሳሌ የተናገረው ስለ ፍሬ ቢስዋ የበለስ ዛፍ ሲሆን የማቴዎሱን ምሳሌ የተናገረው ግን ስለ ፍሬ ቢሶች ገበሬዎች ነው። ሁለቱም ምሳሌዎች እስራኤል በዚያን ጊዜ የነበረችበትን ሁኔታ ነው የሚያሳዩት። "የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም ምሳሌዎቹን ሰምተው ስለ እነርሱ እንደ ተናገረ አስተዋሉ" ይላልና። ፍሬ ቢሶቹን ገበሬዎች ስለ ጥፋታቸው ፍርዱን እራሳቸው እንዲሰጡ አድርጓቸዋል። ስለ በለስዋ ዛፍ ይህንን የመሰለ ዳራ ከሰጠን በኋላ ነው የራሱን ፍርድ ያስታወቀን።

> ኢየሱስ በማግሥቱ ማለዳ ወደ ከተማይቱ በመመለስ ላይ ሳለ ተራበ። በመንገድ ዳርም አንድ የበለስ ዛፍ አይቶ ወደ እርስዋ ሲሄድ ከቅጠል በስተቀር ምንም ስላላገኘባት ከእንግዲህ ፍሬ አይኑርብሽ አላት። የበለሷም ዛፍ ወዲያውኑ ደረቀች . . . (ማቴ 21:18-19)።

እስከ አሁን በራስዋ ምርጫ ፍሬ ቢስ የነበረችው የበለስ ዛፍ ከእንግዲህ ወዲህ ከጌታ ፍርድ የተነሳ ፍሬ ቢስ ትሆናለች። ትደርቃለችም። መድረቅዋም ሆነ ፍሬ ቢስነትዋ ግን ጊዜያዊ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ዛፍዋ ተቆረጠች እንጂ ፈጽሞ አልተነቀለችም። በተቆረጠችም ጊዜ ጉቶዋ ሕያው ሆኖ በመሬት ውስጥ እንዲቀር ተደርጋ ነው የተቆረጠችው። ይህ ፍርድ መጀመሪያ በኢሳይያስ አማካይነት በተነገራትም ጊዜ እንደዚሁ ተብሎ ነበር የተነገራት፦

> ነገር ግን የኮመበልና የዋርካ ዛፍ በተቆረጠ ጊዜ ጉቶ እንደሚቀር፣ ቅዱሱም ዘር እንዲሁ በምድሪቱ ጉቶ ሆኖ ይቀራል (ኢሳ 6:13)።

ስለሆነም የተቆረጠችውና የደረቀችው የበለስ ዛፍ ከረዥም ዘመን በኋላ አቆጠቆጠች። ማቆጥቆጥዋም ለመጨረሻው ዘመን መጨረስ ቁልፍ ምልክት መሆኑ ለእኛ ተነገረን። ይህም ንግርት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ትምህርት ነው። እስራኤል ዳግመኛ የምትሰበሰበው የዓለምን መንግሥታት በሙሉ ወደማይወጡትና ወደማይፈቱት የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ለመክተት ነው። እስራኤል ዳግመኛ የምትሰበሰበው የራስዋንም ለዘመናት የተጠራቀመ ኃጢአት በተመለከተ

የመጨረሻ ፍርድዋን ልትቀበል ነው። እስራኤል ዳግመኛ የምትሰበሰበው የዓለምን ታሪክ ሂደት ለንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ለማመቻቸት ነው።

> የነገርኩህን ቃል ሁሉ በመጽሐፍ ፃፍ። እነሆ የሕዝቤን የእስራኤልንና የይሁዳን ምርኮ የምመልስበት ዘመን ይመጣልና . . . ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠኋት ምድር እመልሳቸዋለሁ፤ እነርሱም ይገዝፁታል . . . ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና፤ እርሱንም የሚመስል የለምና፤ ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው፤ ነገር ግን ከእርሱ ይድናል . . . በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል . . . ቀንበርህን ከአንገትህ እሰብራለሁ፤ እስራትህንም እበጥሳለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህም ለሌላ አትገዛም፤ ለአምላካቸው ለእግዚአብሔርም ፤ ለማስነሳላቸው ለንጉሣቸው ለዳዊትም ይገዛሉ እንጂ ሌሎች አህዛብ እንደገና አይገዙአቸውም (ኤር 30፡1-9)።

በጣም ግልጽ የሆነ ትንቢት ነው። ስላለፈው ከአሦር ወይም ከባቢሎን ምርኮ ስለ መመለሳቸው አይደለም እዚህ ላይ ኤርምያስ የሚናገረው። በቀደመው መመለሳቸው ጊዜ በምድራቸው ላይ ያውም ለተወሰነ ጊዜ ያውም በቅኝ ተገዥነት ኖሩ እንጂ ምድራቸውን የመግዛት መብትና ሥልጣን አልነበራቸውም። የዚህኛው መመለሳቸው ጊዜ የሚመስለው የሌለ የመከራ ጊዜ ይሆናል። ሆኖም አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከባዕድ አገዛዝ ነፃ ይወጣሉ። ለእግዚአብሔርና ለንጉሣቸው ለዳዊት ይገዛሉ። ዳዊት የተባለው ንጉሣቸው "የዳዊት ልጅ" ክርስቶስ ነው።

> እነሆ በዚያ ወራትና በዚያ ዘመን የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ አህዛብን ሁሉ ሰብስቤ ወደ ኢዮሣፍጥ ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ፤ በዚያም . . . እፈርድባቸዋለሁ (ኢዩ 3፡1-2)።

ይህም ሌላው በጣም ግልፅ የሆነ ትንቢት ነው። እስራኤል ዳግመኛ ስትሰበሰብ ዓለም በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ መግባት ይጀምራል። የእስራኤል መንግሥት ከተመሠረተ ወዲህ ያሉት ሃምሳ ምናምን አመታት የመካከለኛው ምስራቅ ቀውስ እየሰፋና እየከረረ የመጣባቸው ናቸው። መስፋቱም ሆነ መክረሩ አህዛብን ሁሉ ወደ አርማጌዶን ጦርነት እስከሚያደርሳቸው ድረስ እንደሚቀጥል ነው ትንቢቱ የሚናገረው። "የኢዮሣፍጥ ሸለቆ" የተባለው ቦታ አርማጌዶን በመባል የሚታወቀው ነው። የፍርድ ጊዜ በግልባጩ የሪቫይቫል ጊዜም እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል።

ስድስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን

በራእይ ዮሐንስ መጽሐፍ ውስጥ የተካተተው መልዕክት የተላከው በመጀመሪያው ምዕት አመት መጨረሻ ላይ በእስያ ጠቅላይ ግዛት ይገኙ ለነበሩ ሰባት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ነው (1፡4-5)። እነዚያም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን በስም ተጠቅሰዋል (1፡11)። በመጀመሪያው ምዕት አመት መጨረሻ በምድር ላይ የነበሩት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን እነዚያ ሰባቱ ብቻ አልነበሩም። በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በስም የምናውቃቸው ሌሎች ብዙ ነበሩ። በስም ያልተጠቀሱና እኛም ያላወቅናቸው ይኖራሉ። ታዲያ ይህ መልዕክት ለምን ለሰባቱ ብቻ ተላከላቸው?

ሰባት የምልዓት ቁጥር ስለሆነ ነው። እነዚያ ሰባት አብያተ ክርስቲያን የተመረጡባቸው ሁለት ሌሎች ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ናሙናዊ (sample) የሆነው ምክንያት ነው። እነዚያ ሰባት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ የሚኖሩትን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ይወክላሉ። በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን ሁሉ ውስጥ የሚኖረው ደካማና ጠንካራ ጎን በእነዚያ በሰባቱ ውስጥ በዚያን ጊዜ ተንጸባርቋል። ስለሆነም መልዕክቱ እነዚያን ሰባቱን ጨምሮ ለአብያተ ክርስቲያን ሁሉ ነው። "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ" የሚለው በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕራፎች ውስጥ ሰባት ጊዜ ተደጋግሞ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሚያረጋግጥልን ይህንኑ ሐቅ ነው።

ሁለተኛው ወቅታዊ (periodic) የሆነው ምክንያት ነው። ሰባቱ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን በቤተክርስቲያን ዘመን ውስጥ ሰባት የተለያዩ ወቅቶችን (periods) እንዲያመለክቱ ሆነው በጥንቃቄ ነው የተመረጡት። በመጽሐፉ ውስጥ በቀጥታ እንደዚህ ተብሎ የተጠቀሰ ነገር የለም። ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ግንዛቤ እንድናገኝ የሚያደርገን መጽሐፉ እራሱ ነው። ለምሳሌ ባለ ራእዩ ዮሐንስ "ያየኸውን፣ አሁን ያለውን፣ ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ፃፍ" ተብሎ እንደታዘዘ ይነግረናል። (1፡19)።

የራእይ ዮሐንስን መጽሐፍ ለመረዳት ይኸ ቁልፍ የሆነ ጥቅስ ነው። ዮሐንስ እንዲጽፍ የታዘዘው ሦስት ነገሮችን ነው። አንደኛ "ያየውን"። ይኸ በመጀመሪያው ምዕራፍ በመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቁጥሮች ውስጥ የተጻፈልንን ያጠቃልላል። ሁለተኛ "አሁን ያለውን"። ይኸ ባንድ በኩል በስም በተጠቀሱት በሰባቱ አብያተ ክርስቲያን ውስጥ በዚያን ጊዜ ያለውን በጎና ክፉ ነገር ማለት ሲሆን

በሌላ በኩል ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ በአብያተ ክርስቲያን ሁሉ ውስጥ የሚኖረውን በጎና ክፉ ነገር ማለት ነው። ምዕራፍ ሁለትና ሦስት በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

ሦስተኛው "ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን" የተባለው ነው። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ካበቃ በኋላ ያለውን ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች ወይም ከምድር ላይ ከተወሰደች በኋላ የሚሆነውን ማለት ነው። ከአራተኛው ምዕራፍ መጀመሪያ አንስቶ እስከ መጽሐፉ መጨረሻ ድረስ ያለው ሁሉ በዚህ በሦስተኛው ውስጥ ይካተታል። ስለዚህኛው ለመጻፍ ሲጀምር ዮሐንስ "ከዚህ በኋላ እነሆ በሰማይ የተከፈተ በር አየሁ" በማለት ነው የሚጀምረው። ከዚያም "ወደዚህ ና፣ ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚገባውን ነገር አሳይሃለሁ አለኝ" ይላል (4፡1)። "ወደዚህ ና" ማለት በሰማይ ወደተከፈተው በር ማለት ነው።

እስከ አሁን ድረስ በምድር ላይ ሆኖ በምድር ላይ ሲሆን የሚያየውን ነገር ነበር ሲዘግብልን የነበረው። ከእንግዲህ በኋላ ግን ዮሐንስም ለቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በናሙናነት የሚያገለግል ይመስላል። ከእንግዲህ በኋላ በሰማይ ላይ ሆኖ በሰማይና በምድር ላይ ሲሆኑ የሚያያቸውን ነገሮች ነው እየተከታተለ የሚዘግብልን። እንዴት ነው "በሰማይ ላይ" የሆነው? በአካል አልነበረም። በመንፈስ ነው። "እኔም ወዲያውኑ በመንፈስ ነበርኩ" ሲል ይሆንን ማለቱ ነው (4፡2)።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያንን በምድር ላይ አያያትም። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ አስራ ዘጠኝ ጊዜ በስም ጠርቷት ነበር። ከዚህ በኋላ ግን አንድ ጊዜም አይጠራትም። ይልቁንም በሰማይ ስለሚያያቸው ዙፋኖች፣ አክሊል ስለ ደፉ ሰዎች ይነግረናል። ስለ እግዚአብሔር ፈጣሪነት፣ የታረደው በግ በደሙ ስለ ዋጃቸው ሰዎች ፍጥረት ሁሉ ሲዘምረው የሚሰማውን ቅኔ ይነግረናል (4-5)። ምድር በሰባት ማህተሞች፣ በሰባት መለከቶችና በሰባት ፅዋዎች በተመሰሉ ፍርዶች በተከታታይ ስትመታ ያሳየናል (6-18)። አቀራረቡም ፍርዶቹን በመርዶነት ሳይሆን በምሥራችነት እንድናያቸው ነው የሚጋብዘን።

ይህንን ሁሉ ሐተታ ያተትኩት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን በስድስተኛው ዘመን ማለትም በቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ የሚገኙ ሰባት የተለያዩ ወቅቶችን ያመለክታሉ ላልኩት ነገር ለምሰጠው ማብራሪያ መግቢያ እንዲሆነኝ ነው። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ኤፌሶን ናት። ይህች ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዋን ምዕት አመት ቤተ ክርስቲያን ታመለክታለች። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን መለያ ፍቅር ነበር።

በምዕት አመቱ መጠናቀቂያ ላይ ግን ያ ፍቅር መቀዝቀዝ ጀምሮ ነበር (2፡4)።

ሁለተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ሰምርኔስ ናት። ይህች ቤተ ክርስቲያን የምታመለክተው ከመጀመሪያው ምዕት አመት መጨረሻ አንስቶ እስከ 313 ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው፣ ይህ ዘመን ታላቁ ቁስጠንጢኖስ በሮም መንግሥት ግዛት ሁሉ የሃይማኖት ነፃነት ከማወጁ በፊት ያለው ነው። ያ ወቅት ለቤተ ክርስቲያን የታላቅ ስደትና መከራ ወቅት ነበር። ሰምርኔስ ማለት ከርቤ ማለት ነው። ከርቤ መራራ ነው። የመከራም ምሳሌ ነው።

ሦስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ናት። የጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ከ313 እስከ 500 ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ታመለክታለች። ያ ዘመን ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት፣ ፖለቲካና ክርስትና በፍቅር መዳራት የጀመሩበት ዘመን ነው። ቄሳሩ እራሱ፣ እርሱንም ተከትለው መሳፍንቱና መኳንንቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡበት ጊዜ ነው። ጎጢአተኛነታቸው ሳይገባቸው፣ ከጎጢአታቸውም ንስሐ ሳይገቡ፣ ሕይወታቸውንም በየግላቸው ስለ ጎጢአታቸው ለሞተላቸው ለክርስቶስ ሳይሰጡ፣ እንዲያው ተግተልትለው በጅምላ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑበት ዘመን ነው። እውነተኛው ወንጌል የ"በለዓም" እና የ"ኒቆላውያን" በተሰኙ የኑፋቄ ትምህርቶች ሊቀየጥ የጀመረበት ነው (2፡14-15)።

አራተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ናት። የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን የምታመለክተው ከ500 እስከ 1500 ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው ይህ ዘመን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ የገነነችበት ነው። የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን በጴርጋሞን የተጀመረው የፖለቲካና የክርስትና መዳራት ያስከተለው ውጤት ናት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ዓይነት ምዕመናን መኖራት የሚጀምሩት በትያጥሮን ነው (2፡24)።

አምስተኛዋ የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህችን ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል በሌላ ምዕራፍ ውስጥ አይተናታል። የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን ከ1500 እስከ 1750 ገደማ ድረስ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ዘመን ታመለክታለች። ሰርዴስ ማለት "ቅሬታ" ወይም "ትሩፋን" ማለት ነው ይላሉ። በሰርዴስም ሁለት ዓይነት ምዕመናን አሉ (3፡4)።

ስድስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ናት (3፡7-13)። የዚህኛው ንውስ ርዕሳችን ጉዳይ ይህች ቤተ ክርስቲያን ናት።

የምታመለክተው ከአስራ ስምንተኛው ምዕት አመት አጋማሽ ገደማ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ባላቋረጠ የተሐድሶና የሪቫይቫል እንቅስቃሴ ውስጥ እያለፈች ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ነው።

የዚህች ቤተ ክርስቲያን ዋኛ መለያ ዓለም አቀፍ የሆነ የወንጌል ስርጭት ነው። "... ማንም ሊዘጋው የማይችል የተከፈተ በር በፊትህ አድርጌአለሁ" ተብሉላታል (3:8)። በጌታ ቅዱስ መንፈስ ባለማቋረጥ እየተሞላች፤ በመለኮታዊ ፍቅሩ እየተቀጣጠለች፤ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት በቅድስና እየተመላለሰች፤ ቀለም፣ ቋንቋና ዘር ሳትለይ የክርስቶስን ወንጌል ለሰው ልጆች ሁሉ ታብስራለች። የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን በጌታ የተወደደች ናት (3:9)። ፊላደልፍያ ማለት "የወንድማማች ፍቅር" ማለት ነው። ይህም የሚያሳየው በፊላደልፍያ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ወደ መጀመሪያው መለያዋ (ፍቅር) በመመለስ ላይ ያለች መሆንዋን ነው።

የፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ሌላው መለያዋ የምትነጠቀው ቤተ ክርስቲያን መሆንዋ ነው። "... በምድር ላይ የሚኖሩትን ሊፈትናቸው በዓለም ሁሉ ላይ ከሚመጣው የፈተና ሰአት እጠብቅሃለሁ" ተብሉላታል (3:10)። ስለዚህም የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የመጨረሻዋ ቤተ ክርስቲያን ናት። እስከ አሁን ድረስ ለ250 አመታት ያህል በምድር ላይ ቆይታለች። ከእንግዲህስ በኋላ ለምን ያህል ጊዜ ትቆይ ይሆን? ያለ ጥርጥር ለረዥም ጊዜ አይሆንም። ምክንያቱም "እነሆ፣ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ" ተብሉላታል (3:11)። ትያጥሮን "... እስክመጣ ድረስ" ነበር የተባለችው (2:25)። ሰርዴስ ደግሞ "እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ፤ በየትኛውም ሰዓት እንደምመጣብህም አታውቅም" ነው የተባለችው (3:3)። ፈዝዘሃል፣ አንቀላፍተሃል፣ ንቃ፣ ለማለት ነው። የሰባቱም አብያተ ክርስቲያን ባህርያት በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ቢሆንም እንኳን፣ አሁን ያለነው ግን በፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍፃሜ ላይ መሆኑ አያጠያይቅም።

ሰባተኛዋ ቤተ ክርስቲያን የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህች ቤተ ክርስቲያን ከፊላደልፍያ ጋር በጉርብትና፣ ጎን ለጎን፣ አብራ የምትኖር ሳትሆን አትቀርም። ክርስቶስ በደጅዋ እንጂ በውስጥዋ የለም (3:20)። ቤተ ክርስቲያንን እያከታተለ በማጥለቅለት ላይ ያለው የተሐድሶና የሪቫይቫል እንቅስቃሴ አልነካትም። ቀዝቃዛም ትኩስም አይደለችም። ከሐዲም ክርስቲያንም አይደለችም ማለት ይመስለኛል። በርዋን ከፍታ ጌታን ወደ ውስጥዋ ካላስገባችው በስተቀር የፊላደልፍያ ቤተ ክርስቲያን የምታመልጠውን፣ በዓለም ሁሉ የሚመጣውን ፈተና የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ትገባበታለች።

ይኸ በዓለም ሁሉ ላይ የሚመጣ የተባለው ፈተና "ታላቁ መከራ" እየተባለ የሚጠራው ነው። በሺዩ ዳንኤል ሰባኛ ሱባኤ ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ነው የሚሆነው (ዳን 9:27)። የታላቁ መከራ ጊዜ ሦስት ተኩል አመታት ወይም አርባ ሁለት ወራት እንደሚሆን ዳንኤልም፣ ዮሐንስም አስታውቀውናል (ዳን 7:25፣ ራእ 12:14፤ 13:5)። ይኸ ጊዜ "የያዕቆብ መከራ ዘመን" ተብሉ የተጠቀሰው ዘመን ነው። ዳንኤልም፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደዚያ ያለ መከራ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዚያ ጊዜ ደረስ ሆኖ እንደማያውቅና ከዚያም በኋላ እንደማይሆን አስተምረውናል (ዳን 12:1፤ ማቴ 24:21)። በዚያም ዘመን ቢሆን ወንጌል ይሰበካል። "ከታላቁ መከራ የመጡ" የሚባልላቸው ዕልፍ አእላፍ ቅዱሳንም አሉ (ራእ 7:13)። ከእነዚያም ብዙዎቹ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የነበሩ ሳይሆኑ አይቀሩም።

የቀረው ዓለም

"የአረማውያን ዘመን" በመባል የሚታወቅ ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ (ሉቃ 21:24)። የአረማውያን ዘመን እስራኤላውያን በጦርነት ድል ሆነውና ምርኮኞች ተደርገው ወደ ዓለም ሁሉ የተበተኑበት ዘመን ነው። ዋና ከተማቸው ኢየሩሳሌምም ከአረማውያን መንግሥታት ሥልጣን ስር የወደቀችበት ዘመን ነው። ቀደም ሲል በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ እንዳየነው ይሁዳ በባቢሎናውያን ሊማረክና ኢየሩሳሌምም በባቢሎናውያን ልትረገጥ የጀመረችው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ606 አመት ላይ ነበር። ሆኖም ኢየሩሳሌም ፈጽማ የወደቀችው በ586 ነው። የእስራኤል መንግሥት የተመሠረተው በ1948 ቢሆንም ኢየሩሳሌም ግን ሙሉ በሙሉ በዚያ መንግሥት ቁጥጥር ስር የሆነችው በ1967 የስድስቱ ቀን ጦርነት ጊዜ ነው። ስለሆነም "የአረማውያን ዘመን" ከ2553 አመታት በኋላ ጁን 10 ቀን 1967 አብቅቷል።

ከእንግዲህ ወዲህ የእስራኤል ሉዓላዊ መንግሥት ምንም ዓይነት አደጋ አያጋጥመውም? ኢየሩሳሌምስ ከእንግዲህ ወዲህ በምንም ዓይነት በሌላ መንግሥት ሥልጣን ስር አትወድቅም? የእስራኤል መንግሥት በእርግጥ አደጋ ያጋጥመዋል። በኢየሩሳሌምም ላይ የእስራኤል መንግሥት ብቸኛው ባለ ሥልጣን የማይሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። እንዲያውም ዝዩዩ ዘካርያስ እንደሚለው፦

> ኢየሩሳሌምን እንዲወጉ አሕዛብን ሁሉ እሰበስባለሁ፤ ከተማይቱ ትያዛለች፤ ቤቶች ይበዘበዛሉ፤ ሴቶችም ይደፈራሉ፤ የከተማይቱም እኩሌታ ይማረካል፤ የሚቀረው ሕዝብ ግን ከከተማይቱ አይወሰድም (14:1-2)።

ሆኖም ያ የጦርነት ጊዜ ነው። የእስራኤል መንግሥት ዳግመኛ ከተመሠረተ በኋላ ያለው ጊዜ ደግሞ የማያባራ ጦርነት ጊዜ ነው። ነገር ግን ዳግመኛ የተመሠረተው የእስራኤል ሉዓላዊ መንግሥት እንደገና እንደ ቀድሞው ከታሪክ ላይ የሚፋቅበት ሁኔታ አይኖርም። እንደዚያ ያለውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ "የአረማውያን ዘመን" በተባለው ውስጥ የሚያካትተው አይመስልም። ከዚህ የማያባራ ጦርነት በአንደኛው ላይ፦

> እግዚአብሔር በጦርነት ጊዜ እንደሚዋጋ እነዚያን አህዛብ ሊወጋ ይወጣል። በዚያን ቀን እግሮቹ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይቆማሉ . . . (ዘካ 14፡3-4)።

እናም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያ የመጨረሻው ጦርነት ይሆናል። ከደብረ ዘይት ተራራ ላይ ክብር ጌታ ወደ ሰማይ የዓረገው (የሐዋ 1፡12)። በዳግም ምፅአቱም ጊዜ የደብረ ዘይትን ተራራ ነው በመጀመሪያ የሚረግጠው።

የአረማውያንን ዘመን ለመረዳት በእጅጉ የሚጠቅሙ ሁለት አስደናቂ ሕልሞች በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ አሉ። አንደኛውን ሕልም (ዳን 2) ያየው የባቢሉን ንጉሥ ናቡከደነፆር ሲሆን፤ ሁለተኛውን ሕልም (ዳን 7) ደግሞ ያየው ዳንኤል ነው። ሁለቱ ሕልሞች የተለያዩ ቢመስሉም ፍቻቸው ተመሳሳይ ነው። በእነዚያ ሕልሞች መሠረት በእስራኤልና በኢየሩሳሌም ላይ የሚሰለጥኑ የአረማውያን መንግሥታት በቁጥር አራት ብቻ ናቸው። እነርሱም የባቢሉን፤ የሜዶንና ፋርስ፤ የግሪክና የሮማ መንግሥታት ናቸው።

አራተኛው መንግሥት መሲህ (ክርስቶስ) ከተገደለ በኋላ ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ያፈረሰው መንግሥት ነው (ዳን 9፡26)። ክርስቶስ በ30 አካባቢ እንደተገደለና ቤተ መቅደሱንም ሮማውያን በ70 ላይ እንዳፈረሱት ይታወቃል። አራተኛው መንግሥት ከእስራኤል ጋር የሰባት አመት ቃል ኪዳን (የሠላም ስምምነት?) ይፈራረማል (ዳን 9፡27)። አራተኛው መንግሥት ይህንን ቃል ኪዳን የሚያደርገው በዘመኑ ፍፃሜ ላይ እንደገና ከሚመሠረተው የእስራኤል መንግሥት ጋር ነው። የእስራኤል መንግሥት ከተመሠረተበት ከ1948 ወዲህ እንደዚህ ዓይነት ስምምነት ከየትኛውም መንግሥት ጋር አልተፈራረመም። ስለዚህም ይኸ ገና ወደፊት ሊሆን ያለ ጉዳይ ነው ማለት ነው።

የሠላም ስምምነቱ ምን ምን ያካትት ይሆን? ዝርዝሩን ሁሉ አናውቅም። አንድ ዋና ነገር ብቻ እናውቃለን። ስምምነቱ እስራኤል ሦስተኛውን ቤተ መቅደስዋን መሥራት ያስችላታል (ዳን 9፡27)። እስራኤላውያኑ መስዋዕትና ቁርባን ለአምላካቸው ማቅረብ የቻሉት ቤተ መቅደሳቸውን እንደገና መሥራት ስለቻሉ መሆን አለበት። ቤተ

መቅደሱ በሌለበት መስዋዕትና ቁርባን ማቅረብ አይቻልምና (ዘዳ 12፡14)። አራተኛው መንግሥት ከእስራኤል መንግሥት ጋር የተጋባውን የሰባት አመት ቃል ኪዳን አጋማሹ ላይ የሚያፈርስ መንግሥት ነው። ስለሆነም ለሦስት አመት ተኩል "የያዕቆብ መከራ ዘመን" ምክንያት የሚሆነው መንግሥት ነው።

የመካከለኛው ምሥራቅ ዕንቆቅልሽ ፍች ማግኘት ያለበት መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። ያ ዕንቆቅልሽ እስካልተፈታ ድረስ በዓለም ላይ ማንም በሠላም መኖር እንደማይችል ከቀን ወደ ቀን የበለጠ ግልጽ እየሆነ ነው። እስራኤል ቤተ መቅደሰዋን የምትሠራ ከሆነ የመካከለኛው ምሥራቅ የፖለቲካ ችግር (ለጊዜውም እንኳን ቢሆን) ይፈታል ማለት ነው። ምክንያቱም ቤተ መቅደሱ የሚሠራበት ቦታ በእግዚአብሄር በራሱ የተወሰነ ቦታ ነው (2ኛ ዜና 3፡1)። የዚህ ቦታ አካባቢ አሁን በሁለት የሙስሊም መስጊዶች ተይዟል። በእስራኤላውያንና በአረቦች መካከል ለዘመናት የኖረው የፖለቲካ ችግር እልባት ሳይበጅለት እስራኤል ቤተ መቅደሰዋን መሥራት የምትችልበት ሁኔታ የሚኖር አይመስለኝም።

እስራኤል ቤተ መቅደስ እንደሚኖራት የሆነ እንደሆነ ግን ዳንኤል ብቻ አይደለም የተነበየው። ጌታ ኢየሱስ እራሱ ቤተ መቅደሱ እንደሚፈራርስና (ማቴ፣ 24፡1-2) እንደገናም እንደሚታነጽ ተንብዮአል (ማቴ 24፡15)። "በተቀደሰው ስፍራ" ማለት በቤተ መቅደሱ ማለት ነውና። ሐዋርያው ጳውሎስም ተመሳሳይ ትንቢት ጽፎአል (2ኛ ተሰ 2፡4)። ጳውሎስ ይህንን በሚጽፍበት ጊዜ ቤተ መቅደሱ ገና ስላልፈረሰ እየተነበየ እንደነበረ አላወቀም።

ቤተ መቅደሱን መሥራት የሚያስችላትን ስምምነት ለእስራኤል ሊሰጣት የሚችል መንግሥት አሁን በዓለም ላይ አለ ወይ? የለም። ይህንን የማድረግ አቅም ያለው አንድም መንግሥት ዛሬ በዓለም ላይ የለም። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ግን ያለ ጥርጥር ይኖራል። ያም መንግሥት በሚያስገርም ፍጥነት በማንሠራራት ላይ ያለው የጥንቱ የሮማ መንግሥት ነው። አራተኛው መንግሥት ማለት ነው።

የሮማ መንግሥት ማለት የኢጣልያ መንግሥት ማለት አይደለም። የጥንቱ የሮማ መንግሥት ዋና ከተማው ሮም ከመሆንዋ በስተቀር ከዛሬው የኢጣሊያ መንግሥት ጋር የሚጋራው ብዙ ነገር የለውም። በዘመኑ ፍፃሜ ላይ የሚያንሰራራው የሮማ መንግሥት መጠሪያውም ሆነ መናገሻው ሮም ላትሆን ትችላለች። ብዙ የትንቢት ተመራማሪዎች ያ መንግሥት "የተባበሩት የአውሮፓ መንግሥታት" እንደሚሆን ነው የሚያስቡት።

እንደዚህ የሚያስቡትም በቂ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይዘው ነው። እንደ ናቡከደነፆር ሕልም የባቢሎን መንግሥት እራስ ሲሆን የሮማ መንግሥት እግር ነው። ሁለት እግሮች ናቸው። በእራስና በእግሮች መካከል ሁለት መንግሥታት አልፈዋል። ሁለት እግሮች አስር ጣቶች አሉአቸው። የሮማ መንግሥት በረዥም ዕድሜው ከላይ ከጭን አካባቢ ጀምሮ አሁን ጣቶች ጋ ደርሷል (ዳን 2፡41-43)።

እንደ ዳንኤል ሕልም ደግሞ አራቱ አራዊት የሚወጡት ከሜዲትራንያን ባህር ውስጥ ነው (ዳን 7፡3)። በዓለም ታሪክ ሂደት ውስጥ ቁልፉን ሚና የሚጫወቱት አገሮችና መንግሥታት በዚህ ባህር አካባቢ ያሉት ናቸው። አራተኛው አውሬ ባለ አስር ቀንዶች ነው። ሌላ ትንሽ አስራ አንደኛ ቀንድ ሲበቅል ከአስሩ ቀንዶች ውስጥ ሦስቱ ይነቀላሉ። ሐዋርያው ዮሐንስ ከባህር (የሜዲትራንያን ባህር?) ሲወጣ በራእይ የሚያየው አውሬ አስር ቀንዶችና ሰባት እራሶች አሉት (ራእ 13፡1)። በአንድ መንግሥት ስር የሚተዳደሩ የአስር መንግሥታት ፌዴሬሽን።

> በእነዚያ ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ፈጽሞ የማይፈርስና ለሌላም ህዝብ የማይሰጥ መንግሥት ይመሠርታል። እነዚያን መንግሥታት ሁሉ ያደቅቃል፤ እስከ መጨረሻውም ያጠፋቸዋል። ይህ መንግሥት እራሱ ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል (ዳን 2፡44)።

አሁን ያለነው "በእነዚያ ነገሥታት" ዘመን ላይ ነው። "የአውሮፓ ሕብረት" አሁን በስሩ ከአስር በላይ መንግሥታት አሉት። በእነርሱም መካከል የጥንቱ የሮማ መንግሥት አካል የነበሩ ብዙ አገሮች አሉባቸው። ቁጥራቸው ወደ አስር እንዴት ዝቅ እንደሚል፣ ለሦስቱ ቀንዶች መነቃቀል ምክንያት የሚሆነው "ትንሽ ቀንድ" እንዴት እንሚበቅል ነው ገና የማናውቀው። ያ መንግሥት በምድር ላይ በጣም ኃያሉ መንግሥት ይሆናል። ከዕድሜውም በመጨረሻዎቹ አርባ ሁለት ወራት "የክርስቶስ ተቃዋሚ" በመባል በሚታወቀው ሰው ይመራል (1ኛ ዮሐ 2፡18)።

ምሳሌዎቹ

ከሌሎች ዘመናት ሁሉ ይልቅ የመጨረሻውን ዘመን መጨረሻ ለይተን እናውቅባቸው ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ አያሌ ምልክቶችን ይደረድርልናል። ከእነዚህም ውስጥ በጣም ወሳኝ (conclusive) የመሰሉኝን ሦስት ጥላዎችና ሦስት ምልክቶች ለማሳየት ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ ሁለት ምሳሌዎችን እናያለን።

እንደ ኖህ ዘመን

> ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም። ልክ በኖህ ዘመን እንደ ሆነው የሰው ልጅ መምጣትም እንደዚሁ ይሆናል። ከጥፋት ውሀ በፊት ኖህ ወደ መርከቡ እስከገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ሲበሉ ሲጠጡ፣ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደነበሩ፣ እስከዚያ ጊዜ ድረስም ምን እንደሚመጣ ሳያውቁ የጥፋት ውሀ እንዳጥለቀለቃቸው፣ የሰው ልጅ ድንገት ሲመጣም እንደዚሁ ይሆናል (ማቴ 24፡36-39)።

"የኖህ ዘመን" የአንድ አሠቃቂ የሆነ ፍርድ ዘመን ነው። በዚያ ፍርድ ከመላው የሰው ዘር ውስጥ በሕይወት የተረፉት ስምንት ሰዎች ብቻ ናቸው። እና ከአእዋፍ፣ ከእንሰሳትና ከአራዊት (ከአሦች)፣ ዝርያዎች ሁሉ ሁለት ሁለት ብቻ። ያ ፍርድ የሰው ልጅ ዕድሜም ከአንድ ሺህ ወደ አንድ መቶ ሐያ ጣራ ዝቅ የተደረገበት ነው። ለመሆኑ የዚህ ፍርድ መነሾ ምን ነበር?

> ሰዎች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው። የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ውብ ሆነው አዩአቸው፤ ከመካከላቸውም የመረጡአቸውን አገቡ። እግዚአብሔርም ሰው ሟች ስለ ሆነ መንፈሴ እያዘነ ከእርሱ ጋር ለዘላለም አይኖርም። ዕድሜው 120 አመት ይሆናል። . . . እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፤ ልቡም እጅግ አዘነ። ስለዚህም እግዚአብሔር የፈጠርሁትን የሰው ዘር ከምድር ገጽ አጠፋለሁ . . . ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና አለ (ዘፍ 6፡1-8)።

በነገራችን ላይ የሰው ዕድሜ በሙሴ ዘመን ከ120 ወደ 70 እና 80 ዝቅ ብሎ ነበር (መዝ 90፡10)። ሙሴ 120 አመት የኖረ ቢሆንም እንኳን የእርሱ የሥርዓቱ (the rule) ሳይሆን የአስተያየቱ (the exception) ነበር።

ኖህ ያንን የሚያህል ትልቅ መርከብ ለመሥራት ብዙ አመታት እንደ ወሰደበት መገመት ይቻላል። መርከቡን ይሠራ የነበረውም ሰው ሁሉ ሊያየው በሚችልበት ሜዳ ላይ እንደሚሆን መገመት አይከብድም። የሚያዩትም ሁሉ ምን እያደረገ እንደሆነ ሳይጠይቁት አይቀሩም። እርሱም እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ሳይነግራቸው አይቀርም። እነርሱ ግን የነገራቸውን አላመኑትም። "በእምነቱ ዓለምን ኮነነ" የተባለለት ለዚህ ነውና (ዕብ 11፡7)። ስለ እነርሱም "በኖህ ዘመን መርከብ ሲሠራ እግዚአብሔር በትዕግሥት ይጠብቃቸው

የነበሩ እምቢተኞች . . .” የተባለው በዚሁ ምክንያት ነው‡ (1ኛ ጴጥ 3፡20)።

“የሰው ልጅ ሲመጣም እንደዚሁ ይሆናል” ነው ጌታ ያለን። “እንደዚሁ ይሆናል” ማለት ሦስት ነገር ማለት ነው የሚሆነው። አንደኛ የሰዎች አጀንዳ መብል፣ መጠጥና አውስቦ (ወሲብ) ይሆናል ማለት ነው። አውስቦውም በኖህ ዘመን እንደነበረው በመናፍስትና በሰዎች መካከል እስከ መሆን ይደርሳል ማለት ነው። ይህ ዛሬ ሊጸፍለትና ሊወራለት የጀመረ ጉዳይ ነው።

እንኳን የመናፍስቱ ተጨምሮበት ሰብአዊውስ ቢሆን ዛሬ ቅጡን አላጣም? ወሲብ ነክ ወንጀሎች በዓለም ዙሪያ እንደዚህ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሱበት ጊዜ አለ? የ60 አመት አረጋዊ በ6 አመት ሕፃን ላይ እንደዚህ ዓይነት ወንጀል እንደ ፈፀመ፣ አባት የገዛ ሴት ልጁን እንደ ደፈረ በመገናኛ ብዙኃን መስማት የለመድንበት እንደዚህ ያለ ሌላ ጊዜ ነበረ? እንደዚህ ዓይነቱ ድርጊትስ በእውነት “ሰብአዊ” ብቻ ሊሆን ይችላል? መናፍስታዊ ቁምር ሳይሆን ይቀራል?

ሁለተኛ ታላቅ የሆነው የእግዚአብሔር ትዕግሥት የሚገለጥበት ጊዜ ይሆናል ማለት ነው። ዛሬ በዓለም ዙሪያ፣ በተለይም በአውስቦ ረገድ፣ የሰው ልጅ የዘቀጠበትን አዘቅት ስናይና ስንሰማ “እስከ መቼ ትታገሳለህ? እስከ መቼስ አትፈርድም?” እንለዋለን። ለእኛ ለኃጢአተኞቹ እንኳን ነገሩ አልፎ አልፎ የማይቻል ይሆንብናል። ሦስተኛ የጌታ ዳግም ምጽአት መቅረቡ፣ ፍርድም በደጅ መሆኑ ለዓለም ሁሉ ይሰበካል ማለት ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው ይኸ መቼም አሁን በሚያስገርም ዓይነት በዓለም ሁሉ እየሆነ ያለ ነገር ነው። በመጨረሻም ብዙ ሰዎች ስብከቱን ለመስማትና ለማመን አይፈልጉም ማለት ነው። በራሳቸው አጀንዳ ተይዘዋል። ተወጥረዋል። ለሌላ ለምንም ነገር ጊዜ የላቸውም።

እንደ ሎጥ ዘመን

> በሎጥ ዘመን እንዲሁ ነበር። ሰዎች ይበሉና ይጠጡ፣ ይገዙና ይሸጡ፣ ተክል ይተክሉና ቤት የሠሩ ነበር። ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ዕለት ግን እሳትና ዲን ከሰማይ ዘንቦ በሙሉ አጠፋቸው። የሰው ልጅ በሚገለጥበትም ቀን እንደዚሁ ይሆናል . . . የሎጥን ሚስት አስታውሱ (ሉቃ 17፡28-32)።

“የሎጥ ዘመን” የአንድ ሌላ አሰቃቂ የሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ ዘመን ነው። የኖህ ዘመኑ ፍርድ የተፈፀመው በውሀ በማጥለቅለቅ ሲሆን የሎጥ ዘመኑ ፍርድ ግን በእሳት በማጋየት ነው የተፈፀመው። የኖህ ዘመኑ ፍርድ በይዘቱ ዓለም አቀፋዊ የነበረ ይመስላል። የሎጥ ዘመኑ ግን ሰዶምና ገሞራ፣ አዳማና ሲባዮ፣ የተባሉ ከተሞችን ብቻ ነው ነጥሎ ያጠፋቸው። እነዚህ ከተሞች ዛሬ የሙት ባህር በሚገኝበት አካባቢ ነው የነበሩት።

ሙት ባህር ውሀ ከእሩብ እጅ በላይ የሚሆነው የማግኒዝየም እና የሶዲየም ክሎራይዶች ነው የሚባለው። በዚህም የሚመስለው ሌላ ውሀ በዓለም ላይ እስከ አሁን ድረስ አልተገኘም። በሙት ባህር ውስጥ ምንም ዓይነት ሕይወት አይኖርም። በሙት ባህር ላይ ለመንሳፈፍ ውሀ ዋና ማወቅ አይጠይቅም። በሙት ባህር ላይ የማይቻል ነገር መስጠም ነው።

ከአራት በላይ ወንዞች ውሀቸውን የሚገብሩለት ቢሆንም ከሙት ባህር ግን አንድ ጠብታ ውሀ እንኳን ወደ ውጭ አይፈስም። ጨውማው ውሀ ጣዕሙ አይቀየርም። ሙትነቱም በሕያውነት አይተካም። በጣም ሞቃት ከሆነው የአካባቢው የዓየር ንብረት የተነሳ ብዙ ውሀ ይተነዋል። ስለሆነም ወንዞቹ የሚገብሩለት ውሀ የትኑን ሚዛን ለማስተካከል ብቻ ነው የሚውለው። የሙት ባህር ዝቅታ (መቼም ከፍታ ሊባል አይችልም) ከሚዲትራኒያን ባህር ወለል በታች በአማካይ 1300 ሜማ ነው።

ይህ አካባቢ እንደዚህ ከመቃጠሉ፣ እንደዚህ ከመክሰሉና አመድ ከመሆኑ በፊት “. . . እንደ እግዚአብሔር ገነት፣ በዞአር አትጣጫ እንዳለው እንደ ግብፅ ምድር ውሀማ . . .” ነበረ (ዘፍ፣ 13፡10)። የአካባቢው ልምላሜ ሎጥን ምንኛ እንዳማለለው መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። እንደዚህ ለም የነበረው አካባቢ አሁን እንዴት እንደዚህ ሆነ?

> ኃጢአት ለሚያደርጉ ሁሉ ምሳሌ እንዲሆኑ የሰዶምን እና የገሞራን ከተሞች አመድ እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎ ከፈረደባቸው . . .(2ኛ ጴጥ 2፡6)።

የሰዶምና የገሞራ ምሳሌነታቸው በምንድነው? በሦስት ነገሮች ነው። እንደኛ በኃጢአታቸው ዓይነት (ዘፍ 19፡4-9)። “ግብረ ሰዶም” በመባል የሚታወቀው የሩካቤ ሥጋ ዓይነት የተጀመረው በዚያ ነው ይባላል። ይህንን በእንስሳትና በአራዊት ዓለም እንኳን የሌለ ድርጊት ሰልጥነዋል የሚባሉት አገሮች ዛሬ ሕጋዊ አድርገውታል። በእነዚህ አገሮች የሚገኙ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያንም ሳይቀሩ ግብረ

ሰዶማውያንን በመድረክቻቸው ላይ በማጋባት ቅዱሱን ጋብቻ በማርከስ አገልግሉት ላይ ተሰማርተዋል።

ሁለተኛ ይኸ ኃጢአት በተለይ የእግዚአብሔርን ቁጣ ቀስቃሽ በመሆኑ። . . . በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አሳፋሪ ለሆነ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው። ሴቶቻቸውም እንኳን ለባሀርያቸው የሚገባውን ግንኙነት ባሀርያቸው ላልሆነው ግንኙነት ለወጡ። እንደዚሁም ወንዶች ለባሀርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወት ተቃጠሉ። ወንዶች ከወንዶች ጋር ነውርን ፈፀሙ። ለክፉ አድራጎታቸውም የሚገባቸውን ቅጣት በገዛ ራሳቸው ላይ አመጡ (ሮሜ 1:24-27)።

ዛሬ በዓለም ዙሪያ ለዚህ "አሳፋሪ ለሆነ ምኞት" እግዚአብሔር አሳልፎ የሰጣቸውን ሰዎች ቁጥር ብዛት ስንመለከት የዓለማችን የፍርድ ጽዋ ሞልቶ በመፍሰስ ላይ መሆኑን እንገነዘባለን። እግዚአብሔርም ይህንን ሁኔታ ከእንግዲህ ወዲህ ለረዥም ጊዜ ሊታገሰው እንደማይችል እንረዳለን።

ሦስተኛ የሰዎችን ህሊና በተጫነው የድንዛዜ ሜና። የሎጥ ሚስት የከተማዋን እርኩሰት ማስተዋል ተስኖአት ነበር። ከተማዋን ሊያጠፋ ከእግዚአብሔር የተላኩት ሁለት መላእክት በቤትዋ ነበር በእንግድነት ያደሩት። የመኝታ ሰአት ሲደርስ የከተማዋ ወጣቶችና ሽማግሌዎች በደጅዋ ተከማችተው ከእንግዶቹ "ሰዎች" ጋር ወሲብ ካልፈፀምን በማለት ያሉት አምባጓሮ ህሊናዋን አላቆሰለውም። ባሏ ሎጥ እንግዶቹን "ሰዎች" ከዚያ አደጋ ለማዳን ሲል በምትካቸው ሁለት ልጃገረዶች ልጆቹን ልስጣችሁ ማለቱ አላሰቀቃትም። ሕሊናዋ ደንዝዞአል።

የሎጥ ሚስት የእግዚአብሔርም ባህርይ ጠፍቷታል። ይኸ ሁሉ እንደዚህ ሊቀጥል እንደማይችል፣ አንድ ቀን እግዚአብሔር መፍረዱ እንደማይቀር ማሰብ አቅቷታል። ልቧ ያለው በሰዶም ባካበተችውና ገናም በምታካብተው ካብት ላይ ብቻ ነው። እጅጉ በመላእክት ተይዘው ከሰዶም ብትወጣም እንኳን ልቧ አልንቀሳቀስልሽ አላት። እናም ከሰዶም ወጥታም ሳትወጣ ቀረች። በዚህም የመላእክቱን ድካም ሳይቀር መና አስቀረች።

ዛሬ የተወሰነ አካባቢ ብቻ ሳይሆን ዓለሙ በሙሉ እንደ ሰዶምና ገሞራ ሆኖአል። ከአስራ ሁለት አመት በፊት የነበረ ስታቲስቲክ እንደሚያሳየው የወንዶች ግብረ ሰዶማውያን ቁጥር በዚያን ጊዜ 80 ሚልዮን ደርሶ ነበር። የሴቶቹ ደግሞ 30 ሚልዮን ነበረ። በዚያ ጊዜ

የዓለሙ ሕዝብ ቁጥር 5,164,000,000 ገደማ ነበረ። ከዚህ ውስጥ ዕድሜአቸው በዚያን ጊዜ ከ15 አመት በታች የነበረውን 1,659,000,000 ብንቀንስ ከተረፉት ውስጥ ግብረ ሰዶማውያኑ ከሦስት በመቶ በላይ ናቸው[3]። ዕድሜአቸው ከ15 አመት በታች የሆነውን የቀነስኩት ገና ልጆች ናቸው በማለት ነው። ዛሬ ይኸ አሐዝ ሦስት በመቶ ላይ እንደነበረ እንደማይሆን ማንም ሊገምት ይችላል። በጣም ከፍ ይላል ማለቴ ነው።

እኛ "ጥሬዎቹ" ኢትዮጵያውያን እንኳን እንደዚህ ባለው ወረ መደንገጥም፣ መደነቅም፣ መቆጣትም ከተውን ሰነባበትን። ለመድነው ማለት ነው። ፖርኖግራፊው፣ ማለትም ጋዜጣው፣ መጽሔቱ፣ ፎቶግራፉ፣ ቪድዮው፣ ቴሌቪዥኑ ሁሉ ግንባር ፈጥረው ዘመቱብን። ወጉን። አዳሸቁን። አልፈሰፈሱን። አፈዘዙን። አደነዘዙን። የኃጢአት ኃጢአትነትም ሆነ የእግዚአብሔር ቅዱስነት ጠፋን። ነገሩ ግን እንደዚህ አይቀጥልም። ጊዜው አልቋል። ፍርድ በደጅ ነው።

ማስጠንቀቂያዎቹ

ይህንን ምዕራፍ፣ ይህችንም መጽሐፍ መጨረሱ ነው። እስከ አሁን ድረስ ወደ 120 በሚሆኑ የተለያዩ ርዕሶች ላይ ለማለት የፈለግሁትን ከሞላ ጎደል ብያለሁ። አሁን ግን ምዕራፉንም፣ መጽሐፍዋንም የማድመደምደም አለብኝ። ግን በምን ልደምድም? ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሱ በምንድነው እራሱን የሚደመድመው? "በቶሎ እመጣለሁ" በሚል ኃይለ ቃል ነው (ራእ፣ 22:20)።

ይኸ ኃይለ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ምዕራፍ ውስጥ ሦስት ጊዜ ነው የተጠቀሰው (7፣12)። ሦስት ጊዜ የተጠቀሰው በአጋጣሚ ይሆን? ለጉዳዩ አፅንኦት ለመስጠት ሲባል ብቻ ይሆን? ሦስት የእግዚአብሔር ቁጥር ስለሆነ ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱሱስ አጨራረስ የሚያጽናና ነው ወይስ የሚያስጠነቅቅ? ሁለቱንም ነው። "ማስጠንቀቂያዎቹ" በሚለው በዚህ ርዕስ እኔም የመጽሐፍ ቅዱሱን ፈለግ ለመከተል ነው የምፈልገው።

እንደ ሌባ

እንግዲህ ጌታችሁ በየትኛው ቀን እንደሚመጣ አታውቁምና ተግታችሁ ጠብቁ። ነገር ግን ይህን ዕወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ሰዓት ሌባ እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ ነቅቶ በጠበቀ

ነበር፤ ቤቱም እንዲቆፍር ባልተወም ነበር (ማቴ 24:42-43)።

ስለ ጌታ ዳግም ምፅአት ሲያስተምር ጴጥሮስም ይህንኑ አባባል ተጠቅሞበታል።

> የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ በድንገት ይመጣል (2ኛ ጴጥ 3:10)።

ምንድነው እየተባልን ያለነው? "ዕወቁ" ነው። "ንቁ" ነው። "ጠብቁ" ነው። ለምንድነው መንቃት ያለብን? ለምንድነው መጠበቅስ ያለብን? ጊዜው ስለማይታወቅ ነው። አመጣጡ "እንደ ሌባ" አመጣጥ ስለሚሆን ነው። ባላሰብነው ጊዜ ስለሚሆን ነው።

ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው የጊዜውን መቅረብ የሚያመላክቱ ብዙ ምልክቶች ተሰጥተዋል። ብዙ ሰዎች ግን ምልክቶቹን ልብ ብለው አያስተውሉአቸውም። እንደ ኖህና እንደ ሉጥ ዘመናት ዘመናችን በማዘናጋት ብርቱ ነው። "እንደ ሌባ" የሚለውን ሀሳብ በሚገባ ለመረዳት የጌታ ዳግም ምጽአት በሁለት ሁኔታዎች እንደሚፈፀም ማወቅ ይጠቅማል።

በመጀመሪያ ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ እራሱ ለመውሰድ ይመጣል። በዚህኛው መምጣቱ ጊዜ ጌታ አሁን ተቀምጦ ካለበት ከአግዚአብሄር አብ "ቀኝ" ተነስቶ ነው የሚመጣው። ሆኖም እስከ ምድር ድረስ አይመጣም። እርሱ እራሱ ስለዚህኛው አመጣጡ ሲናገር፦

> እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፣ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ

ነበር ያለው (ዮሐ 14:3)። "እመጣለሁ"፣ "እወስዳችኋለሁ" ማለት ምን ዓይነት አነጋገር ነው? እርሱ ወደ መሬት ይመጣል፣ እኛንም ከመሬት ይወስደናል ማለት ነው። ስንገናኝ እርሱም በአብ ቀኝ እኛም መሬት ላይ አንሆንም ማለት ነው። ይህኛውን አመጣጡን ነው መጽሐፍ ቅዱሱ "መነጠቅ" ብሎ የሚጠራው።

> የትዕዛዝ ድምፅ፣ የመላእክት አለቃ ድምፅ፣ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማልና፣ ጌታ እራሱም ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስ አምነው የሞቱትም አስቀድመው ይነሳሉ። ከዚህ በኋላ እኛ በሕይወት የምንገኘው ጌታን በዓየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን። ለዘላለምም ከጌታ ጋር እንሆናለን (1ኛ ተሰ 4:16-17)።

ስለዚህ በዚህኛው አመጣጡ ጌታ ወደ መሬት አይመጣም። ቤተ ክርስቲያን ግን ከመሬት ላይ በአካል ወደ እርሱ ትነጠቃለች። እርሱ ከሰማይ ይወርዳል። ቤተ ክርስቲያንም ከምድር ወደ ሰማይ

ትወጣለች። የሚገናኙበት ቦታ "ዓየር ላይ" ብቻ ነው የተባለው። ይህኛው የጌታ አመጣጥ ነው ጊዜው የማይታወቀው። ይህኛው የጌታ አመጣጥ ነው "እንደ ሌባ" የተባለው።

ሁለተኛው ጌታ ወደ እራሱ የነጠቃትን ቤተ ክርስቲያን አስከትሎ በአካል ወደ መሬት ይመጣል። ይህኛው አመጣጡ መቼ እንደሚሆን በትክክል ይታወቃል። ያንሰራሩት የእስራኤልና የሮማ መንግሥታት የሚፈራረሙት የሰባት አመታት የሰላም ስምምነት ማብቂያ ላይ ነው። የሮማ መንግሥት መሪ ያንን ስምምነት በዕድሜው እኩሌታ ላይ እንደሚያፈርሰውም በቅድሚያ ይታወቃል። ይህም ብቻ አይደለም። ስምምነቱ የሚፈርስበትንም ምክንያት እንኪን ሳይቀር በቅድሚያ የምናውቀው ይመስለኛል። የሮማው መንግሥት መሪ በሰባቱ አመት እኩሌታ ላይ "መስዋዕትና ቁርባን ማቅረብን ይከለክላል" (ዳን 9:27) ለምንድነው የሚከለክለው? እርሱ እራሱ ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ "እኔ አምላክ ነኝ" ስለሚል ነው (2ኛ ተሰ 2:4)።

የሰውየው ማንነት የሚገለጠው በዚህ ጊዜ ነው። ለካ የሚፈልገው አምልኮ ኖሮአል? ለካ የሚፈልገው የሰዎችን ነፍስ ኖሮአል? ይህን ካላገኘ በስተቀር ዓለሙን ሁሉ ቢገዛም እንኳን ለካ የልቡ አይደርስም? ይህንን ፍላጎቱን ደብቆ ነበር እስከዚያ ጊዜ ድረስ የቆየው። ለመደበቂያ የተጠቀመባቸው የተለያዩ ጭንብሎች ነበሩት። ጭንብሎቹ አሁንም ያለቁበት አይመስለኝም። ጊዜው ግን አለቀበት። ስለዚህም ተገለጠ። ወይም ለመገለጥ ተገደደ። የእስራኤልን አምልኮ በይፋ ጠየቀ። እስራኤል ደግሞ ይህንን ልትሰጠው አትችልም። ከጌታም ጋር ያጣላት ይኸው ነበር። ". . . እኛ የምንወግርህ . . . ሰው ሆነህ ሳለ ራስህን አምላክ ስላደረግህ ነው" (ዮሐ 10:33)።

የሮማው መንግሥት የመጨረሻ መሪ መጽሐፍ ቅዱስ "የክርስቶስ ተቃዋሚ" እያለ የሚጠራው ሰው መሆኑን ቀደም ሲል ጠቅሻለሁ። "የዓመፅ ሰው" እያለም ይጠራዋል (2ኛ ተሰ 2:3)። "አውሬው"ም ይለዋል (ራእ 13)። በዚያ ጊዜ ዲያብሎስ በምድር ላይ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴው አድርጎ የሚያስነሳው ሰው ነው (ራእ 13:2)። ይህ ሰው ከእስራኤል መንግሥት ጋር የሠላም ስምምነት ከሚፈራረምበት ጊዜ አንስቶ እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት ድረስ የሚኖረው ጊዜ ሰባት አመት ብቻ ነው። የረዘመም እንደሆነ የሚረዝመው በሁለት ተኩል ወራት ብቻ ነው የሚሆነው (ዳን 12:11-12)።

በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ አትሆንም። ከሆነችማ የጌታ አመጣጡ ምኑን "እንደ ሌባ" አመጣጥ ሆነው? ስምምነቱ እኮ ሲፈረም የጌታ መምጫ ታወቀ ማለት ነው። ለስድስተኛዋስ ቤተ

ክርስቲያን ምኑን "- - - በዓለም ሁሉ ላይ ከሚመጣው ከመከራው ሰዓት አድንሃለሁ" ተባለ? የ"ታላቁ መከራ" ጊዜ የሚባለውኮ የሠላም ስምምነቱ ከፈረሰ በኋላ ያለው የሦስት ተኩል አመታት ጊዜ ነው። መጨረሻው ከመጀመሪያው የታወቀ ነው ማለቴ ነው።

እርግጥ በዚህ በኋለኛው የሦስት ተኩል አመታት ጊዜም ቢሆን ወንጌል በምድር ላይ ይሰበካል። ስብከቱም በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደነበረው ዓይነት በሆነ አስደንጋጭና አስገራሚ ተዓምራት ይታጀባል (ራእ 11፡1-13፤ 14፡6-12)። በዚህ የስብከት አገልግሎት መካከለኛውን ስፍራ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ግን እስራኤላውያን ናቸው (ራእ 7፡1-8)። የዚያን ጊዜ ምዕመናንም "ከታላቁ መከራ የመጡ" ተብለው በተለይ ተጠቅሰዋል (ራእ 7፡13-14)። ቤተ ክርስቲያን በ"ታላቁ መከራ" እንደማታልፍማ አዲስ ኪዳን በግልጽ የሚያስተምረው ጉዳይ ነው፦

> ወንድሞች ሆይ፤ ይህ ነገር ስለሚሆንበት ዘመንና ጊዜ ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልግም። ምክንያቱም የጌታ ቀን የሚመጣው ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ ዓይነት መሆኑን እናንተ እራሳችሁ ደህና አድርጋችሁ ታውቃላችሁ። ሰዎች "ሁሉ ነገር ሰላምና ደህና ነው" ሲሉ፣ እርጉዝ ሴት ምጥ እንደሚይዛት ዓይነት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል። በምንም ዓይነት አያመልጡም። እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ፤ በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም። ስለዚህ ቀኑ እንደ ሌባ አይመጣባችሁም። ምክንያቱም . . .። እግዚአብሔር የጠራን ለቁጣ ሳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ደህንነትን እንድናገኝ ነው (1ኛ ተሰ 5፡1-9)።

ያ ቀን በቤተ ክርስቲያን ላይ "እንደ ሌባ" እንዲመጣባት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ያ ቀን እንደ ሌባ በድንገት የሚመጣባቸው በጨለማ ውስጥ ያሉት ናቸው። ያ ቀን እንደ ሌባ በድንገት የሚመጣባቸው በማንቀላፋት ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ የሚወተውተው ሰዎች ማስጠንቀቂያውን ሰምተው፣ ማድረግ የሚገባቸውንም አድርገው፣ በዓለም ላይ በድንገት ሊመጣ ካለው ጥፋት እንዲድኑ ነው።

እንደ ወጥመድ

> እንግዲህ በገደብ የለሽ ሕይወት፣ በመጠጥ ብዛትና ስለ ኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እንዳይዝልና ያ ቀን እንደ ወጥመድ ድንገት እንዳይደርስባችሁ ተጠንቀቁ። ይህ በመላው ምድር በሚኖሩት ሁሉ ላይ ይደርሳልና። ስለዚህ ከሚመጣው ሁሉ

> እንድታመልጡና በሰው ልጅ ፊት መቆም እንድትችሉ ሁል ጊዜ ተግታችሁ ጸልዩ (ሉቃ 21፡34-36)።

ይኸ "ወጥመድ" የተባለ ነገር ሊደርስ ያለው በአንዳንድ አካባቢዎች ብቻ ሳይሆን "በመላው ምድር" ላይ ነው። የሚደርሰውም በ"ድንገት" ነው። የጌታ ፈቃድ ግን ግልፅ ነው። ያ ወጥመድ የተባለ ነገር በማንም ሰው ላይ እንዳይደርስ ነው።

ይኸ "ወጥመድ" የተባለ ነገር ምንድነው እሱ? "ታላቁ መከራ" (the great tribulation) የሚባለው ነው። "የያዕቆብ መከራ" ያልነው ነው። የያዕቆብ መከራ ይባል እንጂ እንዳየነው መከራው የሚመጣው በዓለም ሁሉ ላይ ነው። ስለተመረጡት ሲል እግዚአብሔር ጊዜውን ባያሳጥረው ኖሮ "ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልተረፈ ነበር" የተባለለት ነው (ማቴ፣ 24፡22)። ይህች ምድር ብዙ መከራ ተፈራርቆባታል። የዚያን ዓይነት መከራ ግን በዕድሜዋ ሁሉ አይታ አታውቅም። ከዚህ መከራ የሚያመልጡት "በጌታ ፊት መቆም" የሚችሉት ብቻ ናቸው። በጌታ ፊት መቆም የሚችሉት ማለትም የሚነጠቁት ማለት ነው።

ተዘጋጅታችሁ ኑሩ

መጽሐፍ ቅዱሱ የሚለውን ማለቱ ከሆነ ያለ ጥርጥር ጊዜው አልቋል። ስድስተኛው ቀን ተጠናቋል። ስድስተኛውም ዘመን ሊጠናቀቅ ነው። ስድስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ነን። ስድስተኛው በዓላችን ላይ ነው ያለነው። ይኸ "ስድስት" ተደጋገመ አይደል? አዎ፣ የሰው ቁጥር ስለሆነ ነው። ጽዋው ሞላ ማለት ነው። ሦስት ስድስቶችን መለያው የሚያደርገውም ሰው በቅርቡ በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ይላል። ሦስት የአምላክ ቁጥር ነው። ስድስት ሦስት ጊዜ ማለት ሰው "አምላክ ነኝ" ሲል ማለት ነው።

"የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ" የዚያ ሰው መንገድ ጠራጊ ነው። ምንጩ ተቃራኒው ኃይል ከመሆኑ በስተቀር እሱም እኮ ሪቫይቫል ነው - የጨለማው ኃይል የመጨረሻ ሪቫይቫል። የመጨረሻው ዘመን መጨረሻኮ በአንድ በኩል ድቅድቅ ጨለማ ሕዝቦችን የሚሸፍንበት፣ በሌላም በኩል የእግዚአብሔር ብርሐን በቤቱ ላይ ደምቆ የሚወጣበት ጊዜ ነው (ኢሳ 60፡1-3)። የሁለት ተፃራሪ ሪቫይቫሎች ጊዜ ነው ማለት ነው።

"አምላክ ነኝ የሚለው" የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ትምህርት የተጀመረው ጥንት በመላዕክቱ ዓለም ውስጥ ነበር። በኋላ በኤደን

ገነት በመጀመሪያዎቹ ሰዎች መካከል ተደገመ። አሁን እሱም ዓለም አቀፋዊ መልክ አግኝቷል። በ"ክርስቶስ መስቀል" ላይ የማያተኩሩ ትምህርቶች ሁሉ በጥንቃቄ ነው መጤን ያለባቸው።

የመጨረሻዋ ቤተ ክርስቲያን ነን። ትውልዱም ምናልባት የመጨረሻው ትውልድ። መጪው ሪቫይቫልም የመጨረሻው ሪቫይቫል ነው። ዓለም አቀፋዊ ይዘት የተሰጠውና የዚህን ያህል ቅድመ ዝግጅት እየተደረገበት ያለው ለዚህ መሆን አለበት። በቤተ ክርስቲያንዋ ፊት "መነጠቅ" በትውልዱም ፊት "ታላቁ መከራ" አሉ። ከገሃነመ እሳት ጋር ሲነፃፀር ታላቁ መከራ ማለት ምንም ማለት ላይመስለን ይችል ይሆናል። ዓለማችን በእድሜዋ ከአየቻቸው ብዙ መከራዎች ጋር ሲነፃፀር ግን "ታላቅ" ተብሏል። እግዚአብሔር "ታላቅ" ያለውን ታናሽ አድርገን ባናየው ደግ ነው።

በዓለም ዙሪያ አሁን ብዙ ሰዎች በብዙ መከራ ውስጥ አሉ። በአብዛኛዎቻቸውም ፊት ደግሞ ገና "ታላቁ መከራ" አለ። እግዚአብሔር ለእነዚህ የመጨረሻውን ሪቫይቫል የሚልክላቸው ሊያደላድላቸው ፈልጎ ሊሆን አይችልም። ሊያስመልጣቸው ፈልጎ ነው ሊሆን የሚችለው። እንግዲያው እኛም ስለ መደላደል ልናስብ አንችልም። አይገባንም። ልናስብ የሚገባን ለራሳችን ስለ ማምለጥ ነው። ልናስብ የሚገባን ሌሎችንም ስለ ማስመለጥ ነው - ከታላቁ መከራ። ከገሃነመ እሳትም።

> . . . የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ስለሚመጣ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ (ማቴ 24:44)

ማለት ይህንን ማለት ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው።

ብዙ ምዕመናን በዚህ ረገድ እንዳይሳሳቱ ይፈራሉ። ከዚህ ቀደም ብዙዎች እንደተሳሳቱና ብዙዎችንም እንዳሳሳቱ ስለሚያውቁ ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሄድንበት አካሄድ ግን ከእነዚያ አካሄድ ፈፅሞ የተለየ ነው። "መሳሳት" የምንለው እንደዚህ አይነቱን አካሄድ ሁሉ ከሆነማ፣ ዘንድሮ እንደማይመጣ ገምቶ "ልክ" ከመሆን ይልቅ ዛሬ እንደሚመጣ ጠብቆ "መሳሳት" ነው የሚመረጠው።

አሜን፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ቶሎ ና!

አስር

የግርጌ ማስታወሻዎች

1 ኤኪውሜኒካል እንቅስቃሴ በአገር አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በአብያተ ክርስቲያን መካከል መቀራረብንና መተባበርን የሚያበረታታ እንቅስቃሴ ነው። "የዓለም አብያተ ክርስቲያን ጉባዔ" እና እንዲሁም በየአገሩ ያሉት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ሕብረቶች የዚህ እንቅስቃሴ አካላት ናቸው። እንደ የተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበራት ያሉ አብያተ ክርስቲያን አጋዥ ድርጅቶችም በተዘዋዋሪ መንገድ የዚሁ እንቅስቃሴ አካላት ናቸው።

2 Smith, Oswald J. "Prophecy-What Lies Ahead?", Marshall, Morgan & Scott, Ltd 1952. Pp.82

3 Barrett, David B. and Jansen, Frank K. "The World in Figures", Lausanne II, July 1989

በምድረ በዳ ሲጓዙ የእሥራኤል ልጆች አሰላለፍ

